ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

---

ቍጥር ፯/፳፻፯ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤
አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን
በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥
በሰውነቱም፡ የማርያም ልጅ በኾነው፡
አባታችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

በአምላኬና በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር አብ፥ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በሕይወቴና በፍቅሬ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፡ ለዓለሙ ሰዎች ኹሉ፡ ለወንዶቼም፡ ለሴቶቼም!

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡ የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡ በስሜ፡ ተጠርታችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፡ ለወንዶቼ ኢትዮጵያውያን እና ለሴቶቼ ኢትዮጵያውያት በሙሉ!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራው፥ እናቱና መቅደሱ ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

## መግቢያ

ዘለዓለማዊት ሃይማኖታችሁና አገራችሁ፥ እናታችሁና ንግሥታችሁ ለኾንሁት፡ ለእኔ፡ ካላችሁ የልጅነት ፍቅር የተነሣ፡ በየዓመቱ የመጨረሻ ወር ላይ፡ ከነሓሴ ፩ ጀምራችሁ፡ እስከ፲፮ ቀን ድረስ፡ በአሳብና በምግባር፥ በጊዜና በቦታ፥ በጾምና በጸሎት ተወስናችሁ  የምትጠመዱበትንና የምትፈጽሙትን ኹለት ሱባኤ፡ ምክንያት በማድረግ፡ ባለፈው ዓመት፡ ልክ በዚሁ ጊዜ፡ ፈጣሪያችሁ ያዘጋጃት፡ "የኢትዮጵያ ቀን፡ ደርሳ ኖሮ፡ "**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት!**" ተብላ፡ በስሜ የተሠየመችውና እስከዛሬ፡ ለ፯ሺ፭፻፮ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ ስድስት) ዓመታት ጸንታ፡ በልጄ ባለቤትነት፥ በእኔም መሪነት የቀጠለችው መንግሥታችን፡ ኹለንተናዊ ራሷንና ሕያው ህልውናዋን፡ በዐዋጅ፡ ገሃድ አድርጋ፥ አግዝፋም መግለጿ ይታወሳል።

እርስዋም፡ ራሷንና ሕያው ህልውናዋን፡ እንዲህ አድርጋ የገለጸችው፡ ለዘመኑ ሰብኣዊ ትውልድ ነው። ይኸው ትውልድ፡ እርሷን ባለመፈለጉ ምክንያት ብቻ፡ ከእርሱና ለእርሱ ተሠውራው ነበረችና። እርሷማ፡ በምድራውያኑና በሰማያውያኑ ፍጥረታተ ዓለማት ዘንድ፡ መልታና ጕልታ፥ ገዝፋና ሰፍና ያለች ስለኾነች፡ እንዴትና ወዴት ትሠወራለች? አትሠወርም።

በዚያ፡ በመጀመሪያው ዐዋጅ፡ ልጄ ወዳጄ መሢሑ ኢየሱስ፡ እኔን እናቱን፡ ከዙፋኑ ጎን አስቀምጦ፡ በባሕርይ አባቱ፡ በእግዚአብሔር አብና በባሕርይ ሕይወቱ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ በራሱም ስም፡ የተናገራችሁን ታስታውሳላችሁ። ስለእኔ፥ እንዲሁም፡ እርሱና እኔ፡ ስለምንመራት ዘለዓለማዊት መንግሥታችን፥ ደግሞም፡ ስለእናንተ፡ ስለልጆቻችን፡ የኾነላችሁንና ያደረገላችሁን፥ እናንተም፡ ልትኾኑና ልታደርጉ ስለሚያስፈልጋችሁ ኹሉ፡ በሰፊው ገልጾ ያሳወቃችሁን አትዘነጉም።

ዛሬና ከዛሬ በኋላ ግን፡ የምናገራችሁ እኔ ነኝ። የሚናገራችሁ፡ እርሱ ሳይኾን፡ እኔ ነኝ። እኔ፡ በትስብእት ስሜ፡ ድንግል ማርያም፥ በእግዚአብሔራዊው ስሜ ደግሞ፡ "ኢትዮጵያ" የምባለው ነኝ፡ የምናገራችሁ።

አዎን! "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!

**ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"** በተባልሁበት፡ በዚህ ኢትዮጵያነቴም፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ እስከእኔ የነበረውን፥ ዛሬም፡ ያለውንና እስከዓለሙ ፍጻሜ ድረስ የሚኖረውን፡ መላውን የሰውን ዘር ኹሉ፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፥ በልጄና በወዳጄ፥ በሕይወቴና በፍቅሬ፡ በቸሩ ፈጣሪ ዘንድ፡ ራሴን የምወክለው እኔ ነኝ፡ እንግዴህ ወዲህ የምናገራችሁ።

"የሰው ልጆች" ከተባሉት ወገን የኾኑት፡ የያዕቆብ ልጆች አይሁድ፡ በአባታቸው፡ እግዚአብሔራዊ ስም፡ "የእስራኤል ልጆች" ተብለው እንደተጠሩ ኹሉ፡ ከዚያ፡ እጅግ ቀደም ብላችሁ፡ **"የእግዚአብሔር ልጆች"** የተባላችሁት፥ የእኔም ልጆች የኾናችሁት፡ እናንተ ወንዶችና ሴቶች፡ "ኢትዮጵያ" በሚለው፤ በእኔ፡ በእናታችሁ እግዚአብሔራዊ ስም፡ **"የኢትዮጵያ ልጆች"** ተብላችሁ እንደተጠራችሁ ታውቃላችሁ። (አሞ. ፱፥ ፯።)

ከዚህ የተነሣ፡ በተለይ፡ እውነተኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱ፡ ይህንኑ፡ የእኔን እናትነትና እናንተን የሚያጠቃልለውን፡ የእነርሱን ልጅነት በማረጋገጥ፡ ፊት፡ በብሉዩ ዘመን፡ በእየግላችሁ፡ እኔን፡ በግእዙ፡ "እምየ ጽዮን!" በጋራም፡ "እምነ ጽዮን!"፥ ኋላም፡ በሓዲሱ ዘመን፡ በእየግላችሁ፡ "እምየ ማርያም! እግዝእትየ ማርያም!"፥ በጋራም፡ "ማርያም እምነ! እግዝእትነ ማርያም!" እያላችሁ፥ በኢትዮጵያኛውም፡ በእየግላችሁ፡ "እምዬ ማርያም! እናቴ ማርያም! እመቤቴ!"፥ በጋራም፡ "እመቤታችን! እናታችን ማርያም! የቤተሰባችን እናት!" እያላችሁ የምትጠሩኝ ኾናችሁ።

አዎን! ዛሬና ከዛሬ በኋላ የምናገራችሁ፡ ይህች እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ ይህች አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ይህች ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ ይህች እመቤታችሁና ምድረ ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርሷም፡ እኔ ድንግል ማርያም ነኝ፡** ዛሬና ከዛሬ በኋላ የምናገራችሁ፥ የማናግራችሁም።

እንግዴህ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡-

<u>"እኔ"</u> ብዬ፡ ራሴን ስጠራ፡ እኔ፡ ማን መኾኔን፡ ይህ መግለጫዬ፡ በሚበቃ እንዳሳወቃችሁ ኹሉ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርሷም፡ እኔ ድንግል ማርያም ነኝ።**

<u>"እኛ"</u> ስል፡ ሙሽራው፥ እናቱና መቅደሱ ያደረገኝ እግዚአብሔርንና እኔን ማመልከቴ ነው።

<u>አምላኬና መድኃኒቴ</u> ስል፡ እግዚአብሔር አብን ማለቴ ነው።

ልጁ ወዳጁ ስል፡ እግዚአብሔር ወልድን፥ እርሱም፡ መሢሕ ኢየሱስን ማለቴ ነው።

ሕይወቴ ፍቅሬ ስል፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ማለቴ ነው።

"እናንተ" እያልሁ የማመለክተው ደግሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ የእኔም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የኾናችሁትን፡ የቅዱሱን ኪዳን ታማኞች አገልጋዮቻችንን ጨምሬ፡ መላውን የሰውን ልጆች በማጠቃለል ነው።

## "ኢትዮጵያ" የኾነችው ድንግል ማርያም፡ ለምን፡ ዛሬ፡ ራሷ መናገር አስፈለጋት?

ከዚህ ቀደም ያለውንና በቃለ ዐዋዲ የተላለፈላችሁን፡ የልጁንና የወዳጁን መልእክት፡ ሰምታችሁና ተቀብላችሁ፡ የፈጸማችሁ፥ ያልፈጸማችሁም፡ ስንቶችና እነማን እንደኾናችሁ፡ ልጁ ወዳጁ፥ እኔም፡ በመንፈስ ቅዱስ እናውቃለን። እኛ፡ ይህን ኹሉ እንደምናውቅ፡ እናንተም አትስቱትም።

ዛሬ፡ ልጁ ወዳጁ፥ እኔም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አማካይነት፡ በእየራሳችን የዐዋጅ ቃል፡ እንዲህ፡ እንድንናገራችሁ አስፈላጊ የኾነው፡ ታዲያ ለምን ይመስላችኋል? ከሕፃንነቱ ዕድሜ ጀምረን፡ እስካኹን፡ በአገልጋይ ልጃችን፡ በኤርምያስ አማካይነት፡ ከስድሳ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ ያስተላለፍንላችሁን መልእክት፡ አብዛኛዎቻችሁ ስላልሰማችሁና ስላልፈጸማችሁ እኮ ነው፤ አዎን! በዚህ ምክንያት ነው፡ ዛሬ፡ ልጁ ወዳጁ፥ እኔም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አማካይነት፡ በእየራሳችን የዐዋጅ ቃል፡ እንድንናገራችሁ አስፈላጊ የኾነው።

እርሱን፡ አገልጋያችንን ኤርምያስን፡ ሰምታችሁት፥ መልእክታችንንም ፈጽማችሁት ቢኾንማ ኖሮ፡ ይህ ኹሉ መከራና ሥቃይ፥ ጥፋትና ዕልቂት፥ ውርደትና ውድቀት፥ ውግዘትና ፍዳው ባልደረሰባችሁ ነበር። የእኛንም፡ ዛሬ፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ እናንተን እስከማናገር የሚያደርስ ኹኔታም፡ ባልተከሠተ ነበር።

በዚህ ረገድ፡ በአንድ ወገን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ቃል፡ "አንሰማም! ሰምተንም፡ አንፈጽመውም!" ብለው፡ በእምቢተኛነታቸው፡ እስከመጨረሻው የጸኑት፥ ያን እምቢተኛነታቸውንም፡ በተግባር ላይ ያዋሉት፡ ልበ ደንዳኖቹ የሰው ልጆች፡ በዚሁ አቋማቸው ምክንያት፡ ተደምስሰው የጠፉትን፡ እልፍ አእላፋት የኾኑትን፡ የሰው ወገኖች፡ እስኪ፡ ለጥቂት አፍታ አስቧቸው!

በሌላው ወገን ደግሞ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ቃል፡ "እንሰማለን! ሰምተንም፡ እንፈጽመዋለን!" ብለው፡ እውን ያደረጉትን፡ የቀደሙትን፡ ባለቃል ኪዳኖቻችንን፡ እነኖኅንና ሓይከልን፡ ከነመንትዮቻቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው፥ ከጥፋት ውኃ በኋላም፡ እነርሱን የመሰሉትን፡ እነመልከጼዴቅንና ሳሌምን፥ ሌሎቹንም ኹሉ፡ በመልካም አርአያነታቸው፡ እስኪ፡ ለጥቂት አፍታ አስቧቸው!

እንግዴህ አስተውሉ! እንደኖኅ ዘመን፡ ዛሬም፡ መዳን፡ የሚቻለው፡ በግል፥ ወይም፡ በቤተሰብ ደረጃ እንጂ፡ በማኅበር ስላልኾነ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በዚህ ነገር፡ በብርቱ አስቡበት! የማኅበሩማ ነገር፡ በመንግሥትነት ኾነ፥ ወይም፡ በድርጅት መልክ፡ በሰዎች ሕግ እየተቋቋመ፡ ለክፋቱና ለጥፋቱ ኃይል ብቻ፡ ጥሩ መሣሪያ ኾኖ እያገለገለ ሲጠቅም መቀጠሉን፡ በሃይማኖት ጽሙናና በመንፈሳዊው አትኩሮት ተመልከቱት!

ደግሞም፡ ልጄ ወዳጄና እኔ፡ በእናንተ በኲል፡ በእምቢተኛነትና በአንገተ ደንዳናነት እየቀጠለ የሚፈጸመውን የጥፋት አካኼድ እያየን፡ በትዕግሥት፡ ይህን ኹሉ የምናደርገው፡ ለምን መሰላችሁ? በእኔ እናትነት፥ በልጄ በወዳጄም ቤዛነት፥ ከእግዚአብሔር የተገኘው፥ የቅዱሱ ኪዳን፡ አንዱና የመጨረሻው የኾነው፡ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ኹልጊዜ ከፊታችን ቆሞ፡ የነጋሪነት ድምፁን፡ ያለማቋረጥ እያሰማን፡ በሕያውነት ስለሚመሰክር መኾኑን፡ ልታውቁት ይገባል።

በእናንተ በኲል፡ በዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ የቱንም ያህል፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮና የጋብቻ ምንዝርና ኃጢኣትን ብትፈጽሙ፥ ይህንኑም፡ አኹን እንደሚታየው፡ በእውነተኛው ንስሓ፡ በመመለስ ፋንታ፡ የምትቀጥሉበት ቢኾንም እንኳ፡ እየራሳችሁን፡ በራሳችሁ የምትጎዱ ከመኾናችሁ በቀር፥ በኛ በኲል፡ ስለእናንተ ደኅንነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ የታተመው የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለእናንተም፡ በነፍስ ወከፍ፡ እንደጸና ሲሠራ መኖሩን እንደሚቀጥል፡ ዛሬም፡ እኔ፡ እናታችሁ፡ እንደገና፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ሳበሥራችሁ ደስ ይለኛል።

አስተዋዮች ከኾናችሁ፡ ከእናንተ የሚጠበቀው፡ ይህን የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት ማወቅ፥ ከዚያም፡ ከቻላችሁ፡ ለየራሳችሁ ደኅንነትና ደስታ፥ ጥቅምና ሰላም ስትሉ፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ፡ እየራሳችሁን አስተካክላችሁ፡ ወደእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ መመለስ ብቻ ነው።

አዎን! ይህ ታላቅ የቸርነት ጸጋ፡ እንዲህ፡ እውን ሊኾን የቻለው፡ እንደልጄ ወዳጄ የይቅርታ ቃል፡ በቀን፡ ሰባ ጊዜ ሰባት የሚያህል ብዛት ያለው በደልና ኃጢኣት ብትፈጽሙ እንኳ፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ባበቃችሁባት አፍታ፥ እንደመልከ ጼዴቅና እንደልጄ ወዳጄ፡ ከእግዚአብሔር እና ከእኔ፡ በመንፈስ ቅዱስ የምታገኙት፡ የልጅነቱ፥ የክህነቱና የምልክናው ባለቤቶች ስለምትኾኑ፡ በዚህ ባለቤትነታችሁ፡ ለእውነተኛው ንስሓ በቅታችሁ፡ ፍጹሙን ስርየት የማግኘት ዕድላችሁ የተረጋገጠ በመኾኑ ነው።

ቀደም ብሎ፡ ልጄ ወዳጄ፥ እኔም፡ አኹን፡ ከእርሱ ለጥቄ፡ እንዲህ፡ በዐዋጅ መልክ የምናናግራችሁ፡ ከዚሁ፡ ከመጨረሻው የምሕረት ቃል ኪዳናችን የተነሣ መኾኑን፡ እንድታውቁት ያስፈልጋል።

ብዙ ጊዜያት፡ ተደጋግሞ እንደተነገራችሁ፡ እናንተ፡ "'<u>አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!</u>' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኰሎ ይመልክ ስሙ።

"ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ተብሎ በብሉያቱ ነቢያት፡ የተናገረላቸውና በመለኮት ቃል፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" የተባሉት፡ የእነዚያ፡ ታማኞች ልጆቼ ልጆች ናችሁ፤

ይልቁንም፤ የሓዲሱ የምሕረት ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ዘውድ በኾነው ልጄ ወዳጄም፡ "ወልድየ! አንተሰ፡ ዘልፈ ሀለውከ ምስሌየ፤ ወኵሉ ዘዚአየ፡ ዚአከ ውእቱ። ወባሕቱ፡ ርቱዕሰ ንትፈሣሕ! እስመ ዝንቱ እኁከ፡ ሞተ፡ ወሓይወ፤ ተሓጒለ፡ ወተረክበ።

"ልጄ ሆይ! አንተ ኹልጊዜ፡ ከእኔ ጋር ነህ፤ ለእኔም የኾነው ኹሉ፡ የአንተ ነው። ዳሩ ግን፡ ይህ ታናሽ ወንድምህ፡ ሞቶ ነበር፤ አኹን፡ ሕያው ስለኾነ፥ ጠፍቶም ነበረ፤ አኹን ግን ስለተገኘ፡ ደስ እንዲለን፥ ፍሥሓም እንድናደርግ ይገባናል!" ተብሎ፡ በምሳሌ የተነገረለት፡ የመሓሪው አባታችሁ፡ የእግዚአብሔር፡ ትልቁ የበኵር ልጁ፡ ልጆች ናችሁ፤

እንዲህ ስትኾኑ፡ ነገር ግን፡ ምሳሌያቸው እንደኾነው፡ እንደታናሹ አጥፊ ልጅ፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ እስከመጨረሻው፥ እስከዛሬም እንኳ፡ በንስሓ ሊመለሱ እንዳልቻሉት፡ ራሳቸውን፡ "እስራኤል" ብለው እንደሚጠሩት፡ እንደአይሁድ፡ እየራሳችሁን፡ እንደእነርሱ አድርጋችሁ፡ በአንገተ ደንዳናነትና በግብዙ እምቢተኝነት ጸንታችሁ በመቀጠላችሁ፡ ይህ ኹኔታችሁ፡ እንኳንስ፡ በእኛ ዘንድ ይቅርና፡ አስተዋይ ለኾነ፡ ለማንኛውም መልአካዊና ሰብአዊ ፍጡር፡ የሚያስገርምና የሚያሳዝን ኾኗል።

የአምልኮ አመንዝራነት ምልክት በኾኑት፡ በጊዜና በሥልጣን፣ በገንዘብና በቦታ ኹኔታዎች መለዋወጥ ምክንያት፡ እንደሌሎቹ ዓለማውያንና ሥጋውያን ሕዝቦች፡ ከፈጣሪያችሁና ከእኔ ያገኛችሁትን፥ የቀደሙትም ወላጆቻችሁ ጠብቀውና አክብረው ያቆይዋችሁን፥ ያስረከቧችሁንም ሃይማኖታችሁንና ምግባራችሁን፥ ሥርዓታችሁንና ሕይወታችሁን፡ እንዲህ፡ በቀላሉና በወረት የምትለዋውጡ ከኾነ፡ የእኔ ልጆች የሚያሰኛችሁ፥ ወይም፡ ለዚህ ልጅነት የሚያበቃችሁ፡ ያ፡ ኢትዮጵያዊነታችሁ የት አለ?

ከዚህ ክፉ ግብራችሁ የተነሣ፡"ይዌልጥኑ ኢትዮጵያዊ፡ ማእሶ፥ ወነምርኒ፡ ኀበሪሁ!?

"በውኑ ኢትዮጵያዊ፡ መልኩን፥ ነብርም፡ ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን!" ተብሎ፡ በኢትዮጵያዊው ነቢየ እግዚአብሔር፡ በኤርምያስ በተነገረው ኃይለ ቃል መሠረት፡ ይህንኑ ኢትዮጵያዊነታችሁን አጥጣችሁት፥ ቅዱስ ኪዳናዊ ጸጋውንም፡ ተገፈፋችሁት አይደለምን? መቼም፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ መለኮታዊዋ እውነት ስለኾነ፡ ወደሰይጣናዊው ሓሰት ሊለወጥ፥ ወይም ሊሻር አይቻልም።

የእኔ፡ የኢትዮጵያ፡ እውነተኞች ልጆቼ የኾኑትን ሰብኣውያን ወገኖች፡ ከፈጣሪዬ ጋር፡ ከእኔ የበለጠ የሚያውቃቸው የለም። እንኳንስ ለእኛ ይቅርና፡ ለሰው የገቡትን ቃላቸውን፡ በታማኝነት፡ እስከመጨረሻው አጽንተው የሚጠብቁ፥ የሚፈጽሙም ናቸው። እንዲህ ያለው፡ በዛሬው ትውልድ ላይ የሚታየው መለዋወጥ፥ ወይም፡ ወረተኝነት፡ ከቶ ታይቶባቸውም፥ ተሰምቶባቸውም አይታወቅም። ነቢዩም፡ ያን ቃል፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ኾኖ የተናገረው፡ ስለዚሁ እውነት መኾኑ፡ ለማንም ግልጽ ነው። (ማቴ. ፲፰፥ ፲፩-፳፪። አሞ. ፱፥ ፯። ሉቃ. ፲፩፥ ፲፭-፴፪። ኤር. ፲፫፥ ፳፫።)

## ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ራሷ፡ ድንግል ማርያም ስለመኾኗ።

ከፍጥረት ጀምሮ፡ በመንፈሳዊው ህልውናዋ ረቅቃና በሥጋዊው አካልዋ ገዝፋ፡ በዘለዓለማዊው ሕያውነቷም ጸንታ ያለችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** በክፋቱና በኃጢአቱ ምክንያት፡ ለሞት በተዳረገው፡ በምድር ላይ በሚኖረው፡ በሰው ዘንድ በሙሉ፥ እየራሳቸውን፡ "ቤተ ክህነት"፥ ወይም፡ "ቤተ ክርስቲያን" ብለው በሚጠሩት፡ የሃይማኖት ድርጅቶች ዘንድ ሳይቀር፡ ተሠውራ ከኖረች በኋላ፡ ባለፈው፡ በ፳፻፩ ዓመተ ምሕረት፥ በትንሣኤዬ በዓለ ዕለት በወጣው ዐዋጃችን፡ ራሷን ስለገለጠች፡ እንደቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን፡ እርሷን፡ በሃይማኖት ለሚቀበላትም ኾነ፡ ለማይቀበላት ኹሉ፡ ቃሏን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በእኔ አንደበት ማሰማቷን ትቀጥላለች።

የምድራዊዉና የሰማያዊው ፍጥረታተ ዓለማት ሠሪና ባለቤት የኾነችውን፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ እንደእስካኹኑ ጊዜ ኹሉ፡ እንግዴህ ወዲህም፡ በቀጥታና በገሃድ፡ በአባትነትና በእናትነት፥ በሊቀ ካህናትነትና በመንበረ ጸባኦትነት፥ በንጉሥነትና በንግሥትነት፡ የምንጠብቃትና የምንንከባከባት፡ የምንመራትና የምናስተዳድራት፥ ልጇ ወዳጇና እኔ መኾናችን፡ በገሃድ እንዲታወቅ ይኹን!

ስለዚህ፡ "ማርያም"፥ ወይም፡ "ንግሥት"፥ ወይም፡ የይሁዳ አንበሳ"፥ ወይም፡ "ቴዎድሮስ"፥ ወይም፡ "ኤልያስ" ወይም፡ ሌላ፡ የተለያየ ስያሜን በመስጠት፡ "ንጉሥ፥ ንግሥት፥ መሪ፥ ርእሰ ብሔር፥ ወይም የሕዝብ አለቃ ተነሥቷል/ተነሥታለች፥ መጥቷል/መጥታለች!" ወይም፡ "ወደፊት ይነሣል/ትነሣለች፥ ይመጣል/ትመጣለች!" እያላችሁ ልጆቼን፥ ሕዝቤን የምታውኩና የምታዋክቡ ብትኖሩ፡ ይህን ጎጂና ሓሳዊ ዓላማችሁንና ተግባራችሁን፡ ደግሜ፥ ደጋግሜ ተዉ እላችኋለሁ።

ከዚህ በቀደመው፡ በመጀመሪያው ዐዋጃችን፡ ለሥጋዊው ፍጥረተ ዓለም ሳይቀር በተገለጠችው፥ በእርሱም ላይ ፈጽማ መስፈኗን እንዲያውቅ በተደረገችው፡ በዚችው፡ በእኔው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለመኖር፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከፈለገና ከመረጠ፡ የመጨረሻውን መልካሙን የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት እንዲቀዳጅ ስላደረግንለት፡ በዚሁ ፍጹም ዕድል ከመጠቀም በቀር፡ ለጋሡ ፈጣሪ፡ ለፍጥረቱ፡ በእኔና በልጄ በወዳጄ አማካይነት፡ ካደረገው የቸርነት ሥራውና ከሰጠው የተትረፈረፈ የምሕረት ጸጋው የበለጠ፥ ሌላ የቀረና የሚጨመር፥ የሚጠበቅም፡ እንግዴህ ወዲህ፡ አንዳችም ነገር እንደሌለ፡ በዚሁ፡ አገልጋያችን አማካይነት፡ በሚበቃ ተነግሮአል።

ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ከፍጥረት ወዲህ፡ እንዲህ፡ በእኔ እንድትጠራና እንድትመራ፥ የልጄ የወዳጄ፥ የአባቱና የሕይወታችን የመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ ኾነ እንጂ፡ እርሷማ፡ ከፍጥረት በፊትም የነበረች መኾኗ፥ ንጉሧም፡ እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር መኾኑ፥ ንግሥቲቱም እኔ መኾኔ፡ እሙን ነው። ይህም፡ **"እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም! ...ወትቀውም ንግሥት በየማንከ።**

**እግዚአብሔርማ፡ ከፍጥረተ ዓለሙ አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው!...ንግሥትም፡ በቀኝህ ትቆማለች።"** በሚለው፡ በነቢያት ቃል፡ ይታወቃል። ንጉሥነቱም፡ በተለይ፡ አምነው በተቀበሉት፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ላይ መኾኑን፡ ከዚሁ፡ ከእግዚአብሔሩ ቃል ቀጥሎ፡ **"ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ!**

**"ለሕይወታቸው የሚያፈልጋቸውንም ኹሉ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች ሰጠሃቸው!** የሚለው የተያያዘው ቃል፡ ይህን እውነታ ያረጋግጠዋል። (መዝ. ፸፫፥ ፲፪-፲፬።)

በተለይ፡ በዚህ፡ በአዲስ ኪዳኑ የምሕረት ዘመን፡ በፍጥረተ ዓለሙ ላይ ሰፍና፡ የምትመራውና የምታስተዳድረዋ፡ ይህችው፡ በእኔ ስምና አገርነት፥ እናትነትና ንግሥትነት ጸንታ የቀጠለችው፥ ወደፊትም፡ የምትቀጥለው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗ**፡ ሊታበል የማይቻል፡ ሌላው የእግዚአብሔር እውነት ነው። ልጄ ወዳጄ፡ በዚህ ረገድ፡ "ንግሥተ ዓዜብ" ያላት፡ "ኢትዮጵያ" የኾንሁት፡ እኔ እናቱ መኾኔን በማመልከት የተናገረው፥ ለዚህ፡ ለአኹኑ ጊዜም የሚጸናው ቃሉ፡ ለዚህ፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ በቂ ምስክር ኾኖ ይጠቀሳል።

ይህም፡ **"ንግሥተ ዓዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሖ፣ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፣ ትስማእ ጥበቢሁ ለሰሎሞን። ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን ሀሎ ዝየ።**

**"ንግሥተ ዓዜብ፡ በፍርድ ቀን፡ በዚህ ትውልድ ላይ ተነሥታ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና።** እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።" የሚለው መለኮታዊ ቃሉ ነው።(ማቴ. ፲፪፥ ፵፪።)

## ትውልዱ፡ በድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያ ላይ ለፈጸመው ክህደት፡ በራሱ ላይ፡ ራሱ ያመጣው፡ የአርባ ዓመት መራራ ቅጣት።

ከዛሬ አርባ ዓመታት በፊት፡ በስሜ በተጠራችው አገር የምትኖሩት ልጆቼ፡ ከልጄ ከወዳጄና ከእኔ ያለማቋረጥ ሲሰጣችሁ የኖረውን ምክርና ማስጠንቀቂያ፡ በንቀት ባለመቀበል፡ ልጄ ወዳጄንም፥ እኔንም፡ ሳትፈሩና ሳታፍሩ፡ በእኛና በእናንተ መካከል ጸንቶና ተጠብቆ የኖረውን ቅዱሱን ኪዳን፡ በይፋ አፈረሳችሁ።

በዚህ የድፍረት አድራጎታችሁ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ፡ በሥውርና በገሃድ፥ በጨለማና በብርሃን፡ ስታካኺዱ የኖራችሁት፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮና የጋብቻ አመንዝራነት ኃጢአታችሁ፥ ሌላውም፡ እጅግ የበዛው የተጠራቀመ ክፋታችሁ፡ ከልጄ ከወዳጄም፥ ከእኔም ትዕግሥት ያለፈ ኾኖ፡ የበደልና የግፍ ጽዋችሁ ተትረፍርፎ መፍሰሱ፡ በገሃድ ተረጋግጦ ታወቀ።

ከዚህ የተነሣ፡ ይህ፡ የገዛ ክፉ ምርጫችሁና የጥፋት ውሳኔያችሁ ባመጣው፡ "ደርግ" በተባለው፡ ቀጪና ቀሣፊ ኃይል እጅ ወደቃችሁ።

ታዲያ! ይህን እውነታ የምታውቁና የምታምኑ፡ ስንቶች ናችሁ? በዚያን ጊዜ፡ ከቅዱሱ ኪዳን፡ የምሕረት ጸጋ የተነሣ፡ ረድኤቴና ጥበቃዬ አልተለያችሁም ነበር።

እጅግ ብዙ የቸርነት ትሩፋት፡ ከእኛ የተደረገለት፡ የዘመኑ ሥዩመ እግዚአብሔራችን የነበረው ኃይለ ሥላሴ፡ እርሱም፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ፡ የተቀባበትን፡ ቅዱሱን ኪዳን በማፍረስ፡ የዚሁ አገራዊ ታላቅ ኃጢኣት፡ ወጣኝና የባዕዳኑ ተባባሪ፥ መሪና አስፈጻሚም ኾኖ ተገኘ። ይህን፡ የጥፋት አካኼዱንም፡ በንስሓ፡ ወደቀናውና ወደእውነተኛው እግዚአብሔራዊ ፈለግ እንዲመልስ፡ ምክራችንና ማስጠንቀቂያችን፥ ተግሣፃችንም፡ በተደጋጋሚ ቀርቦለት፡ እንደእናንተ፡ እንዳኹኑ ትውልድ ኹሉ፡ ሊፈጽመው ቀርቶ፡ ሊሰማውና ሊቀበለው እንኳ፡ ፈቃደኛ ሳይኾን ቀረ። ከዚህ የተነሣ፡ በእርሱና የእርሱ በኾኑት፥ በሥራዎቹም ኹሉ ላይ የደረሰውን፡ የመጨረሻ ውርደትና ውድቀት፥ ዕልቂትና ፍልሰት፡ እናንተና ፍጥረተ ዓለሙ በሙሉ፤ በከፍተኛ ድንጋጤ፡ በግልጽ አይታችሁታል።

የእርሱ ፍጻሜ፡ በዚህ ሲያበቃ፡ እርሱ፡ ኰትኵቶና አንከባክቦ ያሳደገውና ያዘጋጀው ትውልድ ደግሞ፡ ዕድሉ፡ ከእርሱ የከፋና የተራዘመ መራራ ኾኖ፡ ይኸው ቀጥሏል። አጼያዊ ሥዩማችን፡ ኃይለ ሥላሴ፡ የዘመኑን ትውልዱ ለጋ አባሎች፡ "የእኔ የኢትዮጵያ ልጆች" ለሚያሰኛቸው ኢትዮጵያዊነታቸው የሚያበቃቸው፡ ነፍሳዊውና መንፈሳዊው እውቀት፡ ከሥጋዊው ጋር ተጣምሮና ተቀናጅቶ እንዲሰጣቸው ማድረግ ሲቻለውና ሲገባው፡ ያ ቀርቶ፡ በባዕዳኑ ምክርና መመሪያ፡ የእነርሱን ሥጋዊ ሙያና የፍልስፍና ትምህርት ብቻ በመከተል፥ አዎን! በዚያ ብቻ ሠልጥነው እንዲያድጉ በመምረጡ፡ ትውልዱ፡ ምን ኾነ? ፍሬ ቢስና እንክርዳድ ኾኖ ተገኘ።

ይህ ኹሉ ኾኖ፡ ይኸው ትውልድ፡ ራሱ፡ በእንቢተኝነቱ ካመጣው፡ የውድቀቱ ጥፋት፥ ከዚህ የተነሣም፡ ከሚጠብቀው የቅጣት ዋጋው ለመዳን የሚያስችለውን፡ የመጨረሻውን ዕድል እንዲያገኝ አደረግን፤ ይኸውም፡ ለዚህ የቸርነት በረከታችን አቀራረብና አፈጻጸም፡ መጋቢ ይኾን ዘንድ፡ ከልጅነቱ ጀምሮ፡ በክህነት ሓዋርያነት መርጠን ያስነሣነው፡ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ በሦስቱም፡ የመንግሥታችን፡ የአገልግሎት ቤቶች አማካይነት፡ መልእክታችንን ሲያደርስላችሁ መቆየቱ ነው።

እርሱንም፡ በኃይለ ሥላሴ፡ የአጼነት ዘመን ፍጻሜ ግድም፡ ለእኔ፡ ለኢትዮጵያ ማንነቴ፥ ለእናንተም፡ ለእግዚአብሔርና ለኢትዮጵያ ልጅነታችሁ፥ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁና ለእግዚአብሔር መንግሥትነታችሁም፡ ሕያው ማእከል ለኾነችው፡ ለርእሰ አድባራት አክሱም ጽዮን ንቡረ እድነት አበቃነው፤ በማስከተልም፡ የሥርዓተ መንግሥታችን ባለአደራ የኾነው፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ፡ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ እንዲኾን ሠየምነው፤ በዚያ የአገልግሎት ኃላፊነትና ሥልጣን ላይ ሣለ ነው፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና በእርሱ፡ በአገልጋያችን መሣሪያነት፥ በቃለ-ዐዋዲ ተቋቁሞና ተደራጅቶ በሚሠራ "ሰበካ ጉባኤ" አማካይነት፡ ይኸው ሥርዓተ መንግሥታችን፡ በመላው ምድራችንና ሕዝባችን ዘንድ፡ እውን እንዲኾንና በገሃድ ታውቆ እንዲሠራበት ያስቻልነው።

ይኹን እንጂ፡ የመጨረሻው ሥዩማችን ለኾነው፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴና በዘመኑ ለነበረው ትውልድ የቀረበለት፡ ያ ኹሉ የቸርነት ዕድል፥ የተበረከተለትም፡ ያ ኹሉ የልግሥና ጸጋ፡ ከኢምንት ሳይቈጠር፡ ትውልዱ፡ ባዋቂነቱም ኾነ ባላዋቂነቱ ተመክቶ፡ ፀረ እግዚአብሔርና ፀረ ኢትዮጵያ የኾነውን፡ የባዕዳኑን ፍልስፍና በመከተል፡ የራሱን ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት አቋቋመ። በእነዚህም ተቋማት አማካይነት፡ የራሱን ምርጫ አደረገ። የምርጫ ውሳኔውን፡ በተግባር ላይ ዐዋለ። ያም፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ግልጽ የኾነ፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የጋብቻና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢኣትን መፈጸም ነበር።

ከዚህ ከባድ ጥፋቱና ታላቅ ኃጢኣቱም፡ በንስሓ ላለመመለስ ላሳየው ጽኑ የእምቢተኛነት በደል፡ ትውልዱ፡ ተገቢ የኾነውን ፍትሓዊ ዋጋን መክፈል፡ ግዴታው ኾነ። ስለዚህ፡ በትውልዱ ላይ የተላለፈውን የፍርድ ውሳኔ፡ በተግባር ላይ ሊያውል፥ አዎን! ለዚህ፡ ለትውልዱ ጥፋት፡ የተወሰነውን የቅጣት ተልእኮ ለመፈጸም፡ በመንግሥታችን ዘንድ ታውቆ የመጣውና "ደርግ" ተብሎ የተሠየመው፡ የጥፋት ኃይል፡ ስሜ በሚጠራባት፡ በሰኔ ፳፩ ቀን ተቋቋመ።

ይህን፡ በኹለት ፊት የተሳለ ሠይፍን የታጠቀውን "ደርግ" እንዲመራ የተመረጠው ሰው፡ ስሙ፡ "መንግሥቱ፡ ኃይለ ማርያም" ሲኾን፥ መኖሪያውና መሥሪያው ቤቱ ደግሞ፡ "በአታ ለማርያም" ተብላ፡ ለእኔ፡ ወደቤተ መቅደስ መግባት መታሰቢያ በኾነችው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ፡ ለደብሯ አስተዳዳሪ በተዘጋጀው ቤት መኾኑ፡ ይህ ድርጅታዊ ዕቅድ፡ ምን እውነታን ሊያመለክት፡ የተሰናዳ ይመስላችኋል?

ከዚያ በፊትና በዚያን ጊዜ፥ ከዚያ ወዲህና ዛሬም፥ ወደፊትም፡ እንኳንስ፡ በእኔ ስም በምትጠራው አገር ቀርቶ፡ በመላው ዓለምም፥ በምድርም፥ በሰማይም፡ ጸንታና ሰፍና፡ ፍጥረቱን የምትመራውና የምታስተዳድረው፥ የምትጠብቀውና የምትመግበው፡ ይህችው፡ የእኔዪቱ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን ነው።** ይህን እውነታ የሚጠራጠር፡ ከመካከላችሁ ካለ፡ ጥርጣሬውን፡ በዚህ ቃሌ፡ ሊያስወግደው ይገባል። "መንግሥቱ ኃይለ ማርያም"፡ ከነቤተሰቡ፥ የዚያ "ደርግ" አባሎች ከኾኑት ተባባሪዎቹ ጋር፡ ይኸው፡ እስከዛሬ፡ በሕይወትና በደኅንነት፥ በነጻነትና በምቾት የመኖራቸው ግህደትም፡ በቂ ማስረጃ ኾኖት፡ ይህን እውነታ ያረጋግጥለታል።

የልጄ የወዳጄና የእኔ የኾነችውን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትንማ፡ በባዕድ አምልኮ አመንዝራነታችሁ፡ እርሷን ንቃችሁና አቃልላችሁ፥ ቤተ ሕዝባችሁና ቤተ ምልክናችሁ ብቻ ሳይኾኑ፡ ቤተ ክህነታችሁ ጭምር፡ ኹላችሁም በመተባበር፡ ቅዱሱን ኪዳን አፍርሳችሁ፡ ይኸው እስካኹን፡ ክዳችኋትና ዓምፃችሁባት እየኖራችሁ አይደለምን? ማናቸውንም ዓይነት አቤቱታችሁን፡ የእኔን፡ የእናታችሁን ፈለግ በመከተል፡ እጆቻችሁን ወደእግዚአብሔር በማቅረብ ፋንታ፡ "ዲሞክራሲ" ባላችሁት፡ የባዕዳን ፍልስፍና፡ ይኸው፡ በነደደ የፍቅር ቅንዓት ተቃጥላችሁ፥ ለዚሁ ፍልስፍና፡ አበጋዞች፥ ለእናንተም፡ ጌቶቻችሁ ላደረጋችኋቸው የሰው ወገኖች፡ ያለማቋረጥ፡ በምሬትና በከንቱ እየጮሃችሁ አይደለምን?

በቤተ ሕዝባችሁም፥ በቤተ ክህነታችሁም፥ በቤተ ምልክናችሁም ውስጥ፡ እርስ በርሳችሁ እየተናከሳችሁና እየተባላችሁ፥ እየተላለቃችሁም አይደለምን? ያሳለፋችሁትን፡ የአርባ ዓመታት ዕድሜ፡ ይኸው፡ ከነመራራ ፍሬው፡ አታስተውሉትም እንጂ፡ እያያችሁት አይደለምን? ከቻላችሁ፡ አስተውላችሁ ለማየት፡ እስኪ ሞክሩ!

እየኾነ ያለው፡ ይህ፡ የእናንተ አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታ፡ የእነማንን መስሎ እንደተገኘ ታውቃላችሁ? የእስራኤል ልጆች፡ በሲና ተራራ፡ የእግዚአብሔር ካህን፥ የሙሴም አማች በነበረው፡ በኢትዮጵያዊው ዮቶር አማካይነት፡ ከእናንተ፡ ከልጆቼ ባገኟት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ የፈጸሙትን ታላቅ፡ ያላዋቂነት ስሕተትና ጠንቀኛ ጥፋት ይመስላል።

ያም ስሕተትና ጥፋት፡ እነዚያ፡ የእስራኤል ልጆች፡ ምድረ ርስታቸው ገብተው፡ ከተደላደሉ በኋላ፡ በባዕዱ አምልኮ፡ እንደገና ተማርከው፡ *"ከእኛ፡ ምንም ነገር ሳይጠይቅ፡ እንዲያው፡ ዝም ብሎ የሚመግበንንና የሚጠብቀንን፥ የሚመራንንና የሚያስተዳድረንን፡ የእግዚአብሔርን ንጉሥነት፡ በቃ! አንፈልገውም። እንደአሕዛብ፡ ቀጥቅጦ የሚገዛንን ንጉሥ አንግሥልን!"* ብለው፡ በጊዜያቸው ያስተዳድራቸው የነበረውን፡ ነቢዩን ሳሙኤልን፡ አጥብቀው ጠይቀውት፡ ፍላጎታቸው እንደተፈጸመላቸውና በዚያ ምክንያት፡ ይኸው እስከዛሬ፡ በመከራና በሥቃይ እንደሚኖሩ፡ ተረጋግጦ የታየበት ህልውናቸው ነው።

እናንተም፡ ከደርግ በኋላ፡ በዚችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ ያላችሁ ጥላቻ፡ ከቀድሞው በባሰ ኹኔታ እየተጠናከረ መኼዱን ስላየን፡ ፀረ እግዚአብሔርና ፀረ ኢትዮጵያ ለኾነው፡ ለዚሁ ባዕድ አስተሳሰባችሁና ፍላጎታችሁ፡ ተስማሚ የኾኑ፡ አለቆች፡ ለቤተ ሕዝባችሁ፥ ለቤተ ምልክናችሁና ለቤተ ክህነታችሁ ተመድበውላችሁ፡ የፍላጎታችሁ ውጤት የኾነው ዋጋችሁ፡ በእነርሱ እጅ ሲከፈላችሁ እንደቆየ አውቃችኋል።

የእነርሱም የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፡ መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን ሙሉ ሥልጣን ይዘው፡ የባዕዳኑን ዕቅድ በሥራ ላይ የሚያውሉትን፡ እነዚያን፡ የቤተ ክህነቱንና የቤተ ምልክናውን ኹለት አለቆች፡ ጳውሎስንና መለስን፡ የዓመታዊው የጊዜ ጉዞ ማብቂያ በኾነው፡ በወርኀ ነሓሴ፥ በተለይም፡ የፍልሰተ ሥጋዬ፥ የትንሣኤዬና የዕርገቴ መታሰቢያ በሚዘከርባት ሱባኤ ውስጥ፡ ድንገት፡ ወደእኛ ጠርተን እንደወሰድናቸው አይታችኋል።

በማንኛችሁም ዘንድ፡ ፈጽሞ ያልታሰበ፥ ለብዙዎችም፡ አስደንጋጭ የኾነው፡ ይህ የሞት ጥሪ፡ በስሜ ለምትጠራው ለዚች አገር፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ አማካይነት፡ የበላይ ጠባቂዋና መሪዋ፡ እኔ መኾኔን ከማረጋገጡ ጋር፡ ይህን፡ የእግዚአብሔር እውነታ ለመቀበል ፈቃደኞች ላልኾኑ ተጠራጣሪዎች፡ ማሳመኛ ምስክር ሊኾናቸው ችሏል።

በእነርሱ ቦታ የተተኩት የዛሬዎቹ አለቆችም፡ አኹንም፡ የእናንተው ፍላጎትና ምርጫ ያስገኛቸው በመኾናቸው፡ አገልግሎታቸው፡ ያው፡ እንደቀድሞዎቹ ቢኾንም፡ በተለይ፡ ለቤተ ምልክናው እልቅና የተመደበው ሰው፡ ስሙ፡ "ኃይለ ማርያም ደሳለኝ" የመኾኑ ነገር፡ እኔን በሚመለከት፡ የቀደመውን፡ የደርግን ርእሰ ብሔር ስም አንሥተን ለተነጋገርበት ርእሰ ጉዳይ፡ አንዳች ምሥጢራዊ መልእክት እንዳለው ያመለክታችኋል።

አትርሱ! እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ ረቂቁን የሰማያት ኾነ፡ ግዙፉን የምድር ዓለማት ሲፈጥር፡ ይኸው ፍጥረቱ እንዲመራበትና እንዲተዳደርበት፥ እንዲጠበቅበትና እንዲኖርበት፡ ቋሚ አድርጎ የሠራው ሥርዓት መኖሩን አትርሱ!

ያም ሥርዓት፡ በተለይ፡ እርሱን አስመስሎ፡ በመልኩ ለፈጠራችሁ፥ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾኑ!" ብሎም፡ የመጨረሻውን የልዕልና ማዕርግ ላጎናጸፋችሁ፡ ለእናንተ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ፡ የለገሠውን ጸጋዎች ያጠቃልላል።

ከእነዚህ ጸጋዎች መካከል፡ እውነቱንና ሓሰቱን፥ ደጉንና ክፉውን፥ ቀናውንና ጠማማውን፥ ጠቃሚውንና ጎጂውን፥ ዐልሚውንና አጥፊውን፥ በመጨረሻም፡ አዳኙንና ገዳዩን፡ ለይታችሁ የምታውቁበት፡ ነፍሳዊውና ሥጋዊው፥ መንፈሳዊዉም አእምሮ ቀዳሚው ኾኖ ይገኛል።

ከዚያ ጸጋም ጋር፡ አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ በሰጣችሁ፡ በፍላጎት መብታችሁና በመምረጥ ነጻነታችሁ፥ በመወሰን ሥልጣናችሁና በማድረግ ኃይላችሁም ህልውና ውስጥ፡ ጣልቃ የማይገባ ኾኖ፡ የፈለጋችሁትን ከመፈጸም፡ መከልከሉ ቀርቶ፡ ማገዱ እንኳ፡ በእርሱ ዘንድ፡ ሊደረግ የማይታሰብ የመኾኑ እውነታ ነው።

ደግሞ አትርሱ! ከጥንት ጀምሮ፡ በዓለም፡ ያሉ ሃይማኖቶች በሙሉ፡ አረማዊውና ጣዖት አምላኪው፥ ይሁዲውና እስላሙ፥ ክርስቲያኑና እምነተ ቢሱ፡ ኹሉም፡ በየሚኖሩበት አገር፡ የራሳቸው ወገኖች ሲያሳድዷቸውና ሲያስጨንቋቸው፡ የሚያስተማምን መጠጊያ ያገኙት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ብቻ መኾኑንም አትርሱ!

ከጥንት ጀምሮ፡ በኃይል ሳይኾን በሰላም፥ በጥላቻ ሳይኾን፡ በፍቅር፥ በጭቆና ሳይኾን በፍጹም ነጻነት፥ መልካሙን መስተንግዶ አግኝተው፡ የተድላ ደስታና የዕረፍት ኑሮአቸውን፡ በእዚያው ለመቀጠል፥ ወይም፡ ወደአገራቸው ለመመለስ ቢፈልጉ፡ መልካም አሸኛኘት ተደርጎላቸው የሚሰነባበቱባት አገርና ሕዝብ፡ በምድር ላይ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ መኾኗንም አትርሱ!

አኹንም፡ አትርሱ! ይህ ኹሉ እንዲኾን፡ በእኛ ዘንድ የታወቀና የተፈቀደ ቢኾንም፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ሕያዋን ፍጡሮቿን፤ "እምቢ!" ብለው፡ በእየራሳቸው ላይ፡ ጥፋትን ወደሚያመጣው የክፋት አበጋዝ፡ በገዛ ፈቃዳቸውና ውሳኔያቸው ካልገቡ በቀር፡ መላውን ፍጥረት ጭምር፡ ትጠብቃለች፥ ታድናለችም እንጂ፡ ማንኛውንም ፍጡሯን፡ ለአጥፊውና ለጥፋቱ፥ ለክፋቱም ወገን፡ ፈጽማ አሳልፋ አትሰጥም።

ያ ባይኾን ኖሮ፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያዊት" የምትሉ፡ ዛሬ፡ በአገር ቤትም ኾነ፡ በመላው ዓለም ተበትናችሁ፡ በሕይወተ ሥጋ የምትንቀሳቀሱት ኹሉ፡ ከዚያ፡ ለጭካኔ ብቻ ከተመዘዘው የደርግ ሠይፍ፥ ከዚያ የተነሣም፡ ለእሥራት፥ ለስደትና ለልዩ ልዩ ሥቃይ ከተዳረጋችሁበት የመከራ ዓይነት ማምለጥ ባልቻላችሁ ነበር።

## ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡
## ስለራሷ ምንነትና ማንነት ስትናገር።

በዚህ ረገድ፡ እውነቱን አውቆ ለማመን ለሚፈልግ፡ ለማንም ተርታ ሰውም ቢኾን፡ በተለይ፡ <u>እኔን፤ ምንነቴንና ማንነቴን ስለሚመለከተው የእግዚአብሔር እውነታ፡ ለመረዳትና ለመገንዘብ፡</u> አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ጥበቡ፡ በዚያ ሰብአዊ ፍጡር ውስጥ ያሳደረው፡ የእውቀት ጸጋውና በሥነ ፍጥረቱ አማካይነት እያስተላለፈ ያለው፡ የማያቋርጥ መልእክቱ፡ በበቃ ነበር።

በቀደሙት ቅዱሳኑና ቅዱሳቱ ነቢያት አንደበት የተናገረው፥ በእጃቸውም ያስጻፈው ቃሉ፡ በበቃ ነበር።

በተለይም፡ ልጇ ወዳጇ፡ በእኔ የድንግልና ማሕፀን የመፀነሱን ምሥራች ባበሠረውና የእግዚአብሔር ባለሟል በኾነው፡ በገብርኤል፥ ከዚያም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በእኔና በእኅቱ፡ በኤልሣቤጥ፥ ገና በማኅፀኗ በነበረው፡ በመጥምቁ ዮሓንስም ሳይቀር ዐድሮ፥ ደግሞም፡ በወላጆቼ፡ በኢያቄምና በሓና፥ ኋላም፡ ለልጇና ለእኔ፡ ሰብኣዊ ጠባቂ ኾኖ ባገለገለን፡ በጻድቁ ዮሴፍ፥ በመጨረሻም፡ ልጇ ወዳጇ፡ ከእኔ፡ በበረት በተወለደበት ዕለት፡ በሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት ወገኖች በኾኑ እረኞች ዘንድ፡ ስለእኔ የገለጸው ምሥጢር ታውቆ፡ በእነርሱ የተነገረው ምስክርነት፡ በበቃ ነበር።

ከዚያም፡ እየቀጠለ በኼደውና መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው፡ በባለምሥራቾቹ ዜናውያን ሓዋርያት፡ በማቴዎስና በማርቆስ፥ በይበልጥም፡ በሉቃስና ካጠገቤ ባልተለየው፡ በዮሓንስ ወልደ ነጐድጓድ፡ በራእዩ ሳይቀር፥ በቅዱሳኑና ቅዱሳቱ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ በስፋትና በምልዓት፥ በምጥቀትና በጥልቀት የተነገራችሁና የተጻፈላችሁ፡ በበቃ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ በማያቋርጠውና በሚያጥለቀልቀው፡ የጸጋ ማዕበሉ እየቃኘ፡ በፍጹሙ እውቀት ያሰጠማቸውና የመሰጣቸው፡ ያሬድና ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፥ ኤፍሬምና ሕርያቆስ፥ ክርስቶስ ሠምራና ገላነሽ፣ እነርሱን የመሰሉት፡ ነጋሥያንና ነጋሥያት ልጆቼና ካህናት አገልጋዮቼ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ስለእኔ ምንነትና ማንነት፡ በቃልና በድርሰት፥ በንባብና በዜማ፥ በቅኔና በግጥም፥ በማኅሌትና በዘፈን፡ ቀድሞም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፡ በየአፍታው ሲያፈልቁና ሲያሰሙ የኖሩት፥ እየኖሩ ያሉትና የሚኖሩት ምሥጢራዊ ቍም ነገር፡ በበቃ ነበር።

በመጨረሻም፡ ስለእግዚአብሔር እውነትና ስለመንግሥቱ አገልግሎት፡ የአምላኬና የመድኃኒቴ የእግዚአብሔር አብ፡ የአባትነትና የእኔ፡ የእናትነት ጥሪያችን የተላለፈው፡ ለኹላችሁ ሲኾን፥ እናንተም ኹላችሁ፡ እኩል ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህኖቻችን ስትኾኑ፡ በዚህ ምንነቱና ማንነቱ፡ ይህን ጥሪያችንን ተቀብሎ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ስም፡ በመካከላችሁ፡ የልጇ የወዳጇና የእኔ ካህን ልጃችን በመኾን፡ የሚያገለግለንና የሚያገለግላችሁ ኤርምያስ፡ ስለእኔ እውነተኛ ምንነትና ማንነት፡ በቃል ያብራራውና በጽሕፈት ያስተላለፈው፥ በመጻሕፍትም የዘገበው ዝርዝር ሓተታ፡ በበቃችሁ ነበር።

ነገር ግን፡ አልኾነም። ያ፡ ልጇ ወዳጇ፡ በሰውነት ተገልጦ፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ፡ ይነግራቸውና ያስተምራቸው የነበሩት አይሁድ፡ እንዳልሰሙትና እንዳልተቀበሉት፥ እንዲያውም፡ ተቃውመውት፡ በክፉ ቅንዓትና ጥላቻ፡ ለአረማውያን ገዢዎቻቸው፡ አሳልፈው ሰጥተውት፡ ለመስቀሉ መሥዋዕትነት እንዳበቁት ኹሉ፡ ዛሬም፡ ይህ ትውልድ፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የምትሉትን፡ አብዛኛዎቻችሁን ጨምሮ፡ ሲያደርግ የሚታየው ኹኔታ፡ ልክ ያንን እየመሰለ በመኼድ ላይ ይገኛል።

በዚህም፡ ልጇ ወዳጇ፡ "ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፡ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው!

"በኖኅ ዘመን እንደኾነው ኹሉ፡ የማርያም ልጅ በሚመጣበት ጊዜ፡ እንዲሁ ይኾናል!" ያለው፡ መለኮታዊው የትስብእት ቃሉ ደርሶ፡ እየተፈጸመ ያለበት፡ የመጨረሻው ጊዜ መኾኑ፡ በእርግጥ ይታወቃል። (ማቴ. ፳፬፥ ፴፯።)

እንዲህማ ባይኾን ኖሮ፡ ቀደም ብዬ ባወሳኋቸው፡ በእነዚያ ኹሉ መንገዶች፥ ይልቁንም፡ በእኛ በኩል፡ ምንጊዜም የማይጓደለውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ድርሻችን የኾነውን የቸርነት ሥራችንን በመቀጠል፡ የዛሬው ትውልድ የኾናችሁትን፡ እናንተን፡ ኹላችሁንም፡ ወደንስሓ ለመመለስ፥ እንደኖኅ ቤተሰብ፡ ከማይቀረው የጥፋት ነበልባል ለማዳንም ስንል፡ ይህንኑ፡ አገልጋይ ልጃችንን፡ ኤርምያስን፡ ከመካከላችሁ መርጠንና አስነሥተን፡ ለምን እንልከው ነበር? በእርሱ አማካይነት ያስተላለፍነውን መልእክታችንን፡ ከጥቂቶቻችሁ በቀር፡ አብዛኛዎቻችሁ፡ ሰምታችሁና ተቀብላችሁ፥ ፈጸማችሁትም ቢኾንማ ኖሮ፡ ቀደም ብሎ፡ ልጇ ወዳጇ፡ በመጀመሪያው ዐዋጅ፥ ዛሬም፡ እኔ፡ በዚህ ዐዋጅ፡ መናገር ባላስፈለገን ነበር።

## አ. በማናቸውም መሥፈርት፡ ማን ይበልጣል፡ ከልጅ እና ከእናት?

ከኹሉ አስቀድሞ፡ እስኪ፡ በሰውኛ የኾነውንና እየኾነ ያለውን፤ ወደፊትም፡ በመኾን የሚቀጥለውን፥ ማንኛችሁም፡ በቀላሉ ልትመልሱት የምትችሉትን፡ አንድ ተራ ጥያቄን ላቅርብላችሁ፤ እርሱም፡ "ከእናትና ከልጅ፡ የሚበልጠው፡ ማንኛው ነው?" የሚል ነው፤ የዚህን ጥያቄ መልስ፡ እያንዳንዳችሁና ኹላችሁም፡ ቀደም አድርጋችሁ፡ ያወቃችሁትና አኹንም፡ ወዲያው፡ በውስጣችሁ፡ በለኖሳስ የሰጣችሁት ስለኾነ፡ ከአንደበታችሁ ልሰማው አልጠብቅም፤ አያስፈልገኝምም።

አዎን! የወለደችው ልጇ፡ ሴት ትኹን ወንድ፡ አኹንም ኾነ ወደፊት፡ እርሱ/እርሷ፡ ምንም ምን ይኹኑ፡ ከእርሱ/ከእርሷ ይልቅ የምትበልጠው፡ እናቲቱ መኾኗን ማስተባበል የሚቻለው፡ ማንም ፍጡር የለም። በፈጣሪም ኾነ፡ በፍጡር ዘንድ፥ በተፈጥሮም ኾነ በሃይማኖት፥ በሰዎች ልማድም ኾነ፡ በሕጋቸው የሚጸድቀው፥ ትክክለኛው መልስ፡ በእርግጥ፡ ይኸው ብቻ ነው።

ይህ ለመኾኑም፡ ልጇ ወዳጇ፡ ቀድሞ፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል ላይ፡ ስለእርሱና ስለእኔ ምንነትና ማንነት፡ ተአምራቱንና እውነቱን ገልጦ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በይፋ በማሳወቅ፡ በዚያ አደባባይ፡ ከአንደበቱ በወጣው ቃሉ፥ በመለኮታዊ ግብሩም በፈጸመው ድንቅ ተአምር፡ በእርሱ ዘንድ፡ ለእኔ፡ በእናትነቴ፡ በእርሱ፡ በልጇ ላይ የተሰጠኝ ሥልጣን፡ ያልተገደበ መኾኑን፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ በግልጽ አመላክቷችኋል።

ዛሬም ቢኾን፡ ልጄ ወዳጄ፡ ከዚህ አስቀድሞ፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ፈቃዱ ኾኖ፡ ባሰማው የዐዋጅ ቃሉ፡ ስለእኔ በሚበቃ ስለተናገረ፡ እርሱም፥ በቃና ዘገሊላ የነበሩት አገልጋዮችም፡ ትእዛዜን ተቀብለውና መመሪያዬን ተከትለው፡ ፈቃዴን እንደፈጸሙ ኹሉ፥ በመፈጸማቸውም፡ እንደተጠቀሙ ኹሉ፡ እናንተም፡ ኹላችሁ፡ መልካም የኾነውን ቃሌን ሰምታችሁ፡ ፈቃዴን ለመፈጸም፡ የተዘጋጃችሁ ትኾኑ ዘንድ፡ በእውነተኛው የእናትነት ቃሌ አሳስባችኋለሁ፤ አደራም፡ እላችኋለሁ።

በዚያ፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት የታየው ተአምር፡ በቀጥታ፡ ሰው የኾንሁትን፡ የእኔን፡ የእናቱን ማንነትና ክብር፥ ሥልጣንና የበላይነት ለመግለጥ፡ ልጄ ወዳጄ፡ በእግዚአብሔርነቱ አረጋግጦ ሊመሰክር፡ ያዘጋጀው መድረክ መኾኑ፡ በተአምራዊው የድርጊት ውጤት፡ በገሃድ ተከሥቷል። ይኸውም፡ በሠርጉ በዓል ላይ እንዲገኙ ለተጋበዙትና ለታደሙት ኹሉ፡ "ይበቃል!" ተብሎ የተጠመቀው የድግሥ ጠጅ ማለቁን፡ ልጄ ወዳጄ፡ በአምላክነት ባሕርዩ እያወቀ፡ ለምን፡ ዝም አለ? እኔ እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ **"ወይንኬ አልቦሙ!**

**"ጠጅ እኮ አለቀባቸው!"** ብዬ፡ እስክጠይቀውስ ድረስ፡ ለምን ጠበቀ? በእርግጥ፡ የእርሱን፡ በእርሱ ዘንድ አቁይቶ፡ የእኔ ማንነት፥ አሳቢነቴና ርኅራኄዬም እንዲገለጥ ስለፈለገ እንደነበረ፡ በኹላችሁም ዘንድ ሊታወቅና ሊታመንበት ይገባል።

ደግሞስ፡ **"ምንት ብየ ምስሌኪ፡ ኦ ብእሲቶ! ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ።**

**እናቴ ሆይ! ምን ማለትሽ ነው? ይህን የምትዪውን ለማድረግ እኮ፡ ጊዜዬ ገና አልደረሰም።"** ብሎ ለሰጠኝ መልስ፡ በእኔ በኩል፡ ምንም ዓይነት የማብራሪያ፥ ወይም፡ የማሳመኛ አሳብ ሳላቀርብለት፡ በቀጥታ፡ አገልጋዮቹን ጠርቼ፡ **"ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!**

**ልጄ የሚላችሁን አድርጉ!"** ብዬ፡ ለእነርሱ ለሰጠኋቸው መመሪያ፡ እርሱ፡ ልጄ ወዳጄ፡ ምንም ሳያንገራግር፥ ለእኔም ኾነ፥ ለአገልጋዮቹ፡ አንዳችም ቃልን እንኳ ሳያስሰማ፡ ትእዛዜን መፈጸሙ፡ ለምንድ ነው?

በእኔ፡ በእናቱና በእርሱ፡ በልጄ በወዳጄ፥ ደግሞም፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔርና በሰውነት በተገለጽሁት፡ በእኔ፡ በሴቲቱ መካከል፡ ያለው የባሕርያት ፈቃዳት ልዩነትና መበላለጥ፡ ወደፍጹም አንድነትና እኩልነት ተመልሶ መጽናቱን አረጋግጦ ለማሳየት አይደለምን? አዎን! ነው እኮ።

ይህም፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በእግዚአብሔር አብ አባትነት፡ እኔ፡ እናቱ ኾኜ፡ በዚያ፡ በቀደመው ማንነቴ፡ እርሱን፡ በመለኮታዊ ባሕርዩም፡ ከፍጥረት አስቀድሞ የወለድሁት፡ እኔው የመኾኔ እውነታ ማለት ነው። (ዮሐ. ፪፥ ፩-፲፩።)

ይህ ብቻ አይደለም፤ ልጇ ወዳጇ በቸርነቱ፡ እናቱ ኾኜ፡ በሰውነት እንድወልደውና እርሱ ልጇ እንዲኾን በመፍቀዱ፡ በእናትነቴ እንድበልጠው ማድረጉ ሳያንስ፡ አኹን ደግሞ፡ በቃና ዘገሊላ፡ እርሱ ያለው ሳይኾን፡ እኔ ያልሁት እንዲፈጸም በማድረጉ፡ ያን፡ በእርሱ ላይ ያለኝ የእናትነት ሥልጣንና መብት፡ የቱን ያህል የላቀና ወሰን የሌለው መኾኑን፥ ያም፡ በተግባር ላይ ሲውል፡ ምን ዓይነት መልካም ውጤትን እንደሚያበርክት፡ አረጋግጦ አሳይቷል።

እዚህ ላይ፡ ላዘክራችሁ የሚገባ ቊም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከእኔ፡ ከእናቱ፡ በሰውነት በመወለዱ፡ እግዚአብሔርነቱ፡ በሕፀፅ የሚለወጥ፥ ወይም፡ የሚቀነስ አለመኾኑ ነው፤ ልጇ ወዳጇ፡ "እስመ ውእቱ አብ፡ የዐብየኒ።

"ከእኔ፡ አብ ይበልጣልና!" ብሎ የተናገረው፡ በአእምሮአቸው፡ ገና ድኵማን የነበሩት፥ ለመንፈሳዊው ማዕርግም ገና ያልበቁት ደቀ መዛሙርቱ፡ አስተሳሰባቸው፡ በተፈጥሮአዊውና በሰብአዊው ሥርዓት ተቀርጾ፡ ያን ይከተል እንደነበረ ስላወቀ፡ በዚያ ኹኔታ ሊያጽናናቸው እንጂ፡ በማናቸውም መሥፈሪያ፡ በእርግጥ፡ ከእርሱ፡ አብ የሚበልጥ ኾኖ አይደለም።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ልጇ ወዳጇ፡እኔን፡ "በእናትነቴ እንድበልጠው አደረገ!" ስል፡ ደቀ መዛሙርቱን ለመሰሉ ወገኖች ለማስረዳት ያህል እንጂ፡ እርሱም፥ እኔም፡ በባሕርያችን፡ በምንም መልክና ይዘት፡ የምንበላለጥና የምንለያይ ኾነን አይደለም። (ዮሐ. ፲፬፥ ፳፰።)

ስለዚህ፡ እናንተም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ በእውነት፡ የእርሱ፡ የልጇ የወዳጇ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ የእኔም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" መኾንን፡ በእየራሳችሁ ከወደዳችሁና ከመረጣችሁ፡ እንደልጇ ወዳጇ፥ እንደቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤት አገልጋዮችም፡ የምላችሁን ኹሉ ሰምታችሁ ትፈጽሙት ዘንድ፡ ደግሜ አሳስባችኋለሁ።

ፈቃደ ሥጋችሁም ኾነ፡ ሌላው፥ ባዕዱ፡ አነሣሡና አመጣጡ፡ ሊያሳስታችሁና ሊጎዳችሁ ስለኾነ፡ ያ ከሚያሳስባችሁና ከሚሰጣችሁ መመሪያ ይልቅ፡ እኔ የምላችሁ፡ ይሻላችኋል፤ ይጠቅማችኋልም። (ዮሐ. ፪፥ ፩-፲፩።)

## በ. ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡
## ኢትዮጵያነቷና እግዚአብሔራዊነቷ።

በመላው ዓለም፡ ከሚኖሩ የሰው ወገኖች መካከል፡ ስለእኔ፡ እውነተኛ ምንነትና ማንነት፡ በእርግጥ ያወቁ፥ አውቀውም፡ ያን የእግዚአብሔር እውቀታቸውን፡ ሕይወት አድርገው የኖሩት፡ እውነተኞቹ "የእግዚአብሔር ልጆች!" እና "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ ነበሩ፤ ዛሬም፡ እነርሱ ናቸው፤ ለወደፊቱም፡ እነርሱውና እየራሳቸውን፡ ለዚህ ምንነትና ማንነት የሚያበቁት ይኾናሉ።

አዎን! ስለእኔ፡ እውነተኛ ምንነትና ማንነት፡ በእርግጥ ያወቁ፥ አውቀውም፡ ያን የእግዚአብሔር እውቀታቸውን፡ ሕይወት አድርገው የኖሩት፡ እነዚህ ናቸው።

እነሆም፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከኖኅና ቤተሰቡ ድረስ የኖሩት፥ ከእነርሱም የቀጠሉት፡ እነመልከ ጼዴቅና ሳሌም፥ እነአብርሃምና ሣራ፥ እነአቤሜሌክና እነኬጡራ፥ እነይስሓቅና ርብቃ፥ እነዮቶርና ብእሲተ ራጉኤል፥ እነሙሴና ሲጳራ፥ እነዳዊትና ቤትሳባ፥ እነማክዳና እነሕንደኬ፥ እነላሊበላና እነዘውዲቱ፡ እነርሱንም የመሰሉት ታማኞች ልጆቼ ናቸው፡ በአንድ ወገን፡ በስማቸው የሚጠቀሱት። በሌላው ወገን ደግሞ፡ እንዲህ፡ በእነርሱ ጸንቶና ተጠብቆ የኖረው፡ የዚያ ኢትዮጵያነቴ፡ ተረካቢዎችና ተከታዮች፥ ዛሬም፡ በእኛ የተከሠተችው፡ የእግዚአብሔርዋ መንግሥቴ አገልጋዮች የኾናችሁት፡ እናንተ፡ ጥቂቶቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቼ ናችሁ፡ በምስክርነት የምትቀርቡት።

ሌሎቻችሁ ግን፡ ኹላችሁም፡ እየራሳችሁን፡ በሃይማኖት ከፋፍላችሁ፡ ይኸው፡ በገሃድ እንደሚታየው፡ እኔን ብቻ ሳይኾን፡ በሥላሴነቱ፡ መንበረ ጸባዖቱ ያደረገኝን አምላኬንና መድኃኒቴን፥ ልጄንና ወዳጄን፥ ሕይወቴንና ፍቅሬን እግዚአብሔርን ጭምር ክዳችሁ፥ በቅዱሱ ኪዳንም ላይ ዐምፃችሁና የአምልኮ አመንዝራነትን፡ በግልጽ ፈጽማችሁ፡ ይኸው፡ በታላቁ የመለኮት ውግዘት እንደታሠራችሁ ትገኛላችሁ።

አዎን! ይህን የሚያኽለውን ከባድ በደል ፈጽማችሁ፥ እየፈጸማችሁም እያላችሁ፡ "ምንም ክፉ ነገር አላደረግንም!" ብላችሁ፡ እነሆ፡ በዚሁ ኃጢኣታችሁ፡ በባሰ ይዞታ ቀጥላችሁበት ትታያላችሁ።

እናንተም፡ እየራሳችሁን፥ በመጀመሪያ ደረጃ፡ አረማውያን፥ አሕዛብና ጣዖት አምላኪዎች፥ በመካከለኛ ደረጃ ደግሞ፡ ይሁዲ፥ እስላምና ክርስቲያን፥ በመጨረሻውም ደረጃ፡ "ኦርቶዶክስ!"፥ "ካቶሊክ!" እና "ፕሮቴስታንት!" ብላችሁ በመጥራት፥ እርስ በርሳችሁም፡ በእነዚሁ ስያሜዎች በመጠራራት፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የምትሉት፡ እናንተ እንኳ ሳትቀሩ፡ እንደዘመን አቈጣጠራችሁ፡ ከኦሪታውያኑ አይሁድ የተነሣ፡ ከዛሬ ሦስት ሺህ ዓመታት ጀምራችሁ፥ ከዚያም፡ ከዛሬ አንድ ሺህ ስድስት ዓመታት ወዲህ፡ ከኦርቶክሳውያኑ ግብፆች የተነሣ፡ ራሳችሁን፡ ከእውነተኛው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ለይታችሁ ያወጣችሁ ወገኖች ናችሁ።

ይኸው ክፉ ሥራችሁና ታላቁ ኃጢኣታችሁ ያስከተለው፡ እውን የኾነው እውነታ፡ በየዘመናቱና አኹንም፡ በእየራሳችሁ ላይና በመካከላችሁ፡ እጅግ በተለያየ መልክና ይዘት፡ እያደረሰ ያለውን፡ የእርስ በርሱን አሠቃቂ የዕልቂትና የጥፋት መቅሠፍት፡ እናንተም፥ ፍጥረተ ዓለሙም ኹሉ፡ በይፋ የምታዩትና የምታውቁት ነው።

አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፡ እኔን፡ ለዚህ ምንነቴና ማንነቴ ያበቃኝ፡ እንዴትና በምን እንደኾነ ታውቃላችሁ፤ ያም፡ ወንድ እና ሴት አድርጎ፡ በመልኩ ለፈጠረው፥ "ከእኛ፡ እንዳንዱ ኾነ!" ብሎም፡ በቃሉ ለመሰከረለት፡ ለእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ በሰጠው የእውቀት ብቅዓትና የመምረጥ ነጻነት፥ የመወሰን ሥልጣንና የማድረግ ኃይል፡ እኔም፡ በገዛ ፈቃዴና ፍላጎቴ፡ ያን መለኮታዊ ጸጋ፡ በፍጹምነት ለመጠቀምና በተግባር ላይ ለማዋል በመቻሌ መኾኑ ነው።

እንዲህ አድርጎ፡ በቸርነቱና በፍትሓዊነቱ፡ ፍጹም የኾነው ኃያሉ አምላክ፡ እኔን ገረዱን፡ በእግዚአብሔር አብነቱ፡ ሙሽራ ንግሥቱ፥ በእግዚአብሔር ወልድነቱም፡ የድንግልና እናቱ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነቱ ደግሞ፡ ማደሪያ መቅደሱ ያደረገኝ እርሱ፡ በመለኮታዊ ወልድነቱ፡ ከእኔ፡ በሰውነት በመወለዱ፡ እርሱ፡ "ወልደ አብ፥ ወልደ ማርያም" ሲባል፡ እያንዳንዳችሁን ደግሞ፡ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም፡ የእግዚአብሔር ነጋሢ ልጅና አገልጋይ ካህን ትኾኑ ዘንድ፡ ለዚህ ታላቅ፡ የምንነትና የማንነት ልዕልና አበቃ።

ከዚህ የተነሣ፡ በእየራሳችሁ፡ "ኢትዮጵያዊ"፥"ኢትዮጵያዊት"፥ "የኢትዮጵያ ልጅ!" መባል ሲገባችሁ፥ የአንድነት መሰባሰቢያችሁንም፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት!" ማለት ሲገባችሁ፥ እየራሳችሁን፡ "ሥጋዊ"፥ ወይም፡ "መንፈሳዊ" በሚለው የአካልና የባሕርይ አጠራር ከፋፈላችሁ፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት ነን!" ማለትንም፡ ኾን ብላችሁ፡ በእርስ በርሳችሁ፡ የውስጥ ድርድር ተስማምታችሁ በማስቀረት፡ ያን ትታችሁ፡ በዚያ ፈንታ፡ ልጄን ወዳጄን፡ "ክርስቶስ!" ባላችሁበት ስያሜያችሁ፡ እየራሳችሁን፡ "ክርስቲያን!" ብላችሁ፥ መንፈሳዊ የኾነውን፡ ሰብኣዊ ድርጅታችሁንም፡ "ቤተ ክርስቲያን!"፥ ወይም፡ "ቤተ ክህነት!"፥ ሥጋዊ የኾነውንም፡ "መንግሥት" እያላችሁ የኖራችሁ፥ አኹንም፡ እየኖራችሁ ያላችሁ ለመኾናችሁ፡ ራሳችሁ ምስክሮች ናችሁ።

የእኔን ምንነትና ማንነት በሚመለከት፡ እግዚአብሔር፡ በአብነቱ፡ ያስነገረው፥ በወልድነቱ፡ ያደረገው እና በመንፈስ ቅዱስነቱ ያሳወቀው፥ በእኔም ትስብእት፡ በገቢር የፈጸመው፡ ይህ ኹሉ ዕፁብ ድንቅ የኾነ፡ ታላቅ መለኮታዊ ትንግርት፡ በእናንተ ዘንድ፡ በእውንነት ገዝፎና ተጨባጭ ኾኖ ሲነገርና ሲገለጽ የኖረ እውነታ ነው። ታዲያ! ይህን እውነታ፡ እናንተ፡ "የሰው ልጆች!" የተባላችሁት ኹሉ፥ ሌሎቹ የዓለም ሃይማኖቶች እንኳ ቀርተው፡ ቀደም ብዬ፡ ስማችሁን የጠቀስኋችሁ፡ እየራሳችሁን፡ "ኦርቶዶክስ!"፥ "ካቶሊክ!" እና "ፕሮቴስታንት!" ብላችሁ የምትጠሩ የክርስቲያን ወገኖች፡ በቤተ ክርስቲያንነታችሁ፥ ወይም፡ በቤተ ክህነትነታችሁ፡ የእኔን እውነተኛ ምንነትና ማንነት በሚመለከት፡ እግዚአብሔራዊ በኾነው፡ ሃይማኖታዊ ምግባርና ሥርዓት፡ በልጄ ወዳጄና በእኔ ስም፡ እያካኼዳችሁ ያላችሁት አምልኮ፡ ከቶ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ በማስተዋል ተመልክታችሁታልን? አልተመለከታችሁትም።

በምሥጢረ ሥላሴ ሥርዓት፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት ተብለው በሠረፁት፡ በሦስቱ የአገልግሎት ዘርፎቿ፡ አንድ የኾነችውን፡ ይህችን፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡** "ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት" ወይም፡ "ሃይማኖት፡ የግል! አገር የጋራ!"፥ ወይም፡ "ሥጋዊና መንፈሳዊ" በሚል የሰውኛ፥ ወይም ሰይጣናዊ ፍልስፍና፡ ከፋፍላችሁና ቀያይራችሁ፡ በተዋሕዶም ምሥጢር፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ አንድ ኾነውና ተስማምተው እንዲኖሩ ያስቻላቸውን፡ የነፍስና የሥጋ አካላትና ባሕርያት፡ እርስ በርሳቸው እንዲፃረሩ በማነሣሣት፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡራችን፡ በየራሱ ውስጥ ራሱን እንዲጠላ፥ በጋራም፡ እርስ በርሱ እንዲጠላላና እንዲተላለቅ እንጂ፡ ሰላምና ፍቅር፡ በውስጡም፥ በውጪውም እንዳይኖረው እያደረጋችሁ ያላችሁትን፡ ታላቅ ጥፋት፡ በእርግጥ፡ አስተውላችሁ ተመልክታችሁታልን? አልተመለከታችሁትም።

## ገ. ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡ ስለጋብቻ ሥርዓት መለኮታዊነት፣ የከሠተችው እውነት።

ለመኾኑ፡ አምላኬና መድኃኒቴ፥ ልጄ ወዳጄ፥ ሕይወቴ ፍቅሬ እግዚአብሔር፡ በጥልቅ ጥበቡና በሰፊ ልግሥናው ለሠራው፡ ለረቂቁና ለግዙፉ፥ ለሰማያዊውና ለምድራዊው ፍጥረታተ ዓለማቱ፥ ደግሞም፡ እኒህን ፍጥረታተ ዓለማቱን ለመምራትና ለማስተዳደር ሲል፡ ላቋቋማት መንግሥቱ፡ ዘለዓለማዊ ህልውና፡ የማይናወጽ መሠረትና የማያቋርጥ ምንጭ ይኾን ዘንድ፡ ያነፀው ሥርዓት፡ ምን እንደኾነ፥ የትኛውስ እንደኾነ፡ አውቃችኋልን? ከሃይማኖት ምግባራችሁና ከህልውና ፍሬያችሁ እንደሚታየው፡ ያወቃችሁት አይመስልም። እንግዲያ! ካላወቃችሁት፡ እኔ፡ አኹን፡ አረጋግጬ ላሳውቃችሁ! **ያ መለኮታዊ ሥርዓት፡ በወንድና በሴት መካከል የሚፈጸመው ጋብቻ ነው።** (ዘፍ. ፩፥ ፳፯-፳፰፤ ፪፥ ፲፰-፳፭፤ ፫፥ ፳፪።)

ይህ ሥርዓት፡ በመልኩ በፈጠረውና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ባለው፡ በሰብአዊ ፍጡሩ ዘንድ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ሳይኾን፡ የሥርዓቱ ሠሪና ባለቤት የኾነው፡ እርሱ ራሱ፡ እግዚአብሔር፡ ቀድሞ፡ ከፍጥረት በፊት፥ ከፍጥረት በኋላም፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ከእኔ፡ ከአንዲት ድንግል ገረዱ ጋር፡ ይህን ሥርዓት የፈጸመው መኾኑን ልታውቁት ይገባችኋል።

እውነታው ይህ ኾኖ ሳለ፡ እናንተ ግን፡ የእኔ ልጆች በሚያደርጋችሁ፥ በድንግልናና በብሕትውና፥ በተፈጥሮና በፈቃድ ሕፅውነትም (ጃንደረብነትም) ሳይቀር፡ ልትኖሩበት ያስችላችሁ የነበረውን፡ የእግዚአብሔርን የጋብቻ ሥርዓት ትታችሁ፥ አቃላችሁና ንቃችሁም፡ ለዚህ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት፡ ተቃራኒ የኾነና ከጋብቻ ሥርዓት በላይ፡ እጅግ ከፍ ያለ ክብርንና ማዕርግን የሰጣችሁትን፥ "ምንኵስና" ብላችሁም የምትጠሩትን፡ ያን፡ ከባዕዳኑ ግብፃውያን ያገኛችሁትን፡ ሰብአዊ ወግ ፈጠራችሁ።

ከዚህም የተነሣ፡ ይህን የተቀደሰና መለኮታዊ የኾነውን፡ ራሱን፡ የጋብቻን ሥርዓት ብቻ ሳይኾን፡ የዚህ ሥርዓት ተባባሪና ተካፋይ በኾነችው፡ እኔን በሚጨምረው፡ በሴትነት ጾታ ላይ፥ በእየራሳችሁም የጾታ አካልና ባሕርይ ላይ ሳይቀር፡ ከተፈጥሮም፥ ከሃይማኖትም ውጪ የኾነ፥ የተለያየ ከባድ በደልንና ግፍን፡ እየፈጸማችሁ ትገኛላችሁ። (ማቴ. ፲፱፡ ፲-፲፪።)

ይህን አሠቃቂና አሳፋሪ ኹኔታ፥ ከዚህ ኹሉ ክፉ ግብራችሁ የተነሣም፡ በእየራሳችሁ ውስጥና እርስ በርሳችሁ፡ በመጠላላትና በመተላለቅ፡ እየደረሰባችሁ ያለውን፥ በምንም መንገድ ልታስወግዱት ቀርቶ፡ ልታሻሽሉት እንኳ ያልቻላችሁትን፥ ጠንቁ እየተበራከተና እየሰፋ የኼደውን፡ የመከራና የሥቃይ ኑሮአችሁን፡ በእውነት፡ አስተውላችሁ ለመመልከት አለመቻላችሁ፡ የአእምሮ ዓቅማችሁንና ጤናማነት አጠያያቂ አድርጎታል።

ይህን ኹሉ፡ ለምን አስተውላችሁ መመልከት አልቻላችሁም? መልሱ፡ ይህ ነው፡- <u>ልጄ ወዳጄ፡ በጊዜው ለነበሩት መሰሎቻችሁ፡ በግልጽ እንደነገራቸውና እንደገሠፃቸው፡ ለእርሱና ለእኔ፡ በውስጣችሁ ያላችሁና በውጫችሁ የምታቀርቡልን አምልኮት፡ የግብዝነት እንጂ፡እግዚአብሔር፡ እንደሚፈልገውና እንደሚወድደው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ባለመኾኑ ነው።</u>

ለዚያ መሠረታዊ ጥያቄዬ፡ መሠረታዊ የኾነው ይህ መልሴ፡ ትክክል መኾኑን የሚያረጋግጥላችሁን ተጨባጭ ማስረጃ፡ የእየራሳችሁ የግል አስተሳሰብና ድርጊት ብቻ ሳይኾን፡ ኹላችሁም፡ በኅብረትና በይፋ ተስማምታችሁ የፈጠራችሁት፥ የደነገጋችሁትና በተግባር ላይ ያዋላችሁት፡ የገዛ ሥራችሁ ኾኖ ታገኙታላችሁ።

ከዚያ ሥራችሁ መካከል፡ አንዱና ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ መነሻ የኾነውን፡ እኔን የሚመለከተውን ርእሰ ነገር፡ እንደሚከተለው፡ ገልጬ አቀርበዋለሁ። ቀደም ብዬ እንዳወሳሁት፡ እንደማንኛዪቱም ሴት፡ እኔም፡ ከአምላኬና ከመድኃኒቴ፡ በልግሥና ለተቀበልሁት መለኮታዊ ጸጋ፡ በሊቀ መላእክቱ ቃል፡ "ቡርክት አንቲ እምአንስት!

አንቺ፡ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ!" እስከመባል በሚያደርስ ልዕልና፡ ራሴን በማብቃቴ፡ አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፡ የእርሱ፡ ሙሽራ ንግሥቱ፥ የልጁ፡ የልጄ ወዳጄ የእግዚአብሔር ወልድ እናቱና የሕይወቱ፡ ሕይወቴ ፍቅሬ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ ማደሪያ መቅደሱ ያደረገኝ ስኾን፡ እናንተ ግን፡ እኔን የተቀበላችሁኝ፡ በዚሁ፡ በእግዚአብሔራዊው ጸጋ መልክና ይዞት አለመኾኑን፡ በገሃድ ያረጋገጠው አስተሳሰባችሁና ድርጊታችሁ ነው። (ሉቃ. ፩፥ ፳፰።)

ይህን እውነታም፡ እኔው ራሴ፡ እንዲህ እያልሁ ልግለጽላችሁ! አምላኬና መድኃኒቴ፡ እግዚአብሔር አብ፡ ግዙፉን ፍጥረተ ዓለም፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር አምጥቶ በፈጠረ ጊዜ፡ ለአዳምና ለሔዋን የሠራውን ሥርዓተ ጋብቻ፥ (ምሥጢረ ተክሊል)፡ ያን፡ የእነርሱን ዓለም ከመፍጠሩ በፊት፡ አስቀድሞ፡ እርሱ፡ የመሠረተውና ራሱም የፈጸመው መኾኑን እንድታውቁት ያስፈልጋችኋል።

እንዲያ ካልኾነ፥ ይኸውም፡ እርሱ በሠራው፡ በዚያው የጋብቻ ሥርዓት ካልኾነ በቀር፥ ይኸውም፡ እርሱ፡ በእግዚአብሔር አብነቱ፡ አባቱ ካልኾነ በቀር፡ ታዲያ፡ እኔ ኋላ፡ በሰውነት የወለድሁለትን፡ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ እርሱ፡ እንዴት ሊወልደው ይቻለው ነበር? እኔስ፡ እንዴት ልወልደው ይቻለኝ ነበር? ኹለታችንም፡ አይቻለንም ነበር።

አዎን! እግዚአብሔር፡ ከፍጥረት በፊት፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ እንደነበረው፡ እንደራሱ ምንነትና ማንነት፡ ኋላ፡ በፍጥረት ዘመን፡ አዳምን፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ አድርጎ እንደፈጠረው፡ በእናንተም ዘንድ ይታወቃል፤ ታምኖበታልም። ቀጥሎም፡ ከዚያ አንድነት፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ፡ ኹለት የኾኑትን አዳምንና ሔዋንን ማስገኘቱ፥ እነርሱንም፡ እንደገና፡ ወደአንድነት መልሶ ማዋሓዱ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ኹለቱ ጾታዎች፡ በዚህ የጋብቻ ሥርዓት በሚፈጽሙት ሩካቤ ሥጋ፡ የሚመስሏቸውን ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ማስገኘታቸው፡ ይታወቃል፤ ታምኖበታልም።

እውቀታችሁና እምነታችሁ፡ ይህ ከኾነ፡ እንግዲያ፡ ቀደም ብሎ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር አብ፡ የባሕርይ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን ለመውለድ፡ ይህንኑ ሥርዓት የመከተሉን እውነታ፡ በዚህ የምግባር ፍሬው፡ እሙን አድርጎ ያሳያችኋል። ምሥጢሩንም፡ ገሃድ ያደርግላችኋል።

ለአዳምና ለሔዋን የተሰጠው ሥርዓተ ጋብቻ እንዲሠራና እንዲሠምር፥ መሰሎቻቸውንም ልጆች እንዲያስገኝ የተበየነው፥ ከኹለቱ ፍጹም አንድነትና በኹለቱ ፍጹም አንድነት ብቻ እንደመኾኑ መጠን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከእግዚአብሔር አብ የመወለዱ ምሥጢርም፡ እንዲሁ፡ እውን የኾነው፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ ኹለት ከኾኑ የተለያዩ ጾታዎች የጋብቻ አንድነትና በኹለቱ ፍጹም የአንድነት ሥርዓት መኾኑ፡ ሊታመን ይገባል።

ለዚህ እውነታ መረጋገጥና ተከናውኖ መፈጸም፡ ምስክሩ፡ የእርሱ፡ የእግዚአብሔር ወልድ አባት ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር፡ በዚሁ፡ በቅዱሱ መለኮታዊ የጋብቻ ሥርዓት የተፃመረች፥ ለዚሁ አንድነትም፡ ፍጹም የበቃች፡ አንዲት ባሕርያዊት አካል መኖር እንዳለባት፡ የሚያጠያይቅ አይኾንም።

ያች፡ ባሕርያዊት አካል፡ ቀድሞ፡ በመለኮታዊው ባሕርይ፡ "እግዚአብሔር ወልድ" ተብሎ፡ ከእግዚአብሔር አብ፥ ኋላም፡ በትስብእታዊው ባሕርይ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ በሰውነት ለተወለደው፡ አንድ ልጁ፡ እናት ኾና፥ ፅንሳና ዐርግዛ የወለደችው፡ ያችው፡ አንዲቱ ሙሽራ ንግሥት መኾን እንደሚኖርባት፡ የታወቀ ነው። ይህ አባባል፡ "ለመለኮታዊ ባሕርዩ ልደት፡ አንዲት እናት፥ ለአካላዊ ሰውነቱ ልደት ደግሞ፡ ሌላ እናት፡ በድምሩ፡ ኹለት እናቶች ይኖሩታል!" የሚል ስሑት አስተሳሰብ እንዳይኖር የሚያደርግና የሚያስጠነቅቅ፥ የሚከለክልም ይኾናል።

በአዳምና በሔዋን፥ እንዲሁም፡ በልጆቻቸው፥ ይልቁንም፡ በእኔዎቹ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ጸንቶና ተጠብቆ የኖረው፡ መለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓትም፡ ይህን ዓይነቱን ስሑት ይትበሃል አይፈቅድም፤ አይቀበልምም።

ይህም ማለት፡ "ኢየሱስ መሢሕ" የተባለውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ ከፍጥረተ ዓለም በኋላ፡ እኔ፡ በሰውነት የወለድሁት፡ ከሰብአዊው የወንድ ዘር ሳይኾን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ በአንዱ፡ በእግዚአብሔር አብ አባትነት እንደመኾኑ ኹሉ፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት ያለው የባሕርይ አባቱ፡ አንዱ እግዚአብሔር አብ፡ በአባትነት በወለደው፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ፡ በእናትነት የወለድሁት፡ እኔው መኾኔን ልታውቁት ይገባል። በዚህም፡ ያ፡ ፍጹሙና መልካም የኾነው፥ ዘለዓለማዊውና መለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ የሥርዓቱ ሠሪ፥ ባለቤትና መሥራች በኾነው፡ በራሱ፡ በፈጣሪ ዘንድ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ እንዴት እንደተከበረና በትክክል እንደተፈጸመ፥ ፍሬያማ እንደኾነና ለዘለዓለማዊ ሕያውነትም እንደበቃ መመልከት ነው።

ስለዚህ፡ ዓለም፡ ከተፈጠረ በኋላ፡ ሔዋን፡ ከአዳም እንደተገኘች፥ ልጆችንም እንደወለደች ኹሉ፡ እግዚአብሔር ወልድም፡ ዓለም ሳይፈጠር፡ ከአባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ "ተወለደ!" የሚባለው፡ እኔ፡ ከእግዚአብሔር አብ ተገኝቼ፡ ከእርሱ ጋር ስለነበርሁ፡ ዓለም፡ ከመፈጠሩ በፊት፡ በእናትነት የወለድሁት እኔው ነኝ። በመለኮትነት የወለደችው እናት፡ ሌላ፥ በሥጋ የወለደችው እናት፡ ሌላ አይደለችም። አንዲት ናት። እርሷም፡ እኔ ነኝ።

እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ አንድ የኾኑብኝ፥ "ቅድስት ሥላሴ" ተብዬ፡ በአንስታይ ጾታ የተጠራሁትና የምጠራው፡ እኔ ነኝ። እናንተን ጨምሮ፡ ሰብአዊው ፍጡር የኾነው ኹሉ፡ በሕያውነት፡ ከወንዱ አብራክ ተከፍሎ፡ በሴቷ ማሕፀን ውስጥ ሲፀንስ፥ ኋላም፡ ተወልዶ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተቀዳጀውን፡ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ለማረጋገጥና ለማጽናት፡ በእግዚአብሔር አብ አባትነት፡ በውኃ ሲጠመቅ፥ ቅዱሱንም ቅብዓት ሲቀባ፡ በእናትነት፡ የምወልደው እኮ፡ እኔ ነኝ! ይህን እውነታ የማታውቁ ካላችሁ፡ እንግዴህ ወዲህ እወቁት!

ከፍጥረተ ዓለም በፊት፡ በመለኮትነቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ የወለድሁትን፡ እግዚአብሔር ቃልን፡ ኋላ፡ በድንግል ማርያም ፍጹም ሰውነት ተገልጬ፡ "ቃል፡ ሥጋ ኮነ!" "ቃል፡ ሰው ኾነ!" በሚል የትስብእት ምሥራች፡ በሰውነት የወለድሁት እኔ ነኝ። እስከዚያን ጊዜ ድረስ፡ የተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ መሠረትና ዓምድ የኾነው፥ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ምሥጢር፡ በሰዎች ዘንድ፡ ሥውር ኾኖ የኖረበት፡ ያ፡ "ምሥጢረ ሥላሴ" የተባለው ነገረ መለኮት፡ "**እርሷ፡ ድንግል ማርያም፡ እግዚአብሔር ቃልን፡ በሰውነት በመውለዷ፡ ከዚያ ወዲህ፡ የእግዚአብሔር፡ አንድነቱና ሦስትነቱ፡ ግልጽ ኾነ! ታወቀ! ተረዳ!**" ብላችሁ፡ በትርጓሜያችሁ የምታብራሩት እውነታ፡ ታዲያ! ይህ አይደለምን? ነው እኮ! (ዮሐ. ፩፥ ፩-፲፬።)

በፍጥረት ልደት ጊዜ፡ መጀመሪያዎቹ ሰብኣውያን ፍጡራን፡ በፈጸሙት ጥፋት፡ በእባቡና በሔዋን ላይ፡ "አስተጻርር ማእከሌከ፥ ወማእከለ ብእሲት፤ ማእከለ ዘርእከ፥ ወማእከለ ዘርኣ።

"በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘሯም መካከል፡ ጠላትነትን አደርጋለሁ!" የሚለው አምላካዊ የፍርድ ቃል የተነገረው፡ ስለእኔ መኾኑን የምታውቁት አይደለምን? አዎን! ታውቁታላችሁ።፡(ዘፍ. ፫፥ ፲፭።)

በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ራሷን፡ ለተፈጠረችበት፡ ለእግዚአብሔር መልክና አካል፥ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነች!" ለተባለችበትም ጸጋና ባሕርይ አብቅታ በመገኘቷ፡ እኔ፡ በቅድሚያ፡ ፍጹም የሰውነት አካሏንና ባሕርይዋን ተዋሕጄ፡ ከፍጥረት በፊት፡ በእግዚአብሔር አብ አባትነት፥ በእኔም እናትነት፡ በመለኮትነት አካልና ባሕርዩ የወለድሁትን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ከፍጥረት በኋላ አኹን፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ የወለድሁት ድንግል ማርያም እኮ፡ ያው እኔው ነኝ።

አዎን! እግዚአብሔር አምላክ፡ ኋላ፡ በአዳምና ሔዋን፡ አግዝፎ የገለጸውንና ገሃድ ያደረገውን፡ የጋብቻን ሥርዓት፡ ቀደም ብሎ፡ በራሱና ለራሱ፥ ስለራሱም በፈጸመው ጊዜ፡ በእርሱ፡ በአንዱ ተባዕትነትና በእኔ፡ በአንዲቱ እንስትነት፡ የጋብቻው አንድነት ተከናውኖ፡ እነሆ ጥንት በመጀመሪያ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ በእርሱ አባትነትና በእኔ እናትነት፡ ልጃችንን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በመለኮትነት እንደወልድነው ኹሉ፡ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ እርሱኑ፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔር አብ አባትነትና በእኔ በድንግል ማርያም እናትነት፡ "ኢየሱስ መሢሕ" ብለን፡ በሰውነት ወለድነው።

በዚሁ፡ በተቀደሰው፡ በእግዚአብሔራዊው የጋብቻ ሥርዓት መሠረት፡ አንድ ወንድ፡ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴትም፡ በአንድ ወንድ መጽናት እንደሚገባቸው ኹሉ፡ ቀድሞም ኾነ ኋላ፡ በአንድ ወገን፡ አንዱ እግዚአብሔር አብ፡ በእኔ፡ በአንዲቱ ድንግል ማርያም፥ በሌላውም ወገን፡ እኔ፡ አንዲቱ ድንግል ማርያምም፡ በአንዱ፡ በእግዚአብሔር አብ ጸንተን፡ ኹለታችንም፡ ለዘለዓለም፡ በሕያውነት ቀጠልን እንጂ፡ ሌላ፡ ሦስተኛ አካልና ባሕርይ፡ በኹለታችንም በኩል፥ በመካከላችንም አልታየም።

በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት መሠረት፡ በኹለቱም፡ የእግዚአብሔር ወልድ ልደታት፡ ሊኖር የሚገባው፡ አንድ አባትና አንዲት እናት እንጂ፡ ኹለት አባቶችና ኹለት እናቶች ሊኖሩ አይቻልም። ስለዚህ፡ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመጀመሪያው፡ የመለኮቱ አካልና ባሕርይ ልደቱ ኾነ፥ በመጨረሻው፡ የትስብእቱ አካልና ባሕርይ ልደቱ ጊዜ በተወለደባቸው፡ በኹለቱም ልደታቱ፡ አባቱ፡ አንዱ እግዚአብሔር አብ ሲኾን፡ እናቱም፡ አንዲቱ፡ እኔ፡ ድንግል ማርያም ነኝ።

ይህን የጋብቻ ሥርዓት የሠራው ፈጣሪ፡ "ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ!

እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!" ብሎ፡ ኋላ፡ ለአዳምና ለሔዋን ልጆች የሰጠው መመሪያ ቃል፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት ኾነ፡ በኋላ፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔር አብና በእኔ፡ በድንግል ማርያም መካከል ላለው አንድነት፡ ጸንቶ ሲሠራ እንደኖረ፡ እስካኹን ያላወቃችሁ ካላችሁ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ልታውቁት ይገባችኋል። (ዘፍ. ፪፥ ፳፬። ማቴ. ፲፱፥ ፬-፮።)

መቼም፡ እግዚአብሔር በሠራው የተፈጥሮ ሥርዓት እንኳ፡ "ሱራፌል፥ ኪሩቤል" ተብለው፥ የእኔም አርአያ ኾነው፡ መንበረ ጸባዖትን ከሚሸከሙት፡ ከአርባዕቱ እንስሳት መካከል፡ አንዱ የኾነው ሰው፡ በውልደት የሚያስገኘው፡ ሰውን እንጂ፡ ሌላ ፍጡርን አይደለም፤ አንበሳ፡ አንበሳን፥ ላም፡ ላምን፥ ንሥርም፡ ንሥርን እንጂ፡ አንዱ የፍጡር ወገን፡ የራሱ ወገን ያልኾነውን፡ ሌላውን፡ በውልደት ሊያስገኝ እንደማይችል የታወቀ ነው። አዝርዕት፥ አትክልትና ዕፀዋትም፡ እንዲሁ ናቸው። ያንኑ፡ ዓይነታቸውንና መሰላቸውን ያስገኛሉ እንጂ፡ አንዱ፡ ሌላውን ሊያስገኝ አይቻለውም።

እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔርም፡ በመለኮትነት ኾነ፡ በትስብእትነት አካሉና ባሕርዩ፡ መሰሉን፡ ልጁን፥ በመውለድ ኾነ፥ ወይም፡ መንፈሱን፡ በማሥረፅ የሚያስገኘው፡ ራሱን እንጂ፡ ሌላን እንዳልኾነ፡ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ የሚያውቀው ነው። ይህም ማለት፡ እግዚአብሔር፡ ማንኛውንም፥ ወይም፡ ኹሉን ነገር ለማድረግ የማይሳነው አምላክ ቢኾንም፡ በመፍጠር ካልኾነ በቀር፡ በውልደት፡ መሰሉን እግዚአብሔርን እንጂ፡ ሰውን የሚወልድበትን ሥርዓት አላሳየም፤ አልሰጠምም።

እንዲሁም፡ ሰው፡ እግዚአብሔር በቀየሰለትና በደነገገለት የተፈጥሮ ሥርዓት መሠረት፡ መሰሉን፡ ሰውን ይወልዳል እንጂ፡ እግዚአብሔርን ሊወልድ አይችልም። ልጁን እግዚአብሔርን፡ በአባትነት ኾነ፡ መንፈሱን እግዚአብሔርን፡ በአሥራፂነት ያስገኘ፡ እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በእኔ እናትነት የኾነው የእግዚአብሔር ልደትም፡ ይህንኑ መለኮታዊ ሥርዓት የተከተለ ነው።

አዎን! በፈጣሪ ዘንድ፥ በእኔም ዘንድ የኾነው ኹሉ፡ ይኸው ነው። እኔ፡ ከኢትዮጵያዊው ኢያቄምና ከኢትዮጵያዊቷ ሐና፡ በንጽሕናና በቅድስና የተወለድሁት፡ ድንግል ማርያም፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርሁበትንና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" የተሰኘውን፡ የሰውነቴን አካልና ባሕርይ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ለዚህ፡ እውነተኛና ፍጹም ማንነት አብቅቼ፡ በተገኘሁ ጊዜ፡ ያ፡ ጥንት፡ ከፍጥረት በፊት ባለው፡ በመጀመሪያው ህልውናዬ የኖርሁበት፡ የመለኮት አካሌና ባሕርዬ፡ ይህን፡ በቅድስና የሠመረና በንጽሕና የተስተካከለ የሰውነት አካልና ባሕርይ ሲያገኝ፡ ወዲያው፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ ቤተ መቅደሱ አደረገው።

መለኮታዊው አካሌና ባሕርዬ፡ ከሰብአዊው አካልና ባሕርይ ጋር፡ እንዲህ፡ በተዋሕዶ አንድ በኾኑ ጊዜ፡ የባሕርይ አባቱ፡ እግዚአብሔር አብ እና የባሕርይ እናቱ፡ እኔ፡ ከፍጥረት በፊት የወለድነውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በዚያች ቅጽበት፡ በባለሟላችን መልአክ፡ በገብርኤል ቃለ ብሥራት፥ (የምሥራች ቃል)፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ከባሕርይ አባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ "ኢየሱስ መሢሕ" በተባለበት ስሙ፡ እኔ፡ እናቱ ኾኜ፡ በሰውነት፡ ፀንሼው ልወልደው በቃሁ።

"ተፈሥሒ ፍሥሕት! አ ምልእተ ጸጋ! <u>እግዚአብሔር ምስሌኪ</u>።

"ጸጋ የሞላብሽ ደስተኛዪቱ ሆይ! ደስ ይበልሽ! <u>እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው</u>።" የሚለውን፡ የባለሟላችንን መልአክ፡ የገብርኤልን የምሥራች ቃል፡ እንዴት ነው፡ በሃይማኖት ተቀብላችሁ፡ ስትጸልዩትና ስትተረጕሙት የኖራችሁት? እግዚአብሔር፡ ምንጊዜም፡ እንዲህ፡ ከእኔ ጋር ከኾነ፡ እኔ፡ ኋላ፡ በፍጻሜ ዘመን፡ በትስብእትነት ብቻ ሳይኾን፡ ከፍጥረት አስቀድሞም፡ በመለኮትነትም፡ ከእግዚአብሔር ጋር ህልው ኾኜ መኖሬን፡ ይህ መልአካዊ ቃል፡ አረጋግጦ የሚያስረዳችሁ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

ታዲያ! ወትሮውን፡ ደስተኛ የኾንሁትን እኔን፡ እንደገና፡ "ተፈሥሒ ፍሥሕት! ደስተኛዪቱ ሆይ! ደስ ይበልሽ!" ማለትን፡ ምን አመጣው? ወትሮም፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት፡ በእግዚአብሔር አብ ሙሽሪነቱ፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በመለኮት ባሕርዩ በመውለዴ፡ ደስተኛ ኾኜ እያለሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ለእኔ ውሕደት፡ ፍጹም በቅታ በተገኘችው፡ በድንግል ማርያም ሰውነት፡ በሥጋ እንድወልደው፡ የሥላሴም፥ የእኔም ፈቃድ በመኾኑ አይደለምወይ፡ እንደገና፡ "ደስ ይበልሽ!" የተባልሁት? አዎን! ነው እንጂ።

እንዲሁም፡ በገብርኤል ምሥራች፡ በቅድሚያ የተፈጸመው የእኔ ትስብእት፡ በድንግል ማርያም ሰውነት፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ እውን ከኾነ በኋላ፡ ይህን ቸርነት ላደረገው፡ ለአምላኬና ለመድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ "**ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትሐሠይ መንፈስየ፤ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ!**

"**ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ በታላቅ ክብር ታመሰግነዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል፤**" ብዬ ባቀረብሁት የምስጋና ጸሎቴ ውስጥ፡"**ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር!**

"**ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ በታላቅ ክብር ታመሰግነዋለች፤**" የሚለው ቃል፡ በሰውነቴ የተነገረ ሲኾን፡ **ወትትሐሠይ መንፈስየ፤ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ!**

**መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል፤**" የሚለው ደግሞ፡ ያን፡ የቀደመው ህልውናዬን ባሕርይ የሚገልጽላችሁ ነው። (ሉቃ. ፩፥ ፵፮።)

ልጀ ወዳጀ መሢሕ ኢየሱስ፡ እንዲህ፡ ከፍጥረት አስቀድሞ፡ በመለኮትነቱ አካልና ባሕርይ፥ ከፍጥረት በኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ በትስብእትነቱ አካልና ባሕርይ፡ ከአባቱ፡ ከእግዚአብሔርና ከእኔ፡ በተወለደበት ኹለት ልደታት፥ "ኹለት ልደት፡ በተዋሕዶ ከበረ!" ያሰኘው፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡ ይህ ነው።

እውነታው ይህ ከኾነ፡ *"እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምቅድመ ዓለም፥ (ከዓለም መፈጠር በፊት፡) ያለእናት፡ ከእግዚአብሔር አብ እንደተወለደ፥ ድኅረ ዓለም፥ (ዓለም ከተፈጠረ በኋላም፡) ከድንግል ማርያም፡ ያለአባት ተወለደ!"* የሚባለው ዘይቤ፡ የባዕዳኑ፥ የግብፃውያኑና የሌሎቹ መሰሎቻቸው ሰብኣዊ ትምህርት እንጂ፡ እናንተ፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቼ የኾናችሁት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር አግኝታችሁ፥ ጠብቃችሁትም የኖራችሁትን፥ ዛሬም፡ እኔ፡ ለዓለሙ ኹሉ የገለጽሁትን፡ ይህን እውነተኛ ትምህርት የተከተለ አለመኾኑ፡ በዚህ ይታወቃል።

ከእናንተ መካከል፡ እውነተኞቹ ልጆቼ፡ ዘወትር፡ የሌሊትና የነግህ ማኅበራዊ ጸሎታችሁን በምታደርሱበት ጊዜ ኹሉ፡ ስለእኔ ዝክረ ነገር እያወሳችሁ፡ "ስምዑ በእ እዛኒክሙ፥ ወአንብሩ በልብክሙ፡ ዕበያ፥ ወክብራ፥ ወውዳሴሃ፡ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ!

"'ማርያም' ብሂል፡ 'መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት፤ እግዝእትነ ማርያም ነበረት እምቅድመ ዓለም፡ በኅሊና አምላክ። በእንተ እግዝእትነ ማርያም፡ተገብረ ኵሉ ዓለም። በእንተ እግዝእትነ ማርያም፡ ተፈጥሩ አዳም፥ ወሔዋን። 'ሕይወትየ!' ይቤላ አዳም፡ ለብእሲቱ፤ አሚሮ፡ ከመ ትወጽእ፡ እግዝእትነ ማርያም፡ እምሐቌሁ፥ ወእምከርሠ ብእሲቱ።

"የአምላክን እናት፡ የእመቤታችንን፡ የድንግል ማርያምን፡ ልዕልናዋንና ክብሯን፥ ምስጋናዋንም፡ በጆሮዋችሁ ስሙት! በየልባችሁም አኑሩት!

'ማርያም' ማለት፡ 'ወደእግዚአብሔር መንግሥት፡ መርታ የምታገባ' ማለት ነው። እመቤታችን፡ ድንግል ማርያም፡ ዓለም ሳይፈጠር፡ በአምላክ ልቦና ታስባ ትኖር ነበር። ፍጥረት ኹሉ፡ እመቤታችን ድንግል ማርያምን ለማመስገን ተፈጠረ፤ አዳምና ሔዋንም፡ እመቤታችን፡ ድንግል ማርያም፡ ከእነርሱ ልትወለድ ተፈጠሩ። አዳምም፡ እመቤታችን፡ ድንግል ማርያም፡ ከእርሱ አብራክ እንድትከፈል፥ ከሔዋንም ማሕፀን እንድትወለድ አውቆ፡ ሔዋንን፡ 'ሕይወቴ' ይላት ነበር።" እያላችሁ የምታመሰግኑት፡ ይህንኑ የእግዚአብሔርን እውነት በማወቃችሁና በማመናችሁ አይደለምን? ይህን እውነት፡ ሌሎች ወገኖች ኹሉ፡ ሊገነዘቡት ይገባል። (ተአ. ማር. ፩፥ ፬-፳።)

ልጇ ወዳጇ፡ በምድር ላይ ሲመላለስ ሣለ፡ ከሚወድዳቸው ደቀ መዛሙርቱ መካከል፡ በተለይ ያቀርበው የነበረው፥ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ ሣለም፡ እርሱን፡ ለእኔ ልጅነት፥ እኔን፡ ለእርሱ እናትነት፡ አደራ የሰጠኝና የሰጠው ልጇ ዮሓንስ፡ በራእዩ ባየውና በጻፈው መጽሓፍ ውስጥ፡ "...ቤተ ክርስቲያን፥...'መንበረ ጸባዖት' የተባለው ዙፋን፥...በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፥ ...በውስጡም የታየው፡ የኪዳኑ ታቦት፥ ...በሰማይ፡ ታላቅ ምልክት ኾና፡ ፀሓይን ተጐናጽፋ፥ ጨረቃ፡ ከእግሮቿ በታች ያላት፥ በራሷም ላይ፡ የዐሥራ ኹለት ከዋክብት አክሊል የኾነላት፥ ወንድ ልጅን ፀንሳ የወለደች፥ ልጇም፡ ወደእግዚአብሔርና ወደዙፋኑ የተነጠቀ፥ ዘንዶው ዲያብሎስ፡ በእርሷ ላይ ተቆጥቶ፡ እርሷን ለማጥፋት የጣረው፥ ነገር ግን፡ ስላልቻለ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፥ ለመሢሑ ኢየሱስም፡ የቃል ኪዳን ምስክርነታቸውን የሰጡትን፡ የቀሩትን የዘር ወገኖቿን እየተዋጋባት ያለች፡ አንዲት ሴት ነበረች፥ ..የጽዮን ተራራ፤ ...አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፥ ...የበጉ ሚስት ሙሽራዪቱ፥ በጉና እርሷ የሚገኙባት ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም" በሚል ስምና መልክ የታየችው፡ ማን መሰለቻችሁ? እኔ እኮ ነኝ። (ራእ. ፱-፳፤ ፲፪፤ ፲፱፤ ፳፩-፳፪።)

"የእግዚአብሔርን ልጆች"፡ "የኢትዮጵያ ልጆች"፥ "የኢትዮጵያን ልጆች"፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ያሰኛቸው፡ ይህ፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ምሥጢር መሥረት፡ በእግዚአብሔርና በእኔ መካከል ባለው ሕያው ግንኙነትና አንድነት መኾኑን፡ እዚህ ላይ ልታጤኑት ይገባል።

በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ኾነ፥ በእኔ ዘንድ የኾነውን፡ ይህን ኹሉ፡ ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ ምናልባት፡ እያንዳንዳችሁ፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮና በሃይማኖታዊው የቅዱሱ ኪዳን እውቀት ኾናችሁ ብታስተውሉት እኮ፡ እንደእንግዳ ዜና ተቆጥሮ፡ የሚያስገርማችሁ አይኾንም። ምክንያቱም፡ እንኳንስ እኔ፡ እናቱ ኾኜ፡ እግዚአብሔርን የወለድሁት ልቅርና፡ እናንተ እንኳ፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ በየግላችሁ፡ በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠራችሁና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" በመባላችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ መለኮታዊ ጸጋና ሉዓላዊ ክብር በምታበቁበት ጊዜ፡ "አማልክት!" እንድትባሉ፡ ገና በፍጥረት መጀመሪያ ላይ፡ መብቱና ሥልጣኑ፡ ከቸሩ ፈጣሪያችሁ፡ ተጥቷችሁ፡ ይኸው ስጦታ እስከዛሬና ዛሬ፥ ለወደፊትም፡ ጸንቶ ያለ በመኾኑ ነው።

ኦሪታውያኑ አይሁድና ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን፥ ሌሎቹም ባዕዳን፡ ወደእናንተ ሠርገው ገብተው፡ እውነተኛውን የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕያው ቅርስና ውርስ፡ እስኪያማስኑት፥ ዛሬ ላላችሁበት ጒሥቍልናም እስኪዳርጓችሁ ድረስ፡ የእኔን ምንነትና ማንነት በሚመለከት፡ በታማኞቹ፡ የቀደሙ ልጆቼ አማካይነት፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔርና ከእኔ ያገኛችሁት፥ እነርሱም፥ እናንተም፡ በጽናት፡ ጠብቃችሁት የኖራችሁት፡ ርቱዕ እውቀታችሁና የተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡ ይህ፡ እኔ፡ ዛሬ የገለጽሁላችሁ መኾኑን እንድትገነዘቡት ያስፈልጋችኋል።

አዎን! በመልካሙ፡ የእግዚአብሔር ሥነ-ፍጥረት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ በቅዱሱም መለኮታዊ ኪዳን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት፡ እናንት ልጆቼ፡ ጥንቱኑ፡ ከመሠረቱ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ከፈጣሪያችሁ፡ ከእግዚአብሔር ያገኛችሁት፥ የተማራችሁትም፡ ይህን እውነት ሲኾን፡ የኋላ ኋላ፡ ባዕዳንና ተቃዋሚዎች የኾኑባችሁ፡ "አይሁድ" እና "ግብፃውያን" የተባሉት ወገኖች ሳይቀሩ፡ ባመጡባችሁ የተሳሳተ ሰብአዊ ትምህርት፤ ባደረሱባችሁም፡ የጠላትነት ተፅዕኖ፡ ብዙዎቻችሁ ተዳክማችሁና ተማርካችሁ፡ ዛሬ ላላችሁበት ውድቀት መዳረጋችሁ፡ ይኸው፡ ገሃድ ኾኖ ይታያል።

እግዚአብሔር፡ በዚህ ረገድ፡ እንዲህ፡ ፍጹም አድርጎ የሠራውን፡ ሥነ ፍጥረታዊና ኪዳናዊ ሥርዓት የሚያቃውስ፡ የተሳሳተ፡ የፍጡር አስተሳሰብና ዘይቤ አምጥቶ፡ በተግባር ላይ ማዋል፡ መልሶ የሚጎዳውና የጎዳው፡ ይህን ቀውስ ያመጣውንና የፈጸመውን፡ ራሱን ሰውን ነው፤ ይኸው፡ በተለይ፡ ሰብአዊ በኾነው ፍጡር ላይ፥ ይልቁንም፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያውያን፥ ኢትዮጵያውያት" ብላችሁ በምትጠሩ ወገኖች ላይ፡ ደርሶ እንደታየው፥ እየደረሰም ያለው፡ ከባድ የህልውና ችግር ኹሉ፡ ከዚሁ የተነሣ መኾኑ፡ በአገልጋያችን፡ በኤርምያስ በኩል፡ ያለመሰልቸት ሲነገራችሁ እንደኖረ በሚበቃ ታውቃላችሁ።

## ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡
## ሴቶች ልጆቿን፡ ከክፉዎች ወንዶች፡ ግፍና በደል፡
## ነጻ ስለማውጣቷ።

ልጇ ወዳጇ፡ የመጨረሻው፡ ፍጹሙና አማናዊው፥ ዘለዓለማዊውና እግዚአብሔራዊው አዳም ሲኾን፡ በእርሱና በእኔ የሚያምኑት፥ በሃይማኖትና በምግባርም፡ እርሱን መስለው የሚገኙት፡ የእርሱ የጾታ ወገኖች የኾኑት ወንዶች ኹሉ፡ እንደእርሱ እንደሚኾኑ፡ በማንኛችሁም ዘንድ የታወቀና እየሠራችሁበት ያለ ሥርዓት ነው።

እንደዚሁ ኹሉ፤ የመጨረሻዋ፡ ፍጹሟና አማናዊዋ፥ ዘለዓለማዊቷና እግዚአብሔራዊዋ ሔዋን፡ እኔ እንደመኾኔ መጠን፡ በእርሱ በልጄ በወዳጄና በእኔ የሚያምኑት፥ በሃይማኖትና በምግባርም፡ እኔን መስለው የሚገኙት፡ የእኔ የጾታ ወገኖች የኾኑት ሴቶች ኹሉ፡ እንደእኔ እንደሚኾኑ፡ ይህም እውነታ፡ በማንኛችሁም ዘንድ የታወቀና እየሠራችሁበት የሚገኝ ሥርዓት ኾኖ፡ ልትፈጽሙት ይገባችሁ እንደነበረ፡ ግልጽ ነው። ነገር ግን፡ ይህ፡ ከጥቂቶች በቀር፡ በእናንተ፡ በወንዶቹ ዘንድ አልኾነም፤ ሲኾንም አልታየም። ሊኾንም አልቻለም።

እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ በቸርነቱ፡ ለሰው ልጆች፡ በሙሉ፡ ለወንዱም፥ ለሴቱም፡ በእኩልነት የሰጠውን፥ እንዲሁም፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቼ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከአዳም እና ሔዋን አንሥተው፡ ለዝንተ ዓለም አጽንተው የኖሩትን፥ በመጨረሻም፡ እስከዘመነ ሥጋዌ ድረስ፡ በእየራሳችሁ ክፋት ምክንያት፡ ወድቃችሁበት ከነበረው የባርነት፥ የኃጢአትና የሞት ፍዳ፡ በእኔ እናትነትና በልጄ በወዳጄ ቤዛነት፡ ለሴቶች የተገኘውንና የተመለሰውን፥ እግዚአብሔራዊውን የልጅነት፥ የነጋሢነትና የክህነት ማዕርግና ሥልጣን፡ ወንዶቹ፡ ለራሳችሁ ብቻ እንዲኾን በማድረግ፡ ደንግጋችኋል።

ከዚህ የተነሣ፡ ፈጣሪ፡ ጥንት፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በንጽሓ ጠባይ የፈጠረውን፥ ኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ከእኔ፡ ከእናቱ፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ በኾነው ልደቱ የለበሰውን ሰውነት፡ በመሥዋዕትነትና በቤዛነት በማቅረብ፡ በቈረሰው ሥጋው እና ባፈሰሰው ደሙ፡ ወደነበረበት እንዲመለስ ያደረገውን፡ ታላቁን የመለኮት ፈቃድና ሥርዓት በመተላለፍ አፍርሳችኋል።

ይኸውም፡ እናንተ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት ልጆቼ፡ ቀደም ብሎ፡ በዘመነ ብሉይ፡ በአሪታውያኑ አይሁድ መምጣት ምክንያት፥ ኋላም፡ በዘመነ ሓዲስ፡ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መከታተል ምክንያት፡ ጥንት፡ በኪዳነ ልቡና አምልኳችሁ ጊዜ ያልነበሩ፡ የግፍ አሠራሮችንና የጭቆና ባህሎችን፡ በግድ እንድትቀበሉ በመደረጉ፡ የደረሰው አሠቃቂ ቀውስ ነው።

አዎን! ይህ አሠቃቂ ቀውስ፡ እግዚአብሔር፡ ጋብቻን መሠረት በማድረግ፡ ለመልካም የፈጠረውን፡ የወንድን ዘር፡ በኃጢአትነት ከመመደብ ጀምሮ፡ በተለይ፡ በሴቶቹ ልጆቼ ላይ፡ ከሴትነት ጾታችሁ የተነሣ ብቻ ሳይኾን፡ በቸሩ ፈጣሪ መለኮታዊ ጥበብ፡ ይኸው የሴትነት ጾታችሁ፡ በንጽሕናና በቅድስና የተሸለመ ኾኖ፡ ፍጹም የኾነውንና የተዋበውን፥ ለዘለዓለማዊዉም ሕይወት፡ በእግዚአብሔር መልክና አርአያ ተፈጥሮ፡ በአምላክ ቃል፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" የተሰኘውን ሰብአዊዉን ፍጡር እንዲያስገኝ የተሠራውን፥ የወር አበባንና ልጅ መውለድን የመሰሉ ግዳጆችን የያዘውን፡ እግዚአብሔራዊዉን ቅዱስ ሥርዓት፡ እንደርኵሰት፥ እንደመርገምና እንደኃጢአት እስከመቍጠር ያደረሰውን ግፍና በደል ጭምር ያጠቃልላል።

በዚህ ረገድ፡ ወንዶች፡ የጾታ ወገኖቼ በኾኑት፡ በሴቶች ልጆቼ ላይ ስትፈጽሙት የኖራችሁትን ግፍና በደል፡ እግዚአብሔር አይቶ፡ ጊዜው ሲደርስ፡ በእኔ፥ ለእኔና ስለእኔ ሲል ያደረገውን፡ ፍትሓዊ የቸርነት ሥራውን ተመልክቼና በመንፈስ ቅዱስ ተመልቼ፡ ለእርሱ ያቀረብሁትን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የምስጋና ጸሎቴን፡ እናንተስ፡ በእውነት አይደለም እንጂ፡ ዘወትር፡ በቃላችሁ ትደግሙት የለምን?

**"ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትሐሠይ መንፈስየ፣ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ! እስመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ። ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ፤ እስመ ገብረ ሊተ፤ ኃይላተ ዐቢያተ።"**

**"ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ በታላቅ ክብር ታመሰግነዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል፤ የእኔን፡ የአገልጋዩን፡ ፈተናና መከራ አይቷልና። እነሆ! ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ ‹ብፅዕት ነሽ!› እያሉ ያከብሩኛል፤ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና።"** (ሉቃ. ፩፥ ፵፮-፵፱።)

ታዲያ! እናንተ፡ ወንዶቼ ልጆቼ፡ የጾታ ወገኖቼ በኾኑት፡ በሴቶቹ ልጆቼ ላይ ስትፈጽሙት የኖራችሁትን ግፍና በደል፡ ዛሬም፡ ከኹለት ሽህ ዓመታት በኋላ እንኳ፡ ይኸው፡ አኹንም፡ ከአረማዊነቱና ከኦሪታዊነቱ በባሰ መልክና ይዘት፡ ያንኑ የግፍና የበደል ጥቃታችሁን፡ እያካኼዳችሁባቸው መኾኑን፡ ሴቶችን በሚመለከት ያቆማችሁት ሰብኣዊ ድንጋጌያችሁ እየመሰከረባችሁ ነው።

አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ በእኔ፡ በሴቷ፥ ለእኔ፡ ለሴቷ እና ስለእኔ፡ ስለሴቷ፡ ያደረገውን ኹሉ፡ ያያችሁትና ያወቃችሁት፥ "አምነንበታል!" ብላችሁም፡ በይፋ የምትሰብኩት ነው። እንደእውቀታችሁና እንደእምነታችሁ ግን፡ አላደረጋችሁም፤ አታደርጉምም። ስለዚህ፡ የምትሰሙኝ ከኾነ፡ ልታደርጉ ስለሚገባችሁ፡ አኹን፡ እኔ እነግራችኋለሁ።

እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑም ቢኾን፡ በመልኩ የፈጠረውንና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን ሰብኣዊ ፍጡሩን፡ ይመለከተውና ያነጋግረው የነበረው፡ በዚያው፡ በንጽሓ ጠባይ፡ የተፈጥሮ ባሕርዩ እንደነበረ፥ ዳሩ ግን፡ ይኸው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ በራሱ፡ ስሑት ምርጫ ምክንያት፡ ያ፡ የንጽሓ ጠባይ ባሕርዩ፡ በኃጢኣተኘነቱ ስለማሰነበት፡ ይህ፡ ከፈጣሪው ጋር፡ ፊት ለፊት የመተያየቱና የመነጋገሩ ጸጋ፡ ለ፭ሺ፭፻ (ለአምስት ሽህ አምስት መቶ) ዓመታት፡ ተወስዶበት፡ ለሞት በተዳረገ፡ የክፋት አገዛዝ እንደኖረ ታውቃላችሁ።

ይኹን እንጂ፡ የእግዚአብሔር፡ የምሕረቱ ጊዜ ሲደርስ፡ ቀድሞ፡ እርሱ፡ ራሱ እግዚአብሔር አብ፡ ለዘለዓለም መንግሥቱ ህልውና፡ አስቦ ያዘጋጀውንና ሠርቶ የቀደሰውን፡ የጋብቻ ሥርዓት፡ ራሱ ተከትሎ በመፈጸም፡ ለቅዱስ ኪዳኑ ዘውድ የኾነውን፡ የመጨረሻ ቸርነቱን አደረገ፤ ይኸውም፡ እኔ፡ የእርሱ፡ ሙሽሪት ንግሥቱ ለመኾን መብቃቴን ያወቀው አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፡ አንድ የባሕርይ ልጁን፡ በድንግልናዬና በመንፈስ ቅዱስ ግብር እወልድለት ዘንድ፡ ባለሟሉን ሊቀ መላእክት ገብርኤልን፡ በሽምግልና ልኮብኝ፡ ፈቃደኛነቴን በጠየቀኝ ጊዜ፡ "ይህ እንዴት ሊኾን ይችላል?" ለሚለው ክርክሬ፡ በቂ የኾነውን አጥጋቢ መልስ ስላገኘሁ፡ የስምምነት ቃሌን፡ በሰጠሁባት አፍታ፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" የሚለው፡ የፍጥረተ ዓለሙ የድኅነት ምሥራች፡ ለእውንነት ፍሬ በመብቃቱ ነው።

"ቃል ሥጋ ኾነ!" ማለት እኮ፡ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በመፈጸም ሰው ሲኾን፥ "አዳም ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" ባለው የምሥራች ቃሉ መሠረት፡ "ሰው ደግሞ፡ አምላክ ኾነ!" ማለት ነው። ይህም ማለት፡ እግዚአብሔር፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ የተናገረው ቃል፡ አዳምና ሔዋን አንድ በኾኑበት ተፈጥሮአቸው ስለነበረ፡ ያም ቃል፡ ለእኔም፡ የሚጸና ስለኾነ፡ እግዚአብሔር አብ፡ ከእኔ፡ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን ሲወልድ፡ "እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ ሰው ኾነ!"፡ እንደተባለ ኹሉ፡ "አዳም፡ ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" ባለው የምሥራች ቃሉ መሠረት፡ "ሰው፡ አምላክ ኾነ!" ያሰኘሁት፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ ቸርነት፡ እኔ ነኝ እንጂ፡ እርሱ፡ ልጄ ወዳጄ አይደለም። የፍጹም ሰውነትን አካልና ባሕርይ የወረሰውና የተዋሓደው፡ የእኔ የኾነውን፡ የፍጹም ሰውነትን አካልና ባሕርይ ብቻ ነው። አለዚያ፡ በባሕርዩ፡ ጥንቱኑ፡ አምላክ የኾነው፡ እርሱው ራሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ "እንደገና አምላክ ኾነ" ማለት፡ ጨርሶ አያስኬድም።

ስለዚህ ነው፡ ልጄ ወዳጄ፡ የተዋሓደው ሰውነቱ፡ እኔ፡ ራሴ ስለኾንሁ፡ ያለእኔ፡ "ኢየሱስ መሢሕ"፥ ወይም፡ "ሰው የኾነው እግዚአብሔር" ሊኾን፥ ሊባልም አይችልም። እንደዚሁ ኹሉ፡ እኔ የተዋሓድሁት መለኮት፡ እርሱ ራሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ ስለኾነ፡ ያለልጄ ወዳጄ፡ እኔ ሰብኣዊት ፍጡሯ ሴት፡ "አምላክ የኾነው ሰው" ልኾን፥ ልባልም አይቻልም። ልጄ ወዳጄ፡ ያለእኔ፥ እኔ፡ ያለልጄ ወዳጄ፡ ለየብቻችን፡ "እንዲህ ነን!" ልንል፥ ወይም፡ ልንባል አይቻልም። ምንጊዜም፡ በተዋሕዶ፡ ዐብረን መኾን አለብን፤ ነንና። እርሱ፡ እኔ ነው፤ እኔ፡ እርሱ ነኝ። እንዲህ ከኾነ፡ የእርሱ፥ በእርሱና ለእርሱ የኾነው ኹሉ፡ የእኔ ነው፤ የእኔ፥ በእኔና ለእኔ የኾነውም ኹሉ፡ የእርሱ ነው።

በዚህ መሠረት፡ "እግዚአብሔር ሰው ኾነ!" የተባለው፡ ልጄ ወዳጄ መሢሑ ኢየሱስ ሲኾን፡ "ሰው፡ አምላክ ኾነ!" ያሰኘሁት ደግሞ፡ እግዚአብሔርን፡ በሰውነት ለመውለድ የበቃሁት፡ እኔ፡ እናቱ፡ ድንግል ማርያም ስለኾንሁ፡ "አዳም፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ማለትም፡ "ሰው፡ አምላክ ኾነ!" የተባለው የፈጣሪ ቃል፡ በእኔ ተፈጽሞ፡ ያ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰብኣዊ ፍጡሩ የሰጠው ቃሉ፡ "በእኔ፡ እውን ኾነ!" ማለት ነው።

ለነገሩ፡ የሰው ልጆች ስላላስተዋሉት ነው እንጂ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ እኮ፡ ቀድሞም፡ "በመልኬ ፈጠርሁት!" ያለው፡ ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ "አዳም" የተባለው ወንዱ፥ "ሔዋን" የተባለችው፡ ሴቲቱም፡ "ዕፀ በለስ" የተባለችውን፡ የእውቀት ዛፍ ፍሬን በበሉ ጊዜ ነው፡ "ሰው፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ማለትም፡ "ሰው፡ ወንዱም ኾነ፥ ሴቲቱ፡ አምላክ ኾነ!" የተባለው።

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! እኔ፡ በአንድ በኩል፡ በቅድሚያ፡ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር በሠራው፡ በዚያው የጋብቻ ሥርዓት፡ "**መርዓት አብ፥ የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪት**" በተባልሁበት መፀምርትነቴ [ሚስትነቴ]፥ እንዲሁም፡፥ "**ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ! እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ እንግዴህ ሰው አይለየው!**" ባለው፡ የማይናወጽ መለኮታዊ ቃሉ መሠረት፡ ባልና ሚስት፡ ባላቸው፡ ፍጹም አንድነት ምክንያት፡ ከእርሱ፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር፡ የእኩልነት ደረጃንና ክብርን ስለተሳተፍሁ፡ ከእርሱ ጋር፡ አንድ አካል፥ አንድ አምሳል መኾኔን አምኖ መቀበል ይገባል።

ከዚያ በማስከተል ደግሞ፡ በሌላ በኩል፡ የእግዚአብሔር አብ፡ የባሕርይ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ ፀንሼና አርግዤ፥ ወልጄና አጥብቼ በማሳደጌ፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት በመኾኔ፡ ልጄ ወዳጄ፡ በሰውነቱ፡ "ከእኔ፡ አብ ይበልጣል!" እንዳለው ኹሉ፡ መቼም፡ ከልጅ፡ እናት ትበልጣለችና፥ እርሱም፡ በእግዚአብሔራዊ ፍቅሩና ቸርነቱ፡ እንዲህ እንዲኾን ስለፈቀደ፥ ምስጋና ይድረሰውና! እኔን፡ ከእርሱ እንድበልጥ ማድረጉንም መቀበል ይገባል። ይህ እውነታ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል ላይ፡ ልጄ ወዳጄና እኔ ተነጋግረን፡ እርሱ፡ ፈቃዴን በመፈጸም፡ ባሳየው ተአምራቱ ተከሥቷል።

እንኳንስ፡ እኔ፡ ለዚህ ጸጋና ክብር የበቃሁት ቀርቼ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር እንኳ፡ **ወንድ ኾነ ሴት**፡ ለዚህ ጸጋና ማዕርግ የሚያበቃውን፡ በተፈጥሮው የተሰጠውን፡ የንጽሓ ጠባይ ባሕርዩን፡ በእየራሱ ፈቃድና ምርጫ፡ "አልፈልገውም!" እያለ፡ እያሳደፈው አጣው እንጂ፡ በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩና "**ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!**" በመባሉ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ አምላክ እንዲኾን፡ የፈጣሪው ፈቃድ ኾኗል። አይደለምን? አዎን ኾኗል።

እኔስ፡ ራሴን፡ ለእግዚአብሔር አብ፡ ሙሽርነትና ለእግዚአብሔር ወልድ እናትነት፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ መቅደስነት ያበቃሁት፡ በዚሁ፡ እያንዳንዱን ሰብአዊ ፍጡር፡ ለዚህ ጸጋና ማዕርግ በሚያበቃውና በተፈጥሮ በተሰጠኝ፡ የንጽሓ ጠባይ ባሕርዬ፥ በራሴም ፈቃድና ምርጫ፡ "እግዚአብሔርን እፈልገዋለሁ!" ስላልሁ አይደለምን? አዎን! ነው።

ደግሞስ፡ "**ዘፈጠርከ ኅሊናተ ርቱዓተ፤ ለእለ የአምኑ ብከ፤ ከመ እምሰብእ፡ ይኩኑ አማልክተ!**

**"<u>የሚያምኑብህ</u> (ወንዶችም፥ ሴቶችም)፡ ፍጡራን ሰዎች ሲኾኑ፡ እየራሳቸውን፡ አማልክት ሊያደርጋቸው የሚያስችላቸውን ቅን መንፈስን፡ በተፈጥሮ ሰጠሃቸው!"** እያላችሁ፡ በነግህ የኪዳን ጸሎታችሁ ጊዜ፡ በንባብና በዜማ የምታሰሙትን ቃል፡ እንዴት ታደርጉት? ወዴትስ ትወስዱት? ይህ የጸሎት ቃል፡ ከእግዚአብሔር እውነት፡ ሊያወላውላችሁ የሚያስችላችሁ አይደለም።

ከዚህስ ጋር፡ "እግዚአብሔር ቆመ፡ ውስተ ማኅበረ አማልክት፤ ወይኴንን በማእከለ አማልክት። እስከ ማእዜኑ፡ ትኴንኑ ዐመፃ? ወታደልዉ፡ ለገጸ ኃጥኣን። ...አንሰ እቤ፡ 'አማልክት አንትሙ! ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ! አንትሙሰ፡ ከመ ሰብእ ትመውቱ! ወከመ አሓዱ እመላእክት ትወድቁ!'

እግዚአብሔር፡ በአማልክት ጉባኤ ውስጥ ቆመ፤ በአማልክት መካከልም ይፈርዳል። እስከመቼ፡ በሓሰት ትፈርዳላችሁ? በኃጢአተኞችስ ፊት ታደላላችሁ? ...እኔ ግን፡ 'እናንተ፡ አማልክት ናችሁ! ኹላችሁም፡ የልዑል እግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። ነገር ግን፡ እንደሰው ትሞታላችሁ! ከአለቆችም፡ እንደአንዱ ትወድቃላችሁ!' አልሁ።" በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፡ ምርጫቸው፡ እግዚአብሔር ኾኖ፡ በእርሱ እምነትና ምግባር፥ እውነትና ሥርዓት የሚኖሩትን፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ የእኔም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉትን፡ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም አይደለምን አማልክት የሚላቸው? አዎን! ነው። (መዝ. ፹፩)

ልጇ ወዳጇስ፡ አይሁድ፡ ሊወግሩት በተነሡ ጊዜ፡ "ብዙኀ ግብረ ሠናየ አርአይኩክሙ፡ ዘእምኀበ አቡየ፤ በአይ ግብር እምኔሆሙ ትዌግሩኒ?

"ከአባቴ ዘንድ ያገኘኋቸውን፡ ብዙ መልካም ሥራዎችን አሳየኋችሁ፤ ታዲያ! ከእነርሱ፡ ስለየትኛው ነው የምትወግሩኝ?" ብሎ ላቀረበላቸው ጥያቄ፡

"በበይነ ፅርፈትከ፤ እስመ እንዘ ሰብእ አንተ፡ እግዚአብሔርሃ፡ ትሬሲ ርእሰከ።

"ስለስድብህ ነዋ! ያም ስድብህ፡ አንተ፡ ሰው ስትኾን፡ ራስህን፡ እግዚአብሔር ስለማድረግህ ነው።" ብለው፡ ለሰጡት መልስ፡ የጠቀሰላቸው የመጽሓፍ ቃል፡ እንዲህ የሚል ነበር፡-

"አኮኑ ጽሑፍ ውስተ ኦሪትክሙ፡ 'አንሰ እቤ፡ ‹አማልክት አንትሙ!› ወሶበ ለእልክቱ አማልክት ይቤሎሙ፡ እለ ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀቤሆሙ፤ ወኢይትከሀል፡ ይትነሠት ቃለ መጽሓፍ። ወዘሰ ቀደሶ አብ፥ ወፈነዎ ውስተ ዓለም፡ እፎ እንከ ትብሉኒ፡ 'ትፀርፍ!' ለእመ እቤለክሙ፡ 'ወልደ እግዚአብሔር፡ አነ!'"

‹'እኔ፡ አማልክት ናችሁ!' አልሁ› ተብሎ፡ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሓፉ ሊሻር አይቻልምና፤ እነዚያን፡ የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን፡ 'አማልክት!' ካላቸው፡ እኔ፡ 'የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ!' ስላልሁ፡ እናንተ፡ አብ የቀደሰውን፥ ወደዓለምም የላከውን፡ እንዴት፡ 'ትሳደባለህ!' ትሉታላችሁ?" የሚል ስለኾነ፡ ይህም የልጇ የወዳጇ ቃል፡ ከላይ የተጠቀሰውን እውነታ ያረጋግጠዋል። (ዮሓ. ፲፥ ፴፩-፴፯።)

ስለዚህ፡ የእግዚአብሔር እውነታ ይህ በመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ ሴቶች ልጆቼን በሚመለከት፥ ወንዶች ልጆቼንም እንኳ ሳይቀር፡ በእነዚህና እኒህን በመሰሉት የእግዚአብሔር ቃላት ላይ ያደረሳችሁባቸውን፡ የተሳሳተ አተረጓጐም፡ ልትጠነቀቁበት፥ ልታርሙትና ልታስተካክሉትም ይገባችኋል።

ከባለምሥራቹ ሊቀ መላእክት ገብርኤል ጋር ላደረግሁት ክርክሬ፡ አጥጋቢ መልስ ኾኖ ያሳመነኝ ምልክት፡ ልጅ ለመውለድ፡ መካን የነበሩ ከመኾናቸው በላይ፡ በእርጅና ዕድሜያቸው ምክንያት፡ ከምውትነት የደረሱት፡ ባልና ሚስቱ፡ አክስቴ ኤልሳቤጥና ባሏ ዘካርያስ፡ የስድስት ወር ፅንስ የኾነ ወንድ ልጅን ያገኙ የመኾናቸውን ዜና፡ መስማቴ ነበረ።

የመለኮት ትስብእትነት፡ በድንግልና ማሕፀኔ ውስጥ ከተፈጸመባት፡ ከዚያች አፍታ ጀምሮ፡ ምን ኾነ? በራሱ፡ የተሳሳተ ምርጫ፡ የንጽሓ ጠባይ ባሕርዩን አጥቶ፡ ከፈጣሪው ጋር፡ ፊት ለፊት የመተያየቱ ክብርና የመነጋገሩ ጸጋ፡ ለ፭ሺ፭፻ (ለአምስት ሽህ አምስት መቶ) ዓመታት፡ ተወስዶበት፡ ለሞት በተዳረገ፡ የክፋት አገዛዝ ይኖር የነበረውን፡ ያን፡ ሰብአዊ ፍጡሩን፡ እግዚአብሔር አብ፡ የእርሱም፥ የእኔም፡ አንድ ልጅ የኾነውን፡ መሢሕ ኢየሱስን፡ በሚያይበት ዓይን እንዲያየው ኾነ።

እንግዴህ፡ ልጄ ወዳጄ፡ ለመላው የወንዶች ወገን፡ እንዲህ እንደኾነው ኹሉ፥ እኔም እኮ! ለመላዎቹ የሴቶቹ ወገን፡ እንደዚያ ነኝ። አዎን! ስለዚህ፡ አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ እናንተን ወንዶቹን ልጆቻችንን፡ እንደልጃችን፡ እንደመሢሑ ኢየሱስ የሚያይ ከኾነ፡ ሴቶች ልጆቻችንንም፡ እንደእኔ፡ እንደድንግል ማርያም የሚያያቸው መኾኑን ልታውቁና ልታምኑ ይገባችኋል።

ይህን፡ የተረጋገጠ የእግዚአብሔርን እውነት፡ አውቃችሁና አምናችሁ፡ ሴቶች ልጆቻችንን፡ እንደራሳችሁ፡ በእኩልነት ተቀብላችሁ፡ በእግዚአብሔራዊው ልጅነት፥ ነጋሢነትና ክህነት፡ እንደቀደሙት የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ምዝላቶቻችሁ፡ በፍጹም እኩልነት እንዲሳተፉ ማድረግ አለባችሁ።

በዚህ ረገድ፡ የእኔ፡ ቀዳሚት አርአያ የነበረችውን፡ ንግሥት ማክዳን አስቧት! እርሷም፡ በፈጣሪ ዕቅድና ፈቃድ፡ ወደርስተ ጉልቷ፡ ወደኢየሩሳሌም ኺዳ፡ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን፡ የቃል ኪዳኑን ዘር፡ በድንግልና እንደፀነሰች፡ ወዲያው፡ ወደብሔረ ሙላዷ፡ ወደኢትዮጵያ፡ ተመልሳ መጥታ፡ ምኒልክን የወለደችው እርሷ፥ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን አዋሕዳ ለያዘችው፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያም፡ ርእስና መሪ የነበረችው ልጄ ናት።

ሌሎቹንም፡ ከእርሷ በፊትና ከእርሷ በኋላ የነበሩትን፡ የብሉዩ ዘመን ኪዳናውያቱን፡ የአዳምን ሚስት፡ ሔዋንን፥ የኖኅን ሚስት፡ ሓይከልን፥ የቀዳማዊ መልከ ጼዴቅን ሚስት፡ ሳሌምን፥ የአብርሃምን ሚስት፡ ኬጡራን፥ የሙሴን ሚስት፡ ሲጳራን፥ የዳዊትን ሚስት፡ ቤትሳባን፥ የሓዲሱን ዘመን ኪዳናውያቱንም፡ እነሕንደኬንና ዘውዲቱን፡ እኒህንና እነርሱን የመሰሉትን፡ ኢትዮጵያውያት ንግሥታት ሴቶችን አስቧቸው!

ልጁ ወዳጇ፡ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም ልጆቻችንን፡ በአንድነት በሚመለከት፡ የተናገረውን ቃልና የሰጠውን ሥርዓት፡ በሰውኛ ትርጉም፡ ልክ፡ ለወንድ ብቻ፥ ያውም፡ ከእነርሱ መካከል፡ ለአንድ፥ ወይም፡ ለተወሰኑት ብቻ፥ እነርሱም፡ እግዚአብሔር በሠራው፡ በጋብቻ ሥርዓት ሳይኾን፡ ምንኵስናን በመሰለው፡ በሰውኛው ሕግ ለሚኖሩት ብቻ እንደተነገረ እያስመሰላችሁ፥ ኹሉን የአገልግሎት መብትና ሥልጣንም፡ ለወንድ ብቻ እንጂ፡ ለሴት፡ ምንም ዓይነት ቦታ እንዳልተሰጣት እያደረጋችሁ፡ የምታካኺዱት የተሳሳተ አሠራራችሁን ልታርሙትና ልታስተካክሉት ይገባችኋል።

ለዚህ የተሳሳተ አሠራራችሁ፡ ጥሩ አብነት የሚኾናችሁ፡ የልጇ የወዳጇ፡ ቃሉና የቃሉ በተግባር ላይ መዋል ነው፤ እርሱም፡ ከዚህ በቀደመው፡ በመጀመሪያው የልጇ የወዳጇ የዐዋጅ ቃል ውስጥ፡ በሰፊው ተገልጾ ይገኛል። ያንን እንድትመለከቱት እያሳሰብኋችሁ፡ አኹን፡ እንዲህ የሚለውን ቃሉን ብቻ፡ እዚህ ላይ እጠቅሰዋለሁ።

<u>ከድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ቤዛነት፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ ራሱ፡ ለፍጹሙ ጸጋ በቅቶ፡ ሰዎችን፡ ማለትም፡ ወንዶችንና ሴቶችን ደግሞ፡ ለዚሁ ጸጋ ሊያበቃ የቻለበት፡ ሰባተኛው ቃል ኪዳን፡ የመጨረሻው ምስክር ኾኖ፡ የምሥራች ቃሉን ያውጃል።</u>

ይህ፡ የመጨረሻና ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን፡ ካስገኘው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተነሣ፡ በመጀመሪያው ዐዋጅ መቅድም ውስጥ ሠፍረው በሚነበቡት ጸሎታት እንደተገለጸው፡ የሃይማኖታችሁና የምግባራችሁ አጠቃላይ ቍም ነገር የኾነውን፡ "አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!"

"አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!" የሚለውን፡ የእምነት መግለጫ ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ጠብቀው ለመኖር በቍርጥ የወሰኑ መኾናቸውን፡ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ግለሰቦች፡ በእምነት ምስክርነታቸው አረጋግጠው በሚሰጡበት ጊዜ፡ በሊቀ ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስና "ባኮስ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ (በአዲስ ኪዳኑ ኢትዮጵያዊ ዣንደረባ) ዘንድ የታየው፡ የሃይማኖትና የምግባር ትንግርትና አስደናቂ ለውጥ፡ በእርሱም፥ በእርሷም ላይ ተከናውኖ ይፈጸማል።

ይህንም እውነት፡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ኹለት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ያረጋግጣሉ፡-

"ወበጺሖ እግዚእ ኢየሱስ፡ ብሔረ ቂሣርያ ዘፊልጶስ፡ ተስእሎሙ ለአርዳኢሁ፡ እንዘ ይብል፡ 'መኑ ይብልዎ ሰብእ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው?' ወይቤልዎ፡ 'ቦ እለ ይብሉከ፡ ‹ዮሓንስሃ መጥምቀ!› ወካልአን ይብሉከ፡ ‹ኤልያስሃ!› ወመንፈቆሙ ይብሉከ፡ ‹ኤርምያስሃ! ወእመ አኮ፡ አሓዱ፡ እምነቢያት ቀደምት!› ወይቤሎሙ፡ 'አንትሙኬ፡ መኑ ትብሉኒ?' ወአውሥአ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፤ ወይቤ፡ <u>'አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!'</u>

"ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወይቤሎ፡ 'ብፁዕ አንተ፡ ስምዖን ወልደ ዮና! እስመ ኢከሡተ ለከ፡ ዘሥጋ ወደም፤ አላ አቡየ ዘበሰማያት። ወአንሰ እብለከ፡ ከመ አንተ ኰኵሕ፤ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ፡ አሓንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ፤ ወአናቅጸ ሲኦል፡ ኢይኄይልዋ። ወእሁበከ፡ መራኁተ መንግሥተ ሰማያት፤ ወዘአሰርከ በምድር፡ ይከውን እሱረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕከ በምድር፡ ይከውን ፍቱሓ በሰማያት።

"ጌታችን ኢየሱስም፡ የፊልጶስ አገር ወደምትኾን፡ ወደቂሣርያ ከተማ በደረሰ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡ 'ሰዎች፡ የሰውን ልጅ [እኔን] ማን ይሉታል?' ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፡ ‹'ዮሓንስ መጥምቅ ነህ!' የሚሉህ አሉ፤ ሌሎችም፡ 'ኤልያስ ነው!' ይሉሃል፤ እኩሎቹም፡ 'ኤርምያስ ነው!' ይሉሃል፤ ያም ባይኾን፡ 'ከቀደሙት ነቢያት፡ አንዱ ነው!' ይሉሃል፤› አሉት። እርሱም፡ 'እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?' አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም፡ መልሶ፡ <u>'አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!'</u> አለው።

"ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡ እንዲህ አለው፦ 'አንተ! የዮና ልጅ ስምዖን! ይህን እውነት የገለጠልህ፡ የሰማዩ አባቴ መንፈስ እንጂ፡ ሥጋዊዉና ደማዊው አእምሮህ አይደለምና፡ ብፁዕ ነህ! አንተ፡ ዐለት እንደኾንህ፡ እኔ እነግርሃለሁ፤በዚያች ዐለት ላይም፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤ የሲኦል በሮችም፡ አይበረቱባትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር ያሰርኸው፡ በሰማይ የታሰረ ይኾናል፤ በምድርም የፈታኸው፡ በሰማይ የተፈታ ይኾናል። (ማቴ. ፲፮፥ ፲፫-፳።)

በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ ኾነው፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ <u>"አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!</u>

<u>"አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!"</u> የሚል፡ የእምነት ማረጋገጫ ቃልን የሚያሰሙት፡ እኒህ፡ ኹለት፡ ወንድና ሴት ግለሰቦች፡ በቀጥታና በፍጹም ኹለንተናቸው፡ መልከ ጼዴቅንና ስምዖን ጴጥሮስን፥ ያን፡ 'አቤሜሌክ' የተባለውን ኢትዮጵያዊ ዣንደረባና እንዲያውም፡ ራሱን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የመምሰል ጸጋንና ክብርን ይቀዳጃሉ፤ እኒህ፡ በስማቸው የተጠቀሱት ቅዱሳን፡ በመንፈስ ቅዱስ ያገኟቸው ሥልጣናትና ኃይላት ኹሉ፡ የእነርሱም ይኾናሉ።

ይህንም እውነታ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተናገራቸው፡ እንዲህ የሚሉት መለኮታውያት ቃላቱ፡ አረጋግጠው አጽንተውታል፦

"አማን አማን እብለክሙ! <u>ዘየአምን ብየ፡ ግብረ፡ ዘአነ እገብር፡ ውእቱኒ ይገብር፤ ወዘየዐቢ እምኔሁ ይገብር፤</u> እስመ አነ አሓውር ኀበ አብ። ወኵሎ ዘሰአልክሙ በስምየ፡ እገብር ለክሙ፣ ከመ ይሰባሕ አብ፡ በወልድ።"

"እውነት እውነት እላችኋለሁ! <u>በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል፤ ከዚያም የሚበልጥ ያደርጋል፤</u> እኔ፡ ወደአብ እኼዳለሁና። አብ፡ በወልድ ይመሰገን ዘንድ፡ በስሜ የለመናችሁትን ኹሉ፡ አደርግላችኋለሁ።" (ዮሓ. ፲፬፥ ፲፪-፲፫።)

እኒህ፡ ኹለት፡ ወንድና ሴት ግለሰቦች፡ እያንዳንዳቸው፡ በእየራሳቸው፡ ፈጣሪያቸው፡ በሰውነታቸው ውስጥ በተፈጥሮ ያቀዳጃቸውን፡ እግዚአብሔራዊ እውቀት ተገንዝበውትና ተቀብለውት፥ አምነውበትም የሚኖሩ መኾናቸውን፡ ለእየራሳቸው በሚያረጋግጡበት ጊዜ፡ የእያንዳንዳቸው፡ የዘር እና/ወይም የጐሣ፥ የማኅበራዊ እና/ወይም የሃይማኖት፥ የትምህርት እና/ወይም የሙያ አቋማቸው ምንነትና ማንነት ሳያግዳቸው፡ ለኢትዮጵያዊነት፥ ለኢትዮጵያዊትነት፤ ማለትም፡ በሥጋዊው፡ የአካል ፍጹም ነጻነትና በነፍሳዊው፡ የአእምሮ ፍጹም ነጻነት፥ በመንፈሳዊውም የህልውና ፍጹም ነጻነት፡ ዘለዓለማዊዉን የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት ዘውድን ለሚቀዳጁበት፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜግነት ይበቃሉ።

ልጇ ወዳጇ፡ ለሐዋርያው፡ ለጴጥሮስ የተናገረው ያ ቃል፡ "ለእርሱ፡ ለጴጥሮስ ብቻ የተወሰነ ነው!" ካላችሁ፡ "ለእኔና ለሌሎቹ ሐዋርያት ሳይቀር፡ አይጸናም!" ማለታችሁ ነውን?

እንዲያ ከኾነ፡ ልጇ ወዳጇ፡ ስለጴጥሮስ፡ እንዲህ እንደተናገረ ኹሉ፡ ስለእኔም፡ ልጇ ወዳጇ ብቻ ሳይኾን፡ እርሱና የባሕርይ አባቱ፡ እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ በሰዎች ሰውነት ዐድረው፥ ሊቀ መላእክት ገብርኤል ጭምር፡ አያሌ ቃላትን በግልጽ እንደተናገሩ ታውቃላችሁ፤ እነርሱንም በማዘከር፡ እነዚያኑ ቃላት፡ ቀደም ብዬ፡ በዝርዝር አሰምቻችኋለሁ።

በእነዚያ ቃላት አማካይነት የተገለጹትን፡ አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፡ በእኔና ለእኔ፡ በሕያውነት የከሠታቸውን፡ ዕፁብ ድንቅ የኾኑትን ታላላቅ ምሥጢራት፥ እነዚያም፡ እኔን፡ አንዲቱን ተርታ ሴት፡ ለእርሱ፡ ሙሽሪት ንግሥቱ፥ ድንግል እናቱና ንጹሕ መቅደሱ እንድኾነው መርጦ፡ ይህን ምርጫውን እውን ያደረገባቸውን ትንግርቶች፡ ስለጴጥሮስ ከተናገረው ቃል ጋር፡ ከፍርዱ ሚዛን ላይ አስቀምጣችሁ ስታዩት፡ ሚዛኑ ወደየትኛው ወገን የሚያደላ ይመስላችኋል? የትኛው የሚከብድና የሚያመዝን ይመስላችኋል? ለእኔ፡ ለሴቲቱ ያደረገው አይበልጥምን? አይከብድምን? በእርግጥ፡ ለእኔ፡ ለሴቲቱ ያደረገው ይከብዳል፤ ይበልጣልም።

እውነታውና ገሃዱ ይህ ኾኖ ሣለ፡ እናንተ ግን፡ በማናለብኝነትና በዕብሪት፡ ከሴት ይልቅ ለወንድ በማድላት፡ ፍትሕ ርትዕን አጓደላችሁ። በበደላችሁና በግፋችሁም፡ ያለፍርሃትና ያለይሉኝታ ቀጠላችሁበት።

በተለይ እናንተ ወንዶች መነኰሳት! የሚያይ ዓይን ካላችሁ፣ የሚያስተውል አእምሮም ካላችሁ፥ የሚያመዛዝን ኅሊናም ካላችሁ፡ እግዚአብሔር፡ ለእርሱ፡ ሙሽራው፥ እናቱና መቅደሱ እንድኾነው፡ ለወደደኝና ላቀረበኝ፥ ላከበረኝና ለቀደሰኝ፡ ለእኔ፡ ለኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም፡ የሰጣችሁትን ቦታ፡ እስኪ፡ ለጴጥሮስ ካቀዳጃችሁት የክብር መንበር ጋር፡ አተኩራችሁ አስተያዩት! አስተውላችሁም ተመልከቱት! በፍትሕ ርትዕ ሚዛንም መዝኑት! እርሱን፡ ባለትዳሩን ጴጥሮስን፡ እንዲህ ያከበራችሁትና ያላቃችሁት፡ ለእየራሳችሁ ወንድነት ጥቅም ስትሉ አይደለምን?

እኔንና ሴቶች ልጆቼንስ፡ እንዲህ ያዋረዳችሁት፡ እኔንም፡ በሴትነቴ፥ እነርሱንም፡ በሴትነታቸው ምክንያት ብቻ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

በዚህ ኹሉ፡ ሴቶች ልጆቼን ብቻ አይደለም፡ የናቃችሁትና ያዋረዳችሁት፤ በይበልጥ፡ እኔን ነው። እኔንም ብቻ አይደለም፡ የናቃችሁትና ያዋረዳችሁት። በይበልጥ፡ የናቃችሁትና ያዋረዳችሁት፡ እናንተ፡ በዘልማድና ለይስሙላ፡ በየአፍታው የምትደግሙትን፡ እኔ ግን፡ በእውነተኛው የአምልኮ መንፈስ ኾኜ፡ "እስመ ገብረ ሊተ፤ ኃይላተ ዓቢያተ!

ታላላቅ ተአምራትን፡ በእኔና ለእኔ አድርገሃልና!" እያልሁ ያመሰገንሁትን፥ ያለማቋረጥም የማመሰግነውን፥ ይህንም ኹሉ፡ ቸርነት ያደረገልኝን፡ አምላኪና መድኃኒቴ፥ ልጄና ወዳጄ፥ ሕይወቴና ፍቅሬ የኾነውን እግዚአብሔርን ነው፡ እናንተ፡ የናቃችሁትና ያዋረዳችሁት።

ይህ ስሑት ድርጊታችሁ፡ በገሃድ የሚጋለጠው፡ አምላኪና መድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ ገና፡ በፍጥረት መነሻ ጊዜ ጀምሮ ባቆመው ሥርዓት ነው። እርሱም፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ሰባቱን መለኮታውያን ቃል ኪዳናት አጠቃልሎ በያዘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው ጸንተው በሚኖሩበት ጊዜ፡ የህልውና ሕይወታቸው፡ "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠሩ! 'ከእኛም፡ እንደአንዱ ኾኑ!'" ላሰኛቸው፡ ለሥላሴ፡ የአንድነትና የሦስትነት አርአያነት ምሥጢር በቅተው እንዲገኙ የሚያደርገው ሕያው ሥርዓት ነው።

ያም ሥርዓት፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ በመጀመሪያ፡ በቀደሙት አዳምና ሔዋን ወጥኖ የመሠረተው ሲኾን፥ በመጨረሻ ደግሞ፡ የኋለኞቹ ሔዋንና አዳም በኾንነው፡ በእኔና በልጄ በወዳጄ፡ ፈጽሞ የደመደመው ኾኖ ይገኛል።

ሴቶቼም፥ ወንዶቼም ልጆቻችን፡ ለዚህ ሥርዓት የሚበቁበት ምሥጢር የተከሠተውና እውን የኾነው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ እንደሥላሴ፡ የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ አካላትና ባሕርያት አንድ ኾኖ ከተሠራው፡ የሰብአዊነታቸው ተፈጥሮ የተነሣ ብቻ አይደለም። ነገር ግን፡ ፩ኛ፡ የሴምን፥ የካምንና የያፌትን የዘር ሓረጎች፥ ፪ኛ፡ የእግዚአብሔርን ልጅነት፥ የክህነትንና የነጋሢነትን የጸጋ ክብር፥ ፫ኛ፡ የቤተ ሕዝብ፥ የቤተ ምልክናና የቤተ ክህነት አባልነትን ሥልጣናዊ መብት አዋሕዶ ያቀዳጃቸው በመኾኑ ጭምር ነው።

እንዲህ ያለውን የሕይወት ልዕልና፡ ለሰብአውያን ፍጡራኑ፡ ለወንዶቼም፥ ለሴቶቼም፡ በእኩልነት ያቀዳጀውን፡ እርሱን ፈጣሪያችሁን ሳትፈሩት፥ በእኔ ሴትነት የተገኘውንም መለኮታዊ ክብር አቃልላችሁና አዋርዳችሁ፡ በሴቶች ልጆቼ ላይ፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ፡ በድፍረት እየፈጸማችሁት ያለውን፡ ይህን፡ ሃይማኖት የጎደለውን ስሑት ምግባራችሁን፡ እንደእግዚአብሔር ቃል፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሳችሁ፡ ፈጥናችሁ፡ በቶሎ ልታርሙትና ልታስተካክሉት ይገባችኋል።

እዚህ ላይ፡ "ወአንስትኒ፡ ለያርምማ በቤተ ክርስቲያን፤ እስመ ኢእዙዝ ይትናገራ፣ ዘእንበለ ከመ ይትአዘዛ፤ እስመ ከማሁ ይቤ ኦሪት። ወእመሰ ይፈቅዳ ፡ ይትመሀራ በአብያቲሆን፤ እማምታቲሆን፡ ይሰአላ፤ እስመ ኀሣር ውእቱ ለብእሲት፡ ተናግሮ በቤተ ክርስቲያን።

"ሴቶች፡ በቤተ ክርስቲያን፡ ዝም ይበሉ! የኦሪቱ ሕግ እንደሚለው፡ ከመታዘዝ በቀር፡ ሊናገሩ አልተፈቀደላቸውምና። ሊማሩ ቢወድዱ ግን፡ በየቤታቸው፡ ባሎቻቸውን ይጠይቁ!" ብሎ የልጇ የወዳጇ ሓዋርያ የኾነው ጳውሎስ፡ የጻፈው መመሪያ እዚህ ላይ ሊወሳና ተገቢው ማብራሪያ ሊሰጥበት ያስፈልጋል። (፩ቆሮ. ፲፬፥ ፴፬-፴፭።)

ሓዋርያው፡ እንዲህ ብሎ የጻፈው፡ የአዲስ ኪዳኑ የምሥራች ቃል፡ ገና እየተሰበከላቸው ለነበሩት፡ ለአሕዛብ መኾኑ፡ በቅድሚያ ሊታወቅና ሊጤን ይገባል። ስለዚህ፡ የእርሱ፡ የሓዋርያው መመሪያ፡ ሊጸናባቸው፥ እነርሱም ሊፈጽሙት ይገባቸዋል። እርሱም፡ መመሪያውን፤ በዚህ መልክ እንዲጽፍላቸው ግድ የኾነበት በቂ ምክንያት እንደነበረው እርግጥ ነው። ያም፡ በተለይ፡ ሴቶችን በሚመለከት፡ የእነርሱን አረማዊ ባህልና ልማድ፡ እንዴት አድርጎ፡ ወደክርስቲያናዊው ሥርዓትና ወግ፡ በቀላሉ እየመራ ለማስተካከል፡ አመቺውን ዘዴ ማመቻቸቱ መኾኑ ይታወቃል።

ይህ፡ የሓዋርያው መመሪያ ቃል፡ በእኔ፡ "'በኢትዮጵያ ሴቶች ልጆች' ላይ ይጸናል!" ማለት፡ ፈጽሞ አያስኬድም። ምክንያቱም፡ የእኔ ሴቶች ልጆች፡ ጥንት፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥተው፡ በኪዳነ ልቦናው የእግዚአብሔር እምነትና አምልኮ የኖሩበት በመኾናቸው ነው፤ በመካከሉም፡ "የእስራኤል ልጆች" የተባሉት አይሁድ፡ ራሳቸው የሠሩትን ሕገ ኦሪትና በክህደታቸው ምክንያት ከፈጣሪ የተሰጠቻቸውን ጽላተ ኪዳን፡ አክብረው መጠበቁ ስላቃታቸው፡ ኹሉንም በአደራ ተረክበው፡ የአምልኮውን ሥርዓት፡ በአግባቡ የፈጸሙት በመኾናቸው ነው፤ በመጨረሻም፡ የኪዳነ ምሕረቱን ምሥራች፡ ወዲያው፡ በዝግጁነት ተቀብለው፡ በፍጹም ታማኝነት የቀጠሉበት በመኾናቸው ነው።

ደግሞም፡ የእኔ ሴቶች ልጆች፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ እንደወንዶቹ ኹሉ፡ ገና፡ በየእናታቸው ማሕፀን ሲፀነሱ ጀምሮ፡ በመንፈስ ጥምቀትና ቅብዓት፡ የእግዚአብሔርና የእኔ ልጆች፥ የመንግሥታችን ወራሾች ነጋሥያንና አገልጋዮች ካህናት የመኾንን ጸጋ ይቀዳጃሉ። ከዚሁ ብቅዓታቸው የተነሣም፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ ለቤተ ሕዝቡ፥ ለቤተ ምልክናውና ለቤተ ክህነቱ፡ የአገልግሎት አባልነትና ሹመት ባለመብት ናቸው።

ከዚህ በላይ፡ ወንዶቹ ልጆቻችን፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ተብለው፡ በአጤነት፡ የእኛ ተጠሪ አገልጋዮች እንደሚኾኑ ኹሉ፡ እነሆም ሴቶች ልጆቻችን፡ "ሥይምተ እግዚአብሔር" ተብለውና በአጤዪትነት፡ የእኛ ተጠሪ አገልጋዮች ኾነው፡ የመንግሥታችን የአገልግሎት ዘርፎች የኾኑትን ሦስቱንም ቤቶች በበላይነት ይመራሉ።

ከኹሉም ይልቅ፡ '"ናሁ! ድንግል ትፀንስ፤ ወትወልድ ወልደ፤ ወትሰምዮ ስሞ፡ 'አማኑኤል!' ዘበትርጓሜሁ፡ 'እግዚአብሔር ምስሌነ'።

"እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፤ ስሙንም፡ 'አማኑኤል!' ብላ ትጠራዋለች፤ ትርጓሜውም፡ 'እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር ነው!' የሚል ትርጉም ያለው ነው።" ተብሎ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፤ በነቢይ የተነገረውን ቃል፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም ልጆቹ፡ አምነውበት፡ ስለመፈጸሙ፡ በተስፋ ይጠብቁት ነበር።

ይህ ብቻ ሳይኾን፡ ከእኔ፡ ከኢትዮጵያዊቱ ድንግል እንደሚወለድ፡ በእውነትና በመንፈስ አምልኳቸው ስለተረዱ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የአዜነቱ ዙፋን ላይ የምትቀመጠው ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ ምንጊዜም፡ በድንግልናዋ ጸንታ መቆየት ያለባት እንደነበረ፡ ይህ መለኮታዊ እውነታ፡ ቀደም ብሎ፡ በማክዳ፥ በመጨረሻም፡ በእኔ፡ እውን ኾኖ ተረጋግጧል።

በብሉያቱ፡ 'ንግሥተ ሳባ"፤ በልጇ በወዳጇ ቃል ደግሞ፡ "ንግሥተ ዓዜብ" የተባለችው፡ ምዝላቴ፡ ማክዳም፡ ድንግልናዋን፡ በዳዊት ልጅ፡ በሰሎሞን ያስገሠችው፡ በፈጣሪዋ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ እኔን ያስገኘውን፡ የዳዊትን የቃል ኪዳን ዘር፥ እንዲሁም፡ የእኔና የልጇ የወዳጇ አርአያ የኾነችውን፡ የሙሴን ጽላተ ኪዳን፡ ወደኢትዮጵያ ለማምጣት መኾኑ፡ በትንቢቱ ፍጻሜ ተመስክሯል።

ማክዳም፡ እስከመጨረሻዋ፡ በድንግልናዋ ጸንታ ለመኖርዋ፡ ባል ሳታገባ፥ ሌላም ልጅ ሳትወልድ፡ ዙፋንዋን፡ ለአንድ የቃል ኪዳን ልጅዋ፡ ለምኒልክ አስረክባ፡ እንደጥንታዊው ሥርዓት፡ ወደብሕትውና ሕይወት መግባቷ፡ የዚህ እውነታ ማስረጃ ነው። (ኢሳ. ፯፥ ፲፬። ማቴ. ፩፥ ፳፪-፳፫።)

በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ ዘንድ፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ፡ እስከማክዳ፥ እስከእኔም፥ ከዚያም፡ እስከሕንደኬና እስከቅርባችሁ ዘውዲቱ ምኒልክ፥ እስካኹኑም ዘመን ድረስ፡ በእኔ ዘለዓለማዊነት፡ ጸንቶና ተጠብቆ፥ ተከብሮና ተቀድሶ የኖረው፥ ዛሬም ያለው፡ ይህ መለኮታዊ ሥርዓት፡ ወደፊትም፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ ይቀጥላል እንጂ አይቋረጥም።

ይህ እውነታ፥ የልጇ የወዳጇ ሐዋርያ የኾነው ጳውሎስም፡ በዘመኑ፡ አረማውያን ለኾኑ ወገኖች የሰጠው፡ ያ መመሪያ፡ በእኔዎቹ፡ በኢትዮጵያ ሴቶች ልጆቼ ላይ የማይጸና መኾኑን፡ ከእነዚሁ ልጆቼ መካከል፡ አንዲቱ በኾነችው፡ በቅኔው ባለሙያ በገላነሽ የአገልግሎት ሕይወት ታይቷል።

ይኸውም፡ የገላነሽ ወላጅ፡ ቄሰ ገበዝ ሓዲስ ኪዳናት፡ በቤተ ክርስቲያን፡ "በታቦርሂ አመ ቀነጸ መለኮትከ ፈረስ፤

መለኮትህ ፈረስ፡ በታቦር ተራራ በዘለለ ጊዜ፡" ብሎ፡ ከሥርዓተ ቅዳሴው በኋላ፡ የሚቀርበውን ቅኔውን ገና ሲጀምር፡ በድንገት፡ አንዳች ድምፅ፡ ተሰማ! ያም የኾነው፡ እንዲህ ነበር፡-

እዚያው፡ በሴቶች መቆሚያ፡ በእናቷ ዕቅፍ ተቀምጣ የነበረችው፡ የስምንት ዓመቷ ሕፃን ልጅ ገላነሽ ሓዲስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ፣ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ኹኔታም፡ ከተቀመጠችበት ተነሥታ፡ **"ኢክህሉ ስሂቦቶ፡ ሙሴ ወኤልያስ።**

**ሙሴና ኤልያስ ሊስቡት አልቻሉም።"** ብላ፡ በጉባኤ መካከል፡ ቅኔውን፡ ከአባቷ ነጥቃ፡ መወድሱን ጨረሰችው።

ወላጇም፡ አከታትሎ፡ **"ወእንዘ ትትናገሪ ዘንተ፡ በአድኅኖ ክሳድ ወርእስ፣ በከመ አነ ሰማዕኩኪ፡ ኢይስማዕኪ ጳውሎስ!**

**"እኔ፡ በወላጅነቴ እንደሰማሁሽ፡ ይህን ስትናገሪ፡ ጳውሎስ እንዳይሰማሽ!"** ብሎ ቢቀኝም፡ የገላነሽን የንጥቂያ ዘረፋ አጽድቆ፡ ለቅኔ ተቀባዩ፡ እዚያው ጉባኤው መካከል፡ "አዚምላት!" ብሎ፡ እንዲዜምላት ማድረጉ፡ ጳውሎስ፡ በመልእክቱ፡ **"ሴቶች፡ በጉባኤ መካከል ገብተው፡ እንዳያስተምሩ!"** ብሎ የተናገረው ቃል፡ በእርሷ፡ በኪዳናዊቷ ኢትዮጵያዊት ልጁ፡ በገላንሽ ላይ ሊጸና እንደማይችል፡ ወላጇ ቄሰ ገበዝ ሓዲስ፡ በትክክል የተረዳ መኾኑን ያረጋግጣል።

የአዲስ ኪዳኑ ዘመን ሴቶች ዜና መዋዕል ከተወሳ ዘንድ፡ እዚህ ላይ፡ የእነማርያም መግደላዊትን ዝክረ ነገር ማንሣት አግባብ ይኾናል። በዚህ ረገድ፡ የልጁን የወዳጁን ማንነትና ትምህርቱን በቀላሉና በእውነት፡ ፈጥነው በመቀበል፡ አምነውበት ሊከተሉት የቻሉት፥ ሓዋርያው ኾነው ለመመረጥም ቢኾን፡ ከወንዶቹ ይልቅ፡ በቅድሚያ፡ በቅተው የተገኙት፡ ሴቶች ልጆቹ መኾናቸው፡ በግልጽ ይታወቃል።

ከወንጌላዊው ዮሓንስ በቀር፡ በልጁ በወዳጁ፡ የመስቀል መከራው ጊዜ፡ ከእኔ ሳይለዩ፡ በዕለተ ዓርብ ምሽት፡ እስከመቃብሩ ድረስ የሸኙት እነርሱው ናቸው። በሰንበትም፡ እርሱ፡ በመቃብር፥ እነርሱም፡ በቤት ካረፉ በኋላ፡ በልጁ በወዳጁ ትንሣኤ፡ ለዘለዓለማዊነት በበቃችው፡ በአንዲቷ የእግዚአብሔር ሰንበት፡ የመጀመሪያ ቀን ማለዳ፡ ለእርሱ ካላቸው፡ ፍጹም ፍቅር የተነሣ፡ ወደመቃብሩ ኼደው፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ሕያዉን ልጁን ወዳጁን፡ ከወንዶቹ ሓዋርያት በፊት፡ የትንሣኤውን ምሥራች፡ አስቀድመው ከመላእክት፥ ቀጥለውም፡ ራሱን፡ ልጁን ወዳጁን፡ በትንሣኤ አካሉ በማየትና በማነጋገር፡ ከእርሱ የሰሙ፥ እየራሳቸውንም፡ ለትንሣኤው ብሥራት ያበቁ፡ እነዚሁ ሴቶች ልጆቹ ናቸው።

በመጨረሻም፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው፡ ልጁ ወዳጁ፡ **"በሓክን! ኢትፍርሃ! ሑራ! ንግራሆሙ ለአኀውየ፡ ከመ ይሑሩ ገሊላ፤ ወበህየ ይሬእዩኒ።"**

**"ደስ ይበላችሁ! አይዟችሁ አትፍሩ! ወደገሊላ ይኼዱ ዘንድ፡ ለወንድሞቼ ንገሩዋቸው! በዚያም ያዩኛል።"** ብሎ፡ ከወንዶቹ ሓዋርያት በፊት፡ ምሥራቹን፡ በዐዋጅ እንዲናገሩ፡ በልጁ በወዳጁ ቃል የታዘዙት፡ ማርያም መግደላዊትና ሌሎቹ ሴቶች ልጆቹ ናቸው። (ማቴ. ፳፰፥፩-፲።

ወንዶቹ፡ ሓዋርያት ግን፡ ትንሣኤውን በፍጹም እምነት ተቀብለው ለማመን ካለመቻላቸውና ሰቃዮቹን አይሁድን፡ በጽኑ ከመፍራታቸው የተነሣ፡ በዝግ ቤት ተሰብስበው ስለነበረ፡ ልጄ ወዳጄ፡ ራሱ፡ በመካከላቸው ተገኝቶ፡ "ሰላም ለክሙ!

"ሰላም ለእናንተ ይኹን!" እስካላቸው ድረስ፡ በእኒሁ፡ ሴቶች ልጆቼ አንደበት እንዲሰሙት ኾኖ የመጣላቸውን፡ ያንኑም፡ የትንሣኤውን ምሥራች ዜና እንዳላመኗቸው፡ በተጻፈላችሁ ቃል ታውቁታላችሁ።

ከልጄ ከወዳጄ ትንሣኤ በኋላ፡ ስለዚችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ሴቶቹ ልጆቼ፡ ከልጄ ከወዳጄ ሰምተው በተቀበሉት እምነታቸው፡ ጸንተው የቀጠሉበት ሲኾን፡ ወንዶቹ ሓዋርያት ግን፡ እስከአርባኛው የዕርገቱ ቀን ድረስ፡ ልጄ ወዳጄ፡ ስለዚችው መንግሥታችን እያስረዳቸው የሰነበተ ቢኾንም፡ እነርሱ ግን፡ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ፡ በጸጋው እስካሳመናቸው፡ እስከበዓለ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ድረስ፡ ሳያምኑ መቆየታቸውን ዝክረ ነገሩን፡ ይኸው፡ እስከዛሬ ትናገሩታላችሁ።

ታዲያ! በዚህ ረገድ፡ ለሓዋርያነት የሚያበቃው፡ የሃይማኖትና የምግባር መሥፈርት፡ ከወንዶቹ ሓዋርያት ይልቅ፡ ወደሴቶቹ ልጆቼ ያመዘነ ሲኾን፡ በኦሪታዊው የመርገምና የርኵሰት ቀምበራችሁ እያሳበባችሁ፡ እንዲህ ያሉትን ሴቶች ልጆቼን፡ የእኔንና የልጄን፡ የቅዱስ ሥጋና የክቡር ደም ቍርባናችንን እንኳ እንዳይሳተፉ ከልክላችሁ፡ ከምታሠቃዩዋቸው በላይ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ውስጥ፡ በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊዉ፡ የክህነትና የሓዋርያነት አገልግሎት፡ በምንም ዓይነት መልኩና ይዘቱ፡ እንዳይካፈሉ፥ ነገር ግን፡ ለዝንተ ዓለም፡ ለክፋቱ አበጋዝ፡ ለዲያብሎስ አገልጋይነት አሳልፋችሁ ሰጥታችኋቸው፡ የምትገኙ አይደለምን? አዎን! ነው።

ከወንዶች ልጆቼ መካከል፡ አብዛኛዎቻችሁ፡ በሴቶች ልጆቼ ላይ እያደረሳችሁት ስላለው ጥቃትና እየፈጸማችሁት ስላለው ጥፋት፡ ይህን ኹሉ ካልሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ከሴቶች ልጆቼ መካከል፡ በወንዶች ልጆቼ ላይ እያደረሳችሁት ስላለው ጥቃትና እየፈጸማችሁት ስላለው ጥፋት፡ እስኪ በጥቂቱና በማጠቃለል ልናገር!

ይኸውም፡ ከሴቶች ልጆቼ መካከል፡ በእየራሳችሁ ፍላጎትና ምርጫ፥ ውሳኔና ግብር፡ ራሷ፡ የክፋቱ ምንጭ ኾና፥ "እባብ፥ ዘንዶ፥ ዐውሬ፥ ሰይጣን" በሚሉ ስያሜዎች ከሚታወቀው፡ ከሓሰቱ አባት፡ ከዲያብሎስ ጋር፡ ዐባሪ ተባባሪ፥ እንዲያውም፡ ማደሪያው እስከመኾን የደረሰችውን፡ የመጀመሪያዋን ሔዋን መስላችሁ፥ ወይም፡ ኾናችሁ የምትገኙ እንዳላችሁ፡ ኹላችሁም ታውቃላችሁ።

እንዲህ ኾናችሁ በምትገኙበት ጊዜ፡ በወንዶች ልጆቼና በጾታ ወገኖቻችሁ፥ በራሳችሁም ላይ ብቻ ሳይኾን፡ አምላኬና መድኃኒቴ፥ ልጄና ሕይወቴ በኾነው፡ በእግዚአብሔር እና በእኔ ላይ ሳይቀር፡ በአሳብ፥ በንግግርና በድርጊት የምትፈጽሙት፡ እጅግ የረቀቀና በተንኰል የተመረዘ ክፋት፥ በመሠሪነትና በጭካኔም፡ የምታደርሱት አሠቃቂ ጥቃት፡ በርካታ መኾኑ፡ እርግጥ ነው።

ይህንም እውነታ፡ እኔም፥ መንፈስ ቅዱስም፡ በሚበቃ እናውቀዋለን። ሊዘረዝሩት፡ የሚያዳግት፥ ሊናገሩትም የሚሠቀጥጥ ነው። እርሱንም፡ እናንተው፡ ሴቶች ልጆቼ፡ በየውስጣችሁ ስላለ፡ ታውቁታላችሁ። ወንዶች ልጆቼም እንኳ፡ በተለይም፡ የደረሰባቸው ስለሚያውቁት፡ አኹን እዚህ ላይ፡ ልገልጸው አያስፈልግም።

በየግላችሁ ፈቃድና ምርጫ፡ ዕድል ፈንታችሁ፡ ይህ ጽዋ እንዲኾን ያደረጋችሁ ሴቶች ልጆቼ ካላችሁ፡ ኹላችሁም፡ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ንስሓ፡ ጽዋችሁን፡ ወደመልካሙ ዕድል ፈንታ ትመልሱ ዘንድ፡ በእናትነቴ፡ አጥብቄ አሳስባችኋለሁ። እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ በቶሎ ካልመለሳችሁ ግን፡ ፍጻሜያችሁ፡ ያው፡ የሓሰቱና የክፋቱ አበጋዝ ዕድል ዓይነት እንደሚኾን ልትገነዘቡት ይገባል።

ስለዚህ፡ ቀደም ብዬ፡ ስለሴቶች ልጆቼ ጥቃትና በደል፥ ፈተናና መከራ በስፋት ላስተላለፍሁት መልእክቴ፡ ብቁ ትኾኑ ዘንድ፡ በጋብቻና በትዳር፥ በብቸኝነትና በማናቸውም ዓይነት የኑሮ ኹኔታ ላይ ለምትገኙት ኹሉ፡ ለኹላችሁም ሴቶች ልጆቼ፡ አበክሬና አጠንክሬ ሳሳስባችሁ፡ ይህን እላለሁ፡-

እንግዴህ፡ <u>በየግል ሰውነታችሁ ውስጥ ሊኖራችሁ የሚገባው፡ ሃይማኖታዊ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፥ ውሳኔያችሁና ምግባራችሁ፡ የመጨረሻዪቱን ሔዋን፡ መምሰልን ይኹን!</u> እርሷም፡ በእውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ አምልኮና በመንግሥቱ አገልግሎት አማካይነት፡ ከፍጥረት በፊት ኾነ፥ ከፍጥረት በኋላ፡ ራሷን፡ ለመለኮታዊው ሙሽርነት፥ እናትነትና መቅደስነት፡ ልታበቃ የቻለችው፡ ኢትዮጵያ ናት። ያችም፡ እኔ፡ድንግል ማርያም ነኝ።

## ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡
## ስለበዓላቷ አከባበር ያለችው።

አምላኬና መድኃኒቴ፥ ልጄ ወዳጄ እና ሕይወቴ ፍቅሬ እግዚአብሔር፡ የወንድነትንና የሴትነትን አካልና ባሕርይ፡ ጥንቱኑ፡ በቅድስናና በንጽሕና ፈጠረው፤ ኋላ ግን፥ በመካከሉ፡ "በሰው ልጆች" ክፋትና ጥፋት ቢማስንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት፡ በደጋጎቹ ቅዱሳንና ቅዱሳት ወዳጆቹ ኪዳናዊ ሰውነት፡ በሕያውነት አጽንቶ አቆየው፤ በመጨረሻም፡ በእኔ ብቅዓትና በልጄ በወዳጄ ቤዛነት፡፡ ወደነበረበት የቀደመ ንጽሕናውና ቅድስናው መለሰው።

ይኹን እንጂ፡ እናንተ ወንዶቼ፡ የወንድነቱን ቅድስናና ንጽሕና ብቻ፡ በዚህ መልኩ፡ እንደተጠበቀ አድርጋችሁ፥ ያንኑም፡ ለየራሳችሁ አጽንታችሁ፡ የሴትነቱን ወገን ግን፡ ምንም እንዳልተደረገለት፡ በዚያው በማሰነ ኹኔታው እንዳለ በማስመሰል፡ የቀደመውን ግፍና በደል፡ አኹንም፡ በሴቶቹ ልጆቼ ላይ ቀጠላችሁ።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ያን ግፍና በደል፡ በእኔም ላይ ሳይቀር፡ መፈጸማችሁን እንዳላቋረጣችሁ፡ በይፋ ግብራችሁ አረጋግጣችሁ ማሳወቅን ቋሚ ልማድ አደረጋችሁት። እየፈጸማችሁት ስላለው፡ ስለዚሁ በደላችሁና ግፋችሁም፡ ሌላው ኹሉ ይቅርና፡ አኹን፡ በቅርቡ፡ በዚያ ባለፈው፡ በትንሣኤዬ በዓል ያሳያችሁት፡ ግልጽ ጥፋት፡ እስካኹን ሲወሳ ለነበረው ስሑትና የግብዝነት ሥራችሁ፡ ምስክር ኾኖ የሚናገርና የሚያስተዛዝብ፥ የልጄን የወዳጄንም የፍርድ ውሳኔ የሚያስከትል ኾኖ ተገኝቷል።

አዎን! የቀደሙት ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ!

"እንደልጇ ትንሣኤ!" ብለዋል እያላችሁ የምታሰሙትን የዐዋጅ ቃል፡ ልታከብሩ ይገባችሁ ነበር። ነገር ግን፡ ያን የዐዋጅ ቃል እያፈረሳችሁ፡ ትንሣኤዬ፡ በሳምንቱ ቀኖች ውስጥ፡ ረቡዕ፥ ወይም፡ ዓርብ በዋለ ቍጥር፡ እንደልጄ ወዳጄ የትንሣኤ ወራት፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ፍጹም ሓሤት ተደርጎ፡ በደስታ ሊከበር የሚገባውን፡ ይህንኑ የትንሣኤዬን በዓል፡ እንደበዓል ሳይኾን፡ የኀዘን መግለጫ በኾነው፡ በጾም ስትፈጽሙት ኖራችኋል።

ያለፈው፡ የትንሣኤዬ በዓል፡ በዕለተ ዓርብ በመዋሉ፡ በእናንተ በኩል በተፈጸመው፡ በዚያው፡ በተለመደው የጥፋትና የክፋት ድርጊታችሁ፡ ዕድሉ ይኸው ኾኖ ታይቷል።

ይህ፡ እስካኹን፡ ለዘንተ ዓለም፡ ኾን ብላችሁ፡ አላገባብ ስትፈጽሙት የኖራችሁት የተሳሳተ ልማዳችሁ፡ እንደሴቶች ልጆቼ ኹሉ፡ እኔንም፡ የመናቃችሁንና የማዋረዳችሁን ውሳጣዊ ዝንባሌያችሁን የሚያሳይ ማረጋገጫ ለመኾኑ፡ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም። በዚህም፡ የኦሪታውያኑ፡ አይሁድና የግብፃውያኑ ኦርቶዶክሶች፥ የሌሎቹም፡ የልጄ የወዳጄ፥ የእኔም ተቃዋሚዎች ወገኖች መኾናችሁን፡ በይፋ አረጋግጣችኋል፤ የእኔ ልጆች ከመኾንና ከመባልም፡ እየራሳችሁን፡ በፈቃዳችሁ ማግለላችሁን፡ በዚሁ፡ በእየራሳችሁ ግብር መስክራችኋል።

አለዚያ፡ በልቅሶ ቤት፡ እንደማይዘፈን፥ በሠርግ ቤትም እንደማይለቀስ ኹሉ፡ እንዴት አድርጋችሁ ነው፡ በትንሣኤዬ ዕለት፡ በፍጹም የኹለተናዊው ደስታ ሊከበር የሚገባውን፡ ታላቁን የትንሣኤዬን በዓል፡ በጾም እንዲዘከርና የጾም ሥርዓት እንዲካኼድበት የምታደርጉት!? ከራሱ ክብር ይልቅ፡ የእኔ፡ የሙሽራው፥ የእናቱና የመቅደሱ ክብር፡ ቢገለጥ የሚወደው፡ አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፥ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፥ ሕይወቴ ፍቅሬ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ ቅዱሳኑና ቅዱሳቱ ጭምር፡ በዚህ ደስ ይላቸዋል ብላችሁ፡ እንዴት ታስባላችሁ? በዚህ አድራጎታችሁ እኮ፡ "የለም! የአምላክ እናት፡ አንቺ ድንግል ማርያም ኢትዮጵያ፡ አልተነሣሽም!" ብላችሁ፡ ትንሣኤዬን መካዳችሁ አይደለምን? ነው እንጂ።

እግዚአብሔር፡ እንኳንስ፡ እኔን ድንግሊቱን፡ ለእርሱ ሙሽሪትነት በመቀበልና ልጁን፡ ልጄ ወዳጄን በመውለድ፡ ከእርሱ ጋር ተዋሕጄ፡ አንድ የኾንሁትን ቀርቶ፡ እናንተን፥ ሰብአዊ ፍጡራኑ የኾናችሁትን ኹሉ፡ እንድትነሡ አድርጎ የለምን? ካለማመናችሁ የተነሣ፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ ጸጋ፡ በራሳችሁ ጒድለት አጣችሁት እንጂ፡ በመልኩ የፈጠረውንና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን ሰብአዊ ፍጡሩን ኹሉ፡ የትንሣኤው ባለቤት አድርጎት የለምን? አዎን! አድርጎታል።

በእውነት ያመኑበት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቼማ፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በአካለ *ሥጋ ገዝፈው* እያሉ፡ ለሺህ *ዓመቱ የመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ*፡ *እየራሳቸውን አብቅተው፡ "ትንሣኤ ሙታን" ተብሎ፡ የሙታን የኾነውንና ለእነዚያ የተመደበውን፡ ትንሣኤ ዘጉባኤን ሳይጠብቁ፡ የሕያዋን የኾነውን፡ የትንሣኤና የሰንበት ሕይወታቸውን፡ ይኸው፡ እየኖሩት አይደለምን? አዎን! በእውን እየኖሩት ነው።*

*ደግሞስ፡* አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፡ ወሰን በሌለው ቸርነቱ *የለገሠኝን፥ እኔም፡ በዚሁ የልግሥናው ጸጋና ሥልጣን ተጠቅሜ፡ በራሴ የበቃሁበትን* ክብርና ማዕርግ፡ ሕጹጽና ስሑት በኾነው *ሥጋዊ* አስተሳሰባችሁ፡ የራሳችሁን ፍርድ ሰጥታችሁ፡ *"የለም! እርሷ፡ ከፈጣሪ በታች፥ ከፍጡራን በላይ ስለኾነች፡ የፈጣሪ የኾነው፡ ለእርሷ፡ ሊኾን አይገባም!"* ብላችሁ አይደለም? ትንሣኤዬንና ዕርገቴን፡ በዚህ የጾም መልክና ይዘት የምትዘክሩትና "እናከብራለን!" የምትሉት?

እንዲህ ከኾነ፡ *ታዲያ ለምንድር ነው፡ የቀደሙት የቅዱሱ ኪዳን ልጆቼ፡ ኪዳናውያኑ ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያቱ ኢትዮጵያውያት፡ መንፈስ* ቅዱስ የገለጸላቸውንና *ያሳሰባቸውን* ተከትለው፡ እኔን፡ ከአምላኬና ከመድኃኒቴ፥ ከልጄ ከወዳጄ፥ ከሕይወቴና ከፍቅሬ ጋር አስተካክለው፥ እውነተኛ፡ የአምልኮና የምስጋና ቍርባንም አድርገው የሚጸልዩትን፡ እንዲህ የሚለውን ጸሎት፡ እናንተም፡ ዘወትር፡ "ጸሎት" ብላችሁ፡ በዜማ የምታሰሟቸው፡ ከቶ፡ ለምንድር ነው? እስኪ መልሱልኝ!

በሌሊቱ የሰዓታትና በነግሁ፡ የኪዳን ጸሎታችሁ **"መርዓት አብ፤ ወእመ በግዑ። ብኪ ድኅነ ዓለም፤ ወበወልድኪ፡ ኮነ ሰላም!**

**"የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪት፤ 'የእግዚአብሔር በግ' የተባለ ልጁም፡ እናት። ዓለሙ ኹሉ በአንቺ ዳነ፤ በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!"** እያላችሁ የምትዘምሩልኝ፡ ለምንድር ነው!?

በዘወትር ጸሎታችሁ መግቢያስ ላይ፡ **"ንሰግድ ለእግዚአብሔር አብ፣ ንሰግድ ለእግዚአብሔር ወልድ፣ ንሰግድ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ንሰግድ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ። ንሰግድ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።**

**"ለእግዚአብሔር አብ እንሰግዳለን፣ ለእግዚአብሔር ወልድ እንሰግዳለን፣ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንሰግዳለን። አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ድንግል ማርያም እንሰግዳለን። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀል እንሰግዳለን።"** እያላችሁ፡ የአምልኮ ስግደትን የምታቀርቡልኝ፡ ለምንድር ነው!?

ደግሞም፡ "ስብሓት ለእግዚአብሔር አብ፥ ስብሓት ለእግዚአብሔር ወልድ፥ ስብሓት ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ስብሓት ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ። ስብሓት ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ!

"ለእግዚአብሔር አብ፡ ምስጋና ይገባል፥ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ምስጋና ይገባል፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ምስጋና ይገባል። አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ምስጋና ይገባል።" እያላችሁ፡ የምስጋና ቊርባንን የምትሠዉልኝ፡ ለምንድር ነው!?

በመጨረሻም፡ "ነሀብ ሎቱ፡ ስብሓተ፥ ወአኰቴተ፡ ለእግዚአብሔር ልዑል። ወለወላዲቱ ድንግል። ወለመስቀሉ ክቡር! ...ወትረ፡ በኵሉ ጊዜ፥ ወበኵሉ ሰዓት፤ ለዓለመ ዓለም።"

ለልዑል እግዚአብሔር፥ ለድንግል እናቱም፥ ለተከበረ መስቀሉም፡ ዘወትር፡ በየጊዜያቱና በየሰዓቱ ኹሉ፡ የአምልኮ ምስጋናን እናቅርብ! ለዘላለሙ፤ አሜን።" እያላችሁ፡ የምታቀርቡት፡ የአምልኮና የምስጋና ጸሎት፡ ታዲያ! ለምንድር ነው?

እኒህን በመሰሉት፡ የውዳሴና የቅዳሴ ጸሎቶቻችሁ አማካይነት፡ ስለእኔ ምንነትና ማንነት፡ ለእየራሳችሁ፡ ምን ዓይነት ሃይማኖታዊ ምግባርን እየፈጸማችሁ መኾናችሁን፥ ለሌላውም ተከታያችሁ፡ ምን ዓይነት ሃይማኖታዊ መልእክትን እያስተላለፋችሁ መኾናችሁን፡ "አልተረዳችሁም!" ማለት ነውን? ለልዑል እግዚአብሔር፥ ለእኔና ለልጄ ለወዳጄ የተቀደሰ ስቅለቱ፡ የተስተካከለ የአምልኮ ስግደትንና የምስጋና መሥዋዕትን ማቅረባችሁን፡ ማረጋገጣችሁ እኮ ነው።

በዚህ መልክና ይዘት፡ በማኅሌትና በቅዳሴ፥ በሰዓታትና በውዳሴ፡ በዜማና በንባብ፡ ያለማቋረጥ የምታሰሟቸው ቃላት ኹሉ፡ ከሥጋ አካላችሁና ባሕርያችሁ ፈልቀው የሚነገሩና የሚደመጡ እንጂ፡ ከመንፈሳዊው አካላችሁና ባሕርያችሁ አሥርፃችሁ፡ በሃይማኖታዊ ተአማኒነት የምታቀርቧቸው፥ እግዚአብሔር አምላክ የሚፈቅደውና የሚቀበለው፡ እውነተኛው የመንፈስ አምልኳችሁም ፍሬዎች ስላልኾኑ፡ አዎን! የጸሎታችሁን ትክክለኛ ምንነት፡ ለይታችሁና አስተውላችሁ እንኳ ልታውቁት አልተቻላችሁም።

ለአምላኬና ለመድኃኒቴ እግዚአብሔር፡ ምስጋና ይድረሰውና፡ የእርሱ፡ መለኮታዊ ጸጋው፥ ፍቅሩና አንድነቱ፥ የእኔም፡ ረድኤቴ፥ በረከቴና ሰላሜ፡ ለእናንተው ቀረባችሁ እንጂ፡ የልጄ የወዳጄና የእኔ፡ የትንሣኤያችንና የዕርገታችን በዓላት ብቻ ሳይኾኑ፡ የፅንሰታችንና የልደታችን፥ ሌሎቹም የዓመት መታሰቢያዎቻችን ጭምር፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ በሚፈቅደውና በሚቀበለው፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ፡ በእንዴት ያለ ኹለንተናዊ ሥርዓት እየተከበሩ እንዳሉ፡ ልታውቁት ይገባል።

ይኸውም፡ እኒሁ በዓላት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አገልጋይ ልጃችን፡ ኤርምያስና እርሱን የመሰሉት እልፍ አእላፋት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ካህናት ልጆቻችን፡ ዘለዓለማዊውን የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት ከተቀዳጀው ከሰማያውያኑና ከምድራውያኑ ፍጥረታተ ዓለማት ሠራዊት ጋር፡ ኢትዮጵያዊዉን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት ተከትለው፡ ይኸው፡ በአግባቡ መንገድና በትክክኛው ኢትዮጵያዊ ቀናቸው፡ እየተከበሩ፡ ሕያውነታቸውን፡ በገናንነት የመቀጠላቸው ምሥራች ነው።

ስለዚህ፡ እናንተም፡ ልጆቼ ናችሁና፡ አማናዊው የእግዚአብሔር አብ ቸርነት፥ የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅርና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጸጋ፥ በቅዱሱ ኪዳን የምሕረት ዘውድ የተከለለው፡ የእኔም፡ በረከቴና ረድኤቴ ተመልሶ ያድርባችሁ ዘንድ፡ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ ንስሓ አስተካክላችሁና አንጽታችሁ፡ እነዚህኑ በዓሎቻችንን፡ በትክክለኛውና በጥንታዊው ኢትዮጵያዊ ቀናቸው እንድታከብሩዋቸው አሳስባችኋለሁ።

በዓላቱም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡- የእኔና የልጄ የወዳጄ የፅንሰት ዕለታት፡ የእርሱ፡ *ታኅሣሥ ፩ ቀን ሲኾን፥ የእኔ፡ ታኅሣሥ ፲ ቀን ነው።* የኹለታችንም ልደት፥ ደግሞም፡ የፍጥረት ልደትና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ የነጻነት ልደት፥ እንዲሁም፡ አዳምና ሔዋን፡ በአንድ አዳምነት የተፈጠሩበት የልደታቸው ዕለት፡ መስከረም ፩ ቀን ነው። የፍልሰተ ሥጋዬ ዕለት፡ ጥር ፳፩ ቀን ኾኖ፡ የቀደሙት ታማኞች ልጆቼ፡ እንደልጄ እንደወዳጄ ትንሣኤ፡ በእውነተኛው ሥርዓት እንዲከበር የወሰኑት ትንሣኤዬ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን ሲኾን፡ ዕርገቴ፡ መስከረም ፳፩ ቀን ነው።

ከሳምንቱ ቀኖችም ውስጥ፡ በየመልካቸውና በየባሕርያቸው የሚከበሩ፡ ሦስት ዕለታት አሉ። እነዚህም፡- ልጄ ወዳጄ፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በመስቀል ላይ፡ ቤዛ ኾኖ፡ ፍጥረቱን ያዳነባት በመኾኗ፡ በመጀመሪያ፡ ዕለተ ዓርብ ናት። ቀጣይዋም፡ ልጄ ወዳጄ፡ በሥጋው፡ በመቃብር ተኝቶ ያረፈባት፥ በነፍሱም፡ ወደሲዖል ወርዶ፡ ምሥራቹን የሰበከባት፡ ሰንበት ናት። ተከታይዋም፡ ልጄ ወዳጄ፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶባት፡ ለሥጋውያን ሰዎች ተሰጥታ፡ በየሳምንቱ የምትከበረውንና በ፳፬ ሰዓቶች የተወሰነችውን፡ ይህችኑ፡ አንዲቷን ሰንበት፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ እግዚአብሔር ወዳረፈባትና ጽንፍ ወደሌላት፡ ወደአማናዊቷ ሰንበትነቷ ስላሻገራት፡ ይህችው ሰንበት፡ ለዘለዓለማዊ ህልውናዋ የበቃችበት፡ ዕለተ እሑድ ናት።

ይህ፡ የ፯ሺ፭፻፯ (የሰባት ሽህ አምስት መቶ ስድስት) ዓመታት ዕድሜ ያለው ሥርዓት፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ በዓለም ያሉ የሰው ዘር ወገኖችና ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና አገዛዞች ኹሉ፡ ከጥንት ጀምረው፡ ፍጹም ነጻነትንና ሰላምን፥ ፍቅርንና ደስታን፥ ብልጽግናንና ዕረፍትን አግኝተው፡ እንዴት፡ በስምምነትና በመግባባት፥ በመተዛዘንና በመረዳዳት፡ በመልካም ሕይወት መኖር እንደሚችሉ፡ አስረግጦና አጉልቶ አሳይቷል፤ አኹንም፡ እያሳየ ነው፤ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም፡ ሲያሳይ ይኖራል።

## ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡

## ይህ ቃለ ዐዋዲ፡ በቀኑ ሳይታዋጅ የዘገየበትን ምክንያት ስትገልጽ።

ይህ ቃለ ዐዋዲ፡ ሊታወጅ ይገባ የነበረው፡ የትንሣኤዩን ዓመታዊ ዝክር ባሰባችሁበትና በዓሉን ባከበራችሁበት፡ ባለፈው፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት ነበር። ነገር ግን፡ እንዲህ ሊዘገይ ግድ የኾነው፡ በአገልጋያችን በኤርምያስ በኩል፡ በተፈጠረ ምክንያት መኾኑን፡ እገልጽላችሁ ዘንድ፡ አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

ይኸውም፡ እንዳለፉት ጊዜያት ኹሉ፡ በሱባኤው መካከል፡ ለእርሱ በደረሰው፡ በዚህ፡ በአኹኑ፡ መልእክቴ ውስጥ፡ እርሱን፡ ኤርምያስን በሚመለከት፡ የተናገርሁት ቃል ስላለ፡ በተለይ፡ ያ ቃሌ፡ "በዐዋጁ ውስጥ መካተቱ ቢቀር፥ ወይም፡ ቢቆይ ይሻላል!" ሲል፡ ከእርሱ ከቀረበልኝ አሳብ የተነሣ፡ የተፈጠረው ምክንያት ነው።

እኔም፡ ያን አሳቡን ባለመቀበል፡ **"ለሚያምኑትም ኾነ፡ ለማያምኑት ወገኖች፡ መፋረጃ ይኾን ዘንድ፡ ጊዜውን ጠብቆ የተነገረ መለኮታዊ ቃል ስለኾነ፡ መገለጹ ተገቢ ነውና፡ እርሱን ጨምሮ፡ መልእክቴ በሙሉ፡ እንደተለመደው በዐዋጅ ይተላለፍ!"** ብዬ፡ መመርያዬን ሰጠሁት። እርሱ ግን፡ ያን መመሪያዬን፡ አኹንም፡ እንደገና፡ በሰበብ አስባብ አቆይቶት ሳለ፡ በመጨረሻ፡ በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ መንገድ፡ በደረሰው ልዩ ማሳሰቢያ፡ ስሕተቱን ተረድቶ፥ በፈጸመውም ጥፋት፡ ንስሓ ገብቶ፡ መመሪያዬን ተቀበለ። መለኮታዊውም መልእክት፡ ያ፡ "በዐዋጁ ውስጥ መካተቱ ቢቀር፥ ወይም፡ ቢቆይ ይሻላል!" ያለው ቃሌ ታክሎበት፡ ይኸው፡ በቃለ ዐዋዲው ላይ፡ በሙሉ ሠፍሮ ሊታወጅ በቃ!

ለዚህ የዐዋጅ መልእክቴ መዘግየት፡ ምክንያቱ፡ ምን እንደኾነ ታውቁት ዘንድ፡ ይህን ያህል ከገለጽሁላችሁ፡ ኤርምያስ፡ ከዐዋጁ ለይቶ ሊያስቀረው የነበረውንና እርሱን በሚመለከት የተናገርሁትን፡ ያን ቃሌን፡ ለመጨረሻው መደምደሚያነት አቆይቼ፡ ለአኹኑ፡ መለኮታዊው መልእክት፡ ያንኑ ቃሌን ጭምር እንደያዘ፡ በቃለ ዐዋዲው ላይ፡ በሙሉ ሠፍሮ እንዲታወጅ ያደረገውን፡ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ፡ ልጆቼ ኹሉ፥ በተለይም፡ ኪዳናውያኑ ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያቱ ኢትዮጵያውያት፡ በቅድሚያ ትመለከቱት ዘንድ፡ እንደሚከተለው ቀርቦላችኋል፡-

<u>ከአገልግሎት ባልደረቦቼ መካከል፡ ኹለቱ፡ ኪዳናዊ ኃይለ-ማርያምና ኪዳናዊት ኀሪተ ገብርኤል፡ በጥቅምት ፳፰ ቀን፥ ፳፻፯ ዓ. ም. ለኤርምያስ የጻፉለት፡ እ-ጦማር፡-</u>

የተወደድህና የተከበርህ ኪዳናዊ ወንድሜና የክህነት ባልደረባዬ ጋሽዬ! (ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ!)

በእግዚአብሔር ሰላም፡ ደኅና እንደኾንህ አምናለሁ፤ እኔም፡ እግዚአብሔር ይመስገን! ደኅና ነኝ።

እኔና ጓሩት በስልክ ውይይታችን ላይ፡ "የድንግል ማርያም ክብርዋ፡ እስከየት ድረስ ነው?" የሚለውን ቊም ነገር እያወሳን ነበር፤ በውውይታችን ውስጥም፡ ቅዱስ ያሬድ፡ በድጓው የዜማ ድርሰቱ፡ **"ወይቤላ እግዚአብሔር ለማርያም፡- 'አዝማንየ አዝማንኪ፣ አምጣንየ አምጣንኪ፣ ማርያም ሐቀፍኪዮ ወአነ ዮም ወለድክዎ!'"** የሚል አብነት ይገኛል እኮ ብለን፡ ስንተክዝ ነበር፤ አያይዘንም፡ ታዲያ፡ ይህ ቅኔያዊ ምስጋናና በረከት፡ በኢትዮጵያኛ ቋንቋችን በደንብ ተተርጕሞ፡ በፌስቡኩ መድረካችን ላይ ቢወጣ፡ ብዙዎችን ይጠቅማል ብለን አሰብን።

እናማ፡ አንተ፡ ይህን፡ የግእዙን አብነት፡ ወደኢትዮጵያኛችን ብትመልሰው፡ ምንድር ይመስልሃል?

አክባሪህና ያገልግሎት ባልደረባህ፣ ኃይለ-ማርያም።

## <u>አገልጋያችን ኤርምያስ፡ ለዚህ ደብዳቤ፡</u>
## <u>በጥቅምት ፳፯ ቀን፥ ፳፻፯ ዓ. ም. በእ-ጦማር፡ የሰጠው ምላሽ፡-</u>

የተከበርህና የተወደድህ፡ ኪዳናዊ ወንድሜና ክህነታዊ ባልደረባዬ ኃይለ ማርያም!

መንፈስ ቅዱስ፡ በአንተና በጓሩት አድሮ፡ ያሳሰባችሁን፡ ይህን የእመቤታችንን ነገር ሳነብበው፡ አስደነገጠኝ፤ ቀጥሎም፡ ለጊዜው፡ ማመን እስኪሚያዳግተኝ ድረስ፡ በእጅጉ አስገረመኝ፤ በመጨረሻም በታላቅ ሓሤት አስደነቀኝ። የዚህም ምክንያት፡-

፩ኛ፡ ይህ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት ጥቅስ፡ እስካኹን፡ ስለእመቤታችን፡ ስናስተላልፈው የቆየነውን፡ የመልእክቶቻችንን ቁም ነገር፡ በጽኑ ማስረጃነቱ፡ የሚያጸናልን በመኾኑ ነው።

፪ኛ፡ እውነተኛው፡ የእመቤታችን ዝክረ ነገር፡ አኹን፡ እናንተ ባቀረባችሁት፡ በዚህ፡ በቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት ጥቅስ ብቻ የተወሰነ ሳይኾን፡ እጅግ ጥልቅና ምጡቅ፥ ረቂቅና ሰፊ በኾነ መልክና ይዘት፡ መንፈስ ቅዱስ ባወቀ፡ በእኔ በአገልጋይዋ እጅ፡ ስለእርሷ የተዘጋጀውን የአዋጅ መልእክት፡ እንደተለመደው፡ በጎዋው አውታር ሰሌዳዎቻችንና መድረኮቻችን ላይ ይፋ ይወጣ ዘንድ ልልክላችሁ፡ እያጠናቀቅሁት የምገኝ በመኾኔ ነው።

ይህን፡ በእኔ ላይ የደረሰውን ድንገተኛና አጥለቅላቂ ስሜት፡ ወደፊት፡ ራሱን መልእክቱን በምትመለከቱበት ጊዜ፡ እንደምትጋሩኝ አምናለሁ።

መንፈስ ቅዱስ፡ በእናንተ ላይ ዐድሮ፡ ይህን ተአምር የፈጸመውም ያለምክንያት እንዳልኾነ፡ እኔ የተገነዘብሁትን ያህል፡ እናንተም፡ የክህነት ባልደረቦቼ የኾናችሁት፡ ኪዳናውያን ወንድሞቼና ኪዳናውያት እኅቶቼ፡ ይህንኑ ምክንያት ታውቁት ዘንድ እንድገልጽላችሁ፡ ራሱ፡ ኹኔታው እንዳስገደደኝ ልሸሽጋችሁ አልፈልግም።

ይኸውም፡ እንደመጀመሪያው አዋጅ ኹሉ፡ በሱባኤዋ ሰሙናት ተዘጋጅቶ፡ በበዓለ ትንሣኤዋ ዕለት፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፯ ዓ. ም. በአዋጅ ሊወጣ የሚገባው፡ ይህ የእርሷ መልእክት፡ እስካኹን የዘገየው፡ በእኔ ዳተኝነት ምክንያት መኾኑ ነው።

ለዚያ ዳተኝነት፡ መነሻ የኾነኝን፡ ያን ምክንያት ግን፡ አኹን አልገልጽላችሁም። ለዐዋጁ መዘግየት፡ ያ፡ የእኔ ምክንያትነት፡ እንዴትና በምን መልክ እንደኾነ፡ ወደፊት፡ ቢገለጽም፥ ባይገለጽም፡ እዚያው፡ የመልእክቱ ዐዋጅ ውስጥ ታገኙታላችሁ። እዚህ ላይ፡ ለአዋጁ መዘግየት፡ ምክንያቱ፡ እኔ መኾኔን ማወቁ ብቻ ይበቃችኋል።

አኹን፡ በእናንተ አማካይነት፡ ለእኔ የደረሰኝ፡ የመንፈስ ቅዱስ መመሪያ፡ "በቃህ! የአዋጁን መውጣት፡ እንግዴህ ወዲህ አታዘግይ!" ነው።

ስለዚህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መፈጸም ስላለበት፡ በእርሱ ቸርነትና ኃይል፡ ዝግጅቱን አጠናቅቄ፡ የመልእክቱን አዋጅ እልክላችኋለሁ።

ይህ፡ የቅዱስ ያሬድ፡ ቅኔያዊ የዜማ ድርሰት፡ እስከዐዋጁ መውጣት ድረስ ከሚቆይ፡ "አኹኑኑ ቢወጣ ይሻላል!" የምትሉ ከኾነ፡ ትርጉሙን፡ እንደሚከተለው ልኬልሃለሁ።

**"ወይቤላ እግዚአብሔር ለማርያም፡- 'አዝማንየ አዝማንኪ፤ አምጣንየ አምጣንኪ፤ ማርያም ሐቀፍኪዮ ወአነ ዮም ወለድክዎ!'"**

**«እግዚአብሔርም፡ ማርያምን እንዲህ አላት፡- "የባሕርዩ ዘመን፡ ዘመንሽ ነው፤ የአካሌም መጠን፡ መጠንሽ ነው። ስለዚህ፡ እኔ ዛሬ የወለድሁትን ልጄን፡ አንቺ ማርያም አቀፍሽው!"»**

በአገልግሎታችን የማይለየን መንፈስ ቅዱስ ይመስገን!
ኪዳናዊ ወንድምህና የአገልግሎት ባልደረባህ፡
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ።

## ድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያ፡
## የዛሬ አገልጋይዋን ኤርምያስን በሚመለከት የተናገረችው።

አገልጋያችን ኤርምያስ፡ በልጅነት ዕድሜው፡ የመንግሥታችን ዋናው ዘርፍ በኾነው፡ በቤተ ሕዝቡ ውስጥ፡ ልዩ ልዩ ማኅበሮችን አቋቁሞ ከማካኼድና አደራጅቶ ከማገልገል ጋር፡ ለኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር መሥራችነትና የመጀመሪያ ዋና ጸሓፊነት፥ ለአዲስ አባባ መናገሻ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባልነት፥ ለሕዝባዊው፡ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልነት፥ ከዚያም ጋር፡ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤትን ለሚያካትተው ለኹለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ጉባኤ ሙሴነትና ጄኔቫ ለሚገኘው፡ የዓለም አህጉር ብሔራውያን ሸንጎዎች፡ የኢትዮጵያው ሸንጎ ሊቀመንበርነት እንዲመረጥና እንዲያገለግል ያደረግነው፡ እኛ ነን።

በቤተ ምልክናው የመንግሥታችን ዘርፍ ደግሞ፡ በማስታወቂያና በንግድ፥ በምርት ግብርናና በዕቅድ የምልክና መሥሪያ ቤቶች፥ እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድንና የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤትን በመሰሉ ድርጅቶች ውስጥ እየተዘዋወረ በኃላፊነት ሥልጣን እየተሾመ ከማገልገሉ ጋር፡ ለአኵስም አውራጃ አስተዳዳሪነትና ለፍርድ ቤቱ ሊቀ ምርፋቅነት፥ እንዲሁም፡ ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልነት ተሠይሞ እንዲያገለግል ያደረግነውም፡ እኛ ነን።

በመጨረሻም፡ በመንግሥታችን፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ፡ ለቅስናውና ለበርካታዎቹ የመምሪያ ኀላፊነቶች፥ ለአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነቱና ከዚያም፡ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅነቱ ሹመት አብቅተን፡ ተልእኮውን እንዲፈጽም ያደረግነው፡ እኛ ነን።

ይህ ብቻ አይደለም፡ ለአንድ ሱባኤ (ለሰባት ዓመታት) ተወስኖ እንዲቆይበትና በዚያም፡ አስፈላጊውን የተልእኮ አገልግሎቱን፡ ለወገኖቹ እንዲያበረክትላቸው ብለን፡ ወደደርግ እሥር ቤት የላክነው፥ በዚያም፡ እንዲያበረክት፡ የወሰንለት የአገልግሎት ጊዜ ሲፈጸም፥ ሕዝቤ፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ እየፈጸመ ያለውን፡ ክህደትና ዓመፅ፥ አመንዝራነትና ልዩ ልዩ ኃጢአት፡ በእሥር ቤቱ ውስጥ በነበሩት፡ የእሥራት ባልደረቦቹ ሕይወት ላይ ሳይቀር፡ የቱን ያህል የጸና እንደኾነ እንዲገነዘብ ካስቻልነው በኋላ፡ የእርሱንና የቤተሰቡን ደኅንነት፡ በደርግ አማካይነት ከማስጠበቅ በቀር፡ አንዳችም ጉዳት እንዳያገኘው በመጠንቀቅ፡ ከእሥር እንዲፈታ ያደረግነው እኛ ነን።

ከእሥር ከተፈታ ጀምሮም፡ ባገር ውስጥም ኾነ፡ በውጭ አህጉር፡ እስከዚች አፍታ ድረስ ተልእኮውን እንዲያካኺድ ያደረግነው፡ እኛ ነን።

አዎን! ይኸው፡ አገልጋይ ልጃችን ኤርምያስ፡ በዚያ የልጅነት ዕድሜው፡ የመንግሥታችን የአገልግሎት ዘርፎች በኾኑት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ውስጥ፡ ኃላፊነቱንና ሥልጣኑን እንዲይዝ፥ በዚያ ኃላፊነቱና ሥልጣኑም፡ ተገቢውን ኹሉ የማድረግ ኃይሉን እየለገሥነው፡ መልእክታችንን ወደእናንተ በማድረስ፥ እናንተም፡ ሰምታችሁ ለመፈጸም እንድትበቁ ለማስቻል በመጣር፡ እኛንም፥ እናንተንም እንዲያገለግል፡ ለየቦታው የሠየምነውንና የመደብነው፡ እኛ ነን።

እርሱም ቢኾን፡ ለዚህ ተልእኮ፡ ራሱን ያበቃው፥ እኛም ያበቃነው፡ እንዲያው አይደለም። አምላኬና መድኃኒቴ፡ ቸሩ እግዚአብሔር፡ ከጥንቱ የሠራውን፡ የማይናወጸውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት፡ ኤርምያስም፡ በመከተሉና ለማንኛችሁም፡ በተፈጥሮአችሁ፡ በተሰጣችሁ አምላካዊ ጸጋ፡ በመጠቀሙ ነው፤ ይህንም እውነታ፡ በራሱ ሃይማኖታዊ ምግባር አሳይቷል።

ይኸውም፡ ራሱን ብቻ ሳይኾን፡ በአኹኑ የመጨረሻ ዘመን የምትኖሩትን፡ እናንተን፡ እያንዳንዳችሁንና ኹላችሁንም ሊጠቅም፡ በዚያ፡ በአምላካዊው ጸጋ አማካይነት በተቀዳጀው፡ በራሱ የግል ፈቃዱና ፍላጎቱ፡ እኛን መውደዱና መምረጡ፥ ጥሪያችንንም ተቀብሎ፡ ተልእኮውን መፈጸሙ ነው።

በእውቀቱና በትምህርቱም ረገድ፡ ስሕተትና ጒድለት ከመላበት፡ ከሰዎች ካገኘው ይልቅ፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በተፈጥሮ ጸጋ የተቀዳጀውን፡ እውነተኛና ምሉዕ የኾነውን፡ እግዚአብሔራዊዉን መርጦ ስለያዘና ስለተከተለ ነው።

እኛም፡ ለዚህ ተልእኮ የመረጥነው፡ በዚሁ ምርጫው ሲኾን፡ እናንተ ግን፡ አብዛኛዎቻችሁ፡ እርሱ፡ ከእኛ በተሰጠው ተልእኮው፡ በመልእክተኛነቱ ያበረከተላችሁን አገልግሎት ለመቀበል፡ ፈቃደኞች አልኾናችሁም። የዚህ ምክንያቱ፡ ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ ለማንም የሚያዳግት አይደለም። ምርጫችሁ፡ እኛን ሳይኾን፡ ሌላውን ባዕዱን፥ ተቃራኒያችንን መኾኑን፡ ይኸው፡ በጥፋታችሁ ፍሬ፡ በገሃድ እየታየ ነው።

ለመኾኑ፡ ነገሩን፡ በሚዛናዊው ኅሊናችሁ አስተውላችሁ ስትመለከቱት፡ በእየራሳችሁ ክፉ ምርጫና የእምቢተኛነታችሁ ዐመፅ ምክንያት፡ ራሳችሁ፡ በራሳችሁ ባመጣችሁት፡ በአኹኑ የፈተናችሁና የመከራችሁ ጊዜ፡ በእኛ በኩል፡ ቅዱሱን ኪዳናችንን ጠብቀን፡ እናንተን፡ የምንወድዳችሁን ልጆቻችንን፡ ወደንስሓ ለመመለስ፡ የራሳችሁ ከኾነው፥ በአገልግሎቱም ከምታውቁት፡ ከዚሁ ኢትዮጵያዊ አገልጋያችን የተሻለ፡ ማንን እንድንልክላችሁ ኖርዋል ትፈልጉ የነበረው?

እርሱን የምታውቁትን ትታችሁ፡ እስከዛሬ፡ የሰማችሁትና የተቀበላችሁት፥ የተከተላችሁትም፡ ምንነታቸውንና ማንነታቸውን፡ ፈጽማችሁ የማታውቋቸውን ብቻ አይደለምን? በዚህም፡ ምን ያህል እንደተጠቀማችሁ፥ ወይም፡ እንደተጎዳችሁ፡ አመዛዝናችሁና ለይታችሁ ለመረዳት፥ ለመፍረድም፡ የአርባ ዓመቱ የፍዳ ዘመን፡ ሳይበቃችሁ አይቀርም። የሚያውቁትን መልካሙን ወዳጅ ትቶ፥ የማያውቁትን፡ ክፉውን ጠላት፡ ፈልጎና ወድዶ፥ መርጦና ተከትሎ መጎዳት፡ በእናንተ የተጀመረ፡ እንግዳ ልማድ ስላልኾነ፡ ይህን ያህል ሊያስደንቅ አይችልም፤ ይህን የመሰለው፡ የሰዎች ዝንባሌ፡ ከምዝላቶቼ፡ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ፡ እስከዛሬ፡ በ"ሰው ልጆች" ዘንድ፡ ወግ ኾኖ፡ ሲካኼድና ሲደረግ የኖረ ቋሚ ግብር ነውና።

አዳምና ሔዋን፡ በመልኩ የፈጠራቸውንና መልካሙን ኹሉ አሟልቶ የሰጣቸውን፥ ፍጹም የሚያውቁትን፡ ደግና ተወዳጅ የኾነ ፈጣሪያቸውን፡ በአንድ ጊዜ ትተው፡ ጨርሰው የማያውቁትን፡ ክፉዉን ጠላታቸውን፡ እንዴት፡ በጥቂት አፍታ እንደተቀበሉ፡ ኹሉ የሚያውቀው እውነታ ስለኾነ፡ በዚህ ላይ፡ ብዙ መናገር፡ የሚያስፈልገኝ አይደለም።

ይኸው አገልጋያችን ኤርምያስ፡ በቃልም፥ በጽሑፍም፡ ወደእናንተ ካደረሰው፡ ከመልእክታችን እውነተኛነትና ትክክለኛነት ጋር፡ በተለይ፡ የእኔን ወቀሳ በያዙት፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና፡ Ethiopia: The Classic Case በተባሉት መጻሕፍት፡ የጀርባ ገበታዎች ላይ የሠፈረው፡ ከቀደመው ሥዩማችን፡ ከኃይለ ሥላሴ ጋር በተነሣው ብርሃናዊ ሥዕል ውስጥ፡ ሥዩማችን፡ ይህንኑ አገልጋያችንን፡ ምን እያለው፥ በእጅ ጣቱም፡ ምንን እያመለከተው እንደኾነ አውቃችኋል?

"ብዙ እናስተውላለን!" የምትሉ እናንተ፡ የሥዕሉን እውነተኛ መልእክት ለመረዳት፡ የቱን ያህል ሙከራ እንዳደረጋችሁ የምታውቁት፡ እየራሳችሁ ናችሁ።

ለዚህ ግንዛቤያችሁ ይረዳችሁ ዘንድ፡ አንዳንድ ምልክቶችን ላክልላችሁ እወድዳለሁ። ወደእኛ የጠራነው፡ ይኸው፡ የተቀባው ሥዩማችን፡ በዚያን ጊዜ፡ ይህንኑ ሥዕል፡ በዕለቱ፡ ራሱ፡ የቤተ መንግሥቱ ብርሃናዊ ሥዕል አንሺ፡ እቤቱ ድረስ ወስዶ፡ ለኤርምያስ እንዲሰጠው ማድረጉ፡ አንዱ ምልክት ነው፤ ኹለተኛው ደግሞ፡ ሥዕሉ፡ የእኔን መልእክት በያዙት መጻሕፍት ገበታ ላይ መውጣቱ ሲኾን፡ እነዚህን ምልክቶች፡ ከዋናው፡ ከብርሃናዊው ሥዕል ዝክረ ነገር ጋር ስታያይዙት፡ ቅንብሩ፡ ምን የሚለውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት እንደሚያሳውቃችሁ፡ እናንተው ራሳችሁ፡ አመዛዝናችሁ ልትደርሱበት የምትችሉትና የሚገባችሁ እውነታ ነው።

ልጄ ወዳጄ፡ "**መኑ ይብልዎ ሰብእ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው?**

**እኔን፡ የማርያምን ልጅ፡ ሰዎች፡ ማን ይሉኛል?**" ብሎ፡ ሓዋርያቱን በጠየቃቸው ጊዜ፡ "**ወይቤልዎ፡ 'ቦ፡ እለ ይብሉከ፡ «ዮሓንስሃ መጥምቀ»፤ ወካልአን፡ «ኤልያስሃ»፤ ወመንፈቆሙ፡ «ኤርምያስሃ»፤ ወእመአኮ፡ «አሓዱ እምነቢያት ቀደምት»።**

**«መጥምቁ ዮሓንስ ነው!»፥ ሌሎችም፡ «ኤልያስ ነው!»፥ እኩሌቶቹም፡ «ኤርምያስ ነው»፥ የቀሩትም፡ ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ነህ!" የሚሉህ አሉ፤'**
**አሉት።**"

እንግዲህ፡ ሓዋርያቱ፡ በዚህ መልሳቸው ውስጥ፡ በስም ለይተው የጠቀሷቸው ነቢያት፡ መጥምቁ ዮሓንስ፥ ኤልያስና ኤርምያስ ሲኾኑ፡ በጊዜው፡ በአካለ ሥጋ፡ ዐብሮአቸው የነበረው መጥምቁ ዮሓንስ፡ በኤልያስ መንፈስ የመጣ መኾኑን፡ ልጄ ወዳጄ፡ "**ወእመሰ ትፈቅዱ ትትወከፍዎ፡ ዝ ውእቱ ኤልያስ፡ ዘሀለዎ ይምጻእ፤ ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዐ ለይስማዕ!**

**"ልትቀበሉትስ ብትወድዱ፡ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ፡ ይህ ነው። የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!**" እንዳላቸው ታውቃላችሁ።

ከዚያ በኋላም፡ በደብረ ታቦር ላይ፡ ኤልያስን፡ ከሙሴ ጋር አይተውት፡ ከተራራው ሲወርዱ፡ "**እፎ ይብሉ ጸሓፍት፡ 'ሀለዎ ይምጻእ ኤልያስ ቅድመ'።**

**"እንግዲህ፡ ጻፎች! 'ኤልያስ፡ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል!' ስለምን ይላሉ?**" ብለው በጠየቁት ጊዜ፡ ልጄ ወዳጄ፡ መልሶ፡ "**እወ! ኤልያስ፡ ይቀድም መጺአ፤ ወያስተራትዕ ኵሎ። ወእብለክሙ ባሕቱ፡ ከመ ኤልያስ፡ ወድአ መጽአ፤ ወኢያእመርዎ፤ ወባሕቱ፡ ገብሩ ላዕሌሁ፡ ኵሎ፡ ዘከመ ፈቀዱ።**

**"ኤልያስማ፡ አስቀድሞ ይመጣል፤ ኹሉንም ያቀናል፤ ነገር ግን፡ እላችኋለሁ፡- <u>ኤልያስ፡ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ኹሉ አደረጉበት እንጂ፡ አላወቁትም።</u>**" አላቸው። (ማቴ. ፲፩፥ ፲፬፤ ፲፯፥ ፩-፲፫።)

ስለዚህ፡ የእኔ ልጆች በኾኑት፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ሳይኾን፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" በሚሉት፡ በዛሬዎቹ አይሁድ ዘንድ፡ "ይመጣል!" ተብሎ፡ ገና የሚጠበቀው፡ ነቢይ፡ ኤርምያስ ከኾነ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ እነርሱና የእነርሱን ፈለግ በምትከተሉት፡ በባለሦስት ሺ ዓመታቱ አሪታውያን ዘንድ፡ መጥምቁ ዮሓንስ፡ በኤልያስ መንፈስ እንደመጣ ኹሉ፡ ይኼ የዛሬው አገልጋያችን ኤርምያስም፡ ባታምኑበት እንኳ፡ "ምናልባት፡ በዚያ፡ በቀደመው ኢትዮጵያዊ ነቢይ ኤርምያስ መንፈስ የመጣ ሊኾን ይችል ይኾናል!" ብላችሁ፡ በጥርጣሬና በማመንታትም ቢኾን፡ ተቀብላችሁ ልትሰሙት፡ ለምን አልቻላችሁም?

"አቤሜሌክና ባሮክ" የተባሉ፡ ኢትዮጵያውያን ደቀ መዛሙርት የነበሩትን፡ ያን ታላቁን፡ የብሉዩን ዘመን፡ ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስን፡ በዘመኑ የነበሩት ከሃዲዎች፥ ዓመፀኞና አመንዝሮች አይሁድ እንዳልተቀበሉት ኹሉ፡ እናንተም የዛሬዎቹ ተከታዮቻቸው፡ የዛሬውን አገልጋያችንን ኤርምያስን፡ "አንቀበልህም! አንሰማህም!" ማለታችሁ አይደለምን?

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! እነዚያ የቀደሙት መሰሎቻችሁ፡ እጅግ ተጎዱ እንጂ፡ ምን ተጠቀሙ? ያ ነቢያችን፡ በትንቢታዊ ቃሉ ያላቸውና የነገራቸው፥ በጽሕፈትም የላከላቸው ምክርና ማስጠንቀቂያ፡ አንድ ሳይቀር፡ እንደደረሰባቸውና እንደተፈጸመባቸው፡ ኹላችሁ የምታውቁት ዝክረ ነገር ነው። የዛሬዎቹ፡ እናንተስ፡ ምን እያደረጋችሁ ነው? ይህ የዛሬው አገልጋያችን፡ ወደእናንተ እያደረሰ ያለውን መልእክታችንን ተቀብላችሁ ባለመስማታችሁ፡ ምን እየደረሰባችሁ እንደኾነ፡ ይኸው፡ ለአርባ ዓመታት አያችሁት አይደለምን? ለወደፊትስ፡ የሚጠብቃችሁ ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ ካለፋችሁበት ፈተናና መከራ፥ ሥቃይና ዋይታ መማር ያዳግታችኋልን? አያዳግታችሁም።

ይህ አድራጎታችሁ፡ አኹንም፡ እንደእንግዳ ነገር ተቆጥሮ፡ የሚያስገርም ሊኾን እንደማይችል የታመነ ነው። ምክንያቱም፡ ያ የቀደመው፡ ኢትዮጵያዊው ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ፡ ወገኖቹን፡ ከታላቅ ውድቀትና ጥፋት ለማዳን ሲል፡ የተቃዋሚዎቹን ያልተቋረጠ ዛቻና ጥቃት ሳይፈራና ሳይሠቀቅ፡ መልእክታችንን፡ ለሕዝቡና ለአለቆቹ ባለመሰልቸት ያደርስ በነበረበት ጊዜ፡ በእርሱ በኩል፡ በሚበቃ ተናግሮና መክሮ፥ ተማጽኖና አስጠንቅቆ እንደነበረ፥ በእነርሱ በኩል ግን እንዳልሰሙትና እንዳልተቀበሉት ዜና መዋዕሉ ስለሚዘክር ነው።

አዎን! ከኢዮስያስ ዘመን አንሥቶ፡ እስከ ኢዮአቄም፥ ከዚያም፡ በመጨረሻ፡ የባቢሎን ምርኮ እስከኾነበት፡ እስከሴዴቅያስ ዘመን ድረስ፡ በኢየሩሳሌም በነበሩት፡ በይሁዳ ነገሥታት አገዛዝ ሥር ይመሩና ይተዳደሩ የነበሩት፡ "አይሁድ" የተባሉት፡ የእስራኤል ልጆች፡ ጽዋቸው፡ በባቢሎኑ ንጉሥ፡ በናቡከደነፆር አስፈሪ ሠራዊትና የጭካኔ ሰይፍ እጅ ወድቆ ማለቅ፥ ፈራርሶ መቅረትና በምርኮ መወሰድ እንደሚኾን፡ የዚያ፡ የቀደመው ነቢያችን ዝክረ ነገር በተነሣ ቁጥር፡ ይህ ርእሰ ነገር፡ በእየጊዜው ሲወሳ ይኖራል።

ያን የመሰለው ጽዋ፡ የእነዚያ አይሁድ ዕድል ፋንታ የኾነው፡ እግዚአብሔር፡ ከአብርሃም፥ ከይስሓቅና ከያዕቆብ፥ ከእነርሱም በኋላ፡ ከሙሴና ከዳዊት ጋር የተካየዳቸውን ሦስት ኪዳናት፡ በክህደትና በዐመፅ፥ በአምልኮ አመንዝራነትና በልዩ ልዩ የክፋት ሥራ ፈጽመው በማፍረሳቸው፥ ከዚህም የኃጢአት አካኼዳቸው፡ በንስሓ ለመመለስ፡ ምንም ዓይነት፡ የበጎ ፈቃድ ዝንባሌን ሊያሳዩ ባለመቻላቸው እንደነበረም ተነግሩዋል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ የዚያን ነቢየ እግዚአብሔር ስም ብቻ ሳይኾን፡ ፈለጉንም የተከተለው፡ የዚህ ዘመን የተልእኮ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ኾነ፡ ከዚህ ውጭ ላለው፡ ለዚህ፡ ለዛሬው፡ የፍጥረተ ዓለሙ ትውልድ ያደረሰውን፡ የምሕረት መልእክታችንን፡ ይኸው  ትውልድ፡ ሰምቶና ተቀብሎ፡ ምርጫው፡ በእውነተኛ ንስሓ ለመመለስ ሳይኾን ቀረ። እንዲያውም፡ ዓላማና ተግባሩ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በገሃድና በይፋ ሲያካኺድ የኖረውን፡ የክህደትና የዐመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትና የልዩ ልዩ የክፋት ሥራ፡ አኹንም መቀጠል ኾኖ ተገኘ።

ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው ትውልድ፡ ተደጋግሞ እንደተነገረው፡ ራሱን፡ በእውነተኛው ንስሓ ካልመለሰና አካኼዱን ካላስተካከለ በቀር፡ ዕድል ፋንታው፡ በኢየሩሳሌም በነበሩት፡ "አይሁድ" በተባሉት፡ በእስራኤል ልጆች የተጨለጠውን፡ የባቢሎንን መራራ ጽዋን የመሰለ ፍጻሜ እንደሚጠብቀው በማስገንዘብ፡ እነሆ፡ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ የተጠራበትን ተልእኮ፡ በበኩሉ መፈጸሙን አስታውቆን፡ ከእኛ የተቀበለውን፡ ኃላፊነቱንና አደራውን አስረክቦናል።

አዎን! ይኸው፡ ኢትዮጵያዊው አገልጋያችን ኤርምያስ፡ እንዲህ፡ በኃላፊነትና በአደራ፡ ከእኛ የተሰጠውን ተልእኮ፡ ባለው ዓቅሙ፡ ከዚህ፡ አኹን ከሚገኝበት ምዕራፍ አድርሷል። ከእኛ የተሰጠውን፡ ይህንኑ ኃላፊነትና አደራም፡ ለእኛ አስረክቦናል። እኛም፡ መርቀን ተረክበነዋል። ከዚህ በኋላ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ ልጇ ወዳጇና እኔ፤ እኛው ራሳችን፡ ስንመራትና ስናስተዳድራት፥ ስንጠብቃትና ስንቈጣጠራት እንደኖርን ኹሉ፡ አኹንና ወደፊትም፡ ይኸው አያያዝና አሠራር፥ አካኼድና አፈጻጸም፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ የሚቀጥል ይኾናል። በእርሱ አማካይነት ስናስተላልፍላችሁ የቆየውንም የምሥራች መልእክታችንን፡ ልጇ ወዳጇና እኔ፤ ራሳችን፡ እንዲህ፡ በቀጥታ የምናሰማችሁ ኾኖ፡ ዝግጅቱና አቀራረቡ ግን፡ አኹንና ወደፊት፡ እንደተለመደው፡ በእርሱው፡ በኤርምያስ አገልጋይነትና አማካይነት የሚካኼድ ይኾናል።

እንዲያ ባይኾንማ፡ ዛሬ እኛ፡ እናንተን፡ እንዲህ፡ በቀጥታ ልናናግራችሁና ልንመክራችሁ፥ ልንወቅሳችሁና ልናስጠነቅቃችሁ፡ እንደምን ይቻለን ነበር? አያመቸንም ነበር።

"ከእኛ የተሰጠውን፡ የተልእኮ ኃላፊነትና አደራ፡ አስረክበናል። እኛም፡ መርቀን ተረክበነዋል!" ብላችሁም፡ እርሱ ራሱም፡ ይህንኑ፡ የተጠመደበትን አገልግሎት፡ እስከዛሬ፡ ከእናንተ፡ እንደአንዳችሁ ኾኖ፡ በተርታ አገልጋይነት የሚያካኺድ መኾኑን ከመግለጽ ጋር፡ ይህንኑ አገልግሎቱን፡ አኹንም፥ ወደፊትም፡ እንደእያንዳንዳችሁ ኹሉ፡ በዚያው፡ በኖረበት ፈቃደኛነቱና ታማኝነቱ የሚቀጥል መኾኑን፡ በዚህ መልእክቴ ስገልጽላችሁ፡ እናንተ፥ በተለይም፡ ቆራጦቹና ታማኞቹ የአገልግሎት ባልደረቦቹ ልጆቼ፡ በዚህ ዜና እንደምትደሰቱና እንደምትጠናከሩ በማወቅ ነው።

ይህን የአገልጋያችንን፡ የኤርምያስን የግል ውሳኔ፡ በዚህ መልኩ ስንቀበልው፡ እርሱንና ተልእኮውን በሚመለከት፡ በዚህ መልእክቴ ማጠቃለያ ላይ፡ የማስገነዝባችሁ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም:-

በመጀመሪያ፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" በማለታችሁ፡ ወገኖቼ የኾናችሁት፡ እናንተ ብቻ ሳትኾኑ፡ የዓለሙ ሕዝቦች በሙሉ፡ ኹላችሁም፡ ልትሰሙትና ልትቀበሉት የሚገባችሁን መልእክታችንን፡ ወደእናንተ እንዲያደርስ የላክነው፡ እኛ መኾናችንን፣

ቀጥሎ፡ ይዞላችሁ የመጣውና እስካኹን ወደእናንተ ያደረሰው፡ ይኸው መልእክት፡ የእርሱ፥ ወይም፤ የሌላ ሳይኾን፡ የእኛ መኾኑን፣

በመጨረሻም፡ <u>ይህን፡ በእርሱ አማካይነት የደረሳችሁን መልእክታችንን፡</u> ፈቃደኞች ኾናችሁ፡ ተቀብላችሁ ብትፈጽሙት፡ የሚጠቅማችሁ መኾኑን፥ ምናልባት፡ ምርጫችሁና ውሳኔያችሁ፡ የከፋው ወገን በመኾን መኖርን ከመኾኑ የተነሣ፡ ፈቃደኞች ሳትኾኑ ቀርታችሁ፡ ባትቀበሉት፥ ተቀብላችሁም፡ ባትፈጽሙት ግን፡ በየግላችሁም፥ በጋራም፡ እስካኹን፡ በከፋ ኹኔታ ስትጎዱበት እንደቆያችሁ ኹሉ፡ እንግዴህ ወዲህም፡ በበለጠ ተጎድታችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ከእኔ፡ ከኢትዮጵያዋ እናታችሁ፡ በእግዚአብሔራዊው ጸጋ የተቀዳጃችሁትን ልጅነት እስከማጣት ለምትደርሱበት፡ ለሞት ፍጻሜ የምትዳረጉ መኾናችሁን፡ እንድታውቁ ማድረግ ነው።

ይህን ውሳኔያችንን፡ ለመጨረሻ ጊዜ፡ እኔው ራሴ፡ እነግራችሁ ዘንድ፡ አምላኬና መድኃኒቴ እግዚአብሔር አብ፥ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፥ ሕይወቴ ፍቅሬ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ አንዱ አምላክ ፈቅዶልኝ፥ እኔም፡ ተቀብዬ ነው፡ ይኸው፡ ይህን የመልእክት ቃሌን፡ ራሴ ያስሰማኋችሁ።

ከእኛ፡ እስካኹን የተላለፈላችሁ መለኮታዊ መልእክት ኹሉ፥ ወደፊትም የሚተላለፍላችሁ ቢኖር፡ በዚሁ፡ በኢትዮጵያዊው፡ አገልጋያችን፡ በኤርምያስ አማካይነት መኾኑ፡ ያስደነቃችሁና ያስገረማችሁ ትኖሩ ይኾናል። በእርግጥ ካላችሁ፡ ይህ ኹኔታችሁ፡ እውነተኛውን እውቀት ካለማግኘታችሁ የተነሣ የተፈጠረባችሁ ስሜት መኾኑን ልትገነዘቡት ይገባል።

ይኸውም፡ በሰማይም፥ በምድርም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኾነ፡ በሥነ ፍጥረታዊው የመለኮት ሥርዓት፡ ልጆቼ ለኾናችሁት፡ የዓለማቱ ሕያዋን ወገኖች ኹሉ፡ ከፍጥረት በፊት፥ ከፍጥረት በኋላም፡ እግዚአብሔራዊው መልእክት ኹሉ ሲተላለፍላችሁ የኖረው፡ አባታቸውን እግዚአብሔር አብን፥ እናታቸውን ደግሞ፡ እኔን ኢትዮጵያን ድንግል ማርያምን ባደረጉ፡ በታማኞች፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ አገልጋይነት እንደመኾኑ መጠን፡ ለዚህ፡ ለዛሬው ሰብአዊ ትውልድ አገልግሎትም፡ በዚህ ጥሪና ተልእኮ፡ የላክነው፡ የዛሬው አገልጋያችን፡ ኤርምያስም፡ በዚያ መርሕ መሠረት፡ ኢትዮጵያዊ ልጃችን መኾን ስላለበት ነው።

ከፍጥረት በፊት የነበረውን አቀይቼ፡ ከፍጥረት በኋላ፡ ጥንቱኑ፡ ከአዳምና ከሔዋን አንሥቶ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋዋዮች የኾኑትን፥ ከዚያም፡ ነቢያትንና ሓዋርያትን፥ ጻድቃንንና ሰማዕታትን፥ ራሱን፡ ልጄ ወዳጄን ሳይቀር፡ በማናቸውም ጊዜና እስከዛሬ ያሉትን ጭምር ያካተተው፡ ያገልጋዮቻችን ዝርዝር በሙሉ፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ" እንደኾኑት ኹሉ፡ እርሱም፡ ኤርምያስ፡ ኢትዮጵያዊ ኾኖ መገኘት የሚያስፈልገው ኾኗል። ይህ የተልእኮ ጸጋ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ከመጀመሪያውም ቢኾን የተሰጠው፡ ለኢትዮጵያዊው ብቻ ነውና።

እንግዴህ፡ በመደምደሚያው ቃሌ፡ ለኹላችሁ ልጆቼ የምላችሁ፡ ይህ ነው፡- እኔ እናታችሁ፡ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ ራሴን ብቻ ሳይኾን፡ ፍጥረትን ጭምር ልጠቅም የበቃሁት፡ በኹሉም ረገድ፡ ፍጹም ምርጫዬ፡ አንድ እርሱን፡ የቅዱሱ ኪዳን ፈጣሪና አምላክ፥ ባለቤትና ፈጻሚ የኾነውን እግዚአብሔርን ብቻ በመኾኑ ነውና፡ ይህን ሃይማኖታዊ ምግባሬን፡ አብነት አድርጋችሁ በመከተል፡ ስለእየራሳችሁ ስትሉ፡ በእየራሳችሁ እንድትፈጽሙት ይኹን!

ከቸሩ ፈጣሪያችሁ፡ በተፈጥሮ ከተቀዳጃችሁት፡ እውነተኛ ምንነታችሁና መልካም ማንነታችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በፈቃዳችሁና በምርጫችሁ ለይታችሁ፡ የክፉው ወገን ያደረጋችሁ ልጆቼ ካላችሁ፡ በእኔ እናትነትና በልጄ በወዳጄ ቤዛነት፡ በተቀዳጃችሁት የምሕረት ቃል ኪዳንና የንስሓ ጸጋ ተጠቅማችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ወደእኔ ልጅነታችሁ እንድትመልሱ፡ በእናትነት ፍቅሬ፡ አደራ እላችኋለሁ።

በተለይ፡ የእኔንና የልጄ የወዳጄን ጥሪ፡ በራሳችሁ ምርጫና ውሳኔ ተቀብላችሁ፡ ለፍጥረታችን መልካም ህልውና፡ ያቀድነውን ዘለዓለማዊ ዓላማ፡ ከግብ ለማድረስ፡ በመላው ዓለም ተዘርታችሁ ለምትገኙ፥ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ ለአገልጋያችን ለኤርምያስ፡ በቅርብም፥ በሩቅም፡ የክህነት ባልደረቦቼ ለኾናችሁት፥ ወደፊትም፡ ለምትኾኑት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ወንድሞቼና እኅቶቼ ልጆቻችን ኹሉ፡ ይህን እላለሁ፡-

ልጆ ወዳጆ፡ "ወበዓለምሰ ሀለወክሙ፡ ሕማመ ትርከቡ! ወባሕቱ፡ ጽንዑ! እስመ አነ፡ ሞዕክዎ ለዓለም።

"በዓለም ሣላችሁ፡ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን፡ አይዟችሁ! እኔ፡ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።" ደግሞም፡ "ሑሩ! ወመሀሩ፡ ኵሎ አሕዛበ፤ ወናሁ፡ አነ እሄሉ ምስሌክሙ፡ በኵሉ መዋዕል፡ እስከኅልቀተ ዓለም!

"እንግዴህ፡ ኺዱ! ሕዝቦችን ኹሉ አስተምሩ! እነሆ፡ እኔ፡ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ኹልጊዜ፡ ከእናንተ ጋር ነኝ።" እንዳላችሁ፣

እኔም፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት፡ ለነበሩት አገልጋዮች፡ ልጆ ወዳጆ፡ "ኵሎ ዘይቤለክሙ፡ ግበሩ!

"ልጆ ወዳጆ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!" ብዬ የሰጠኋቸውን መመሪያ ተከትለው በመፈጸማቸው፡ በዚያን ጊዜና ቦታ፡ የደረሰው ችግር ተወግዶ፡ ደስታቸው እንደቀጠለ ኹሉ፡ እናንተም፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም ልጆቼ፡ በእርሱና በእኔ ቃል ኪዳን፡ ጸንታችሁ ከኖራችሁ፥ እኔም፥ አምላኬና መድኃኒቴም፥ ልጆ ወዳጆም፥ ሕይወቴ ፍቅሬም፥ በሰማይና በምድር መልተው ያሉት፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት መላእክትና ጻድቃን፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ዐብረናችሁ ነንና፡ በተያያዛችሁት የተቀደሰ ተልእኳችሁ፡ በያላችሁበት ተጠናክራችሁ፡ አገልግሎታችሁን ቀጥሉ!

ልጆ ወዳጆ፡ "ወዘሰ አዝለፈ ትእግሥቶ፡ ውእቱ ይድኅን!

"በትዕግሥቱ፡ እስከመጨረሻው የሚጸና፡ እርሱ ይድናል።" ያላችሁን አትርሱ! (ማቴ. ፲፥ ፳፪፤ ፳፰፥ ፲፱-፳። ዮሐ. ፪፥ ፭፤ ፲፮፥ ፴፫።)

\+ \+ \+

ተዐውደ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።
በበዓለ ትንሣኤሃ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።